በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮምኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

የአማርኛ ቋንቋ ዘያዊ ልዩነቶቹና መምህራንና ተማሪዎች ስለዘዬ ያላቸዉ ግንዛቤ አማርኛን በማስተማር መማር ሂደት የሚያሳድሩት ተጽእኖ በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች ናሙናነት

በ

ፍሬስብሐት ጸጋ

ታህሳስ 2012 ዓ.ም.

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የአማርኛ ቋንቋ ዘያዊ ልዩነቶቹና መምህራንና ተማሪዎች ስለዘዬ ያላቸዉ ግንዛቤ አማርኛን በማስተማር መማር ሂደት የሚያሳድሩት ተጽእኖ በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች ናሙናነት

በ

ፍሬስብሐት ጺጋ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት
የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛ ቋንቋ ለማስተማር ኤም.ኤ ዲግሪ
ማሟያነት የቀረበ ጥናት

አማካሪ

አቶ አክሊሉ ይልማ

ታህሳስ 2012 ዓ.ም.

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና
ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

ድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

የአማርኛ ቋንቋ ዘያዊ ልዩነቶቹና መምህራንና ተማሪዎች ስለዘዬ ያላቸዉ ግንዛቤ አማርኛን በማስተማር መማር ሂደት የሚያሳድሩት ተጽእኖ በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች ናሙናነት

በ

ፍሬስብሐት ጸጋ

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ	ቀን	ፊርማ
--------------------------	----------------------	--------------------
ፈታኝ		
--------------------------	----------------------	--------------------
ፈታኝ		
--------------------------	----------------------	--------------------

ምስጋና

ከመነሻ እስከ መድረሻ የጥናቱን ትክክለኛ አቅጣጫ በመጠቆም ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለአቶ አክሊሉ ይልማ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፤ ለመልካም ትህትናቸዉና ለቀና ትብብራቸዉ የተለየ አክብሮትና አድናቆት አለኝ፡፡በመቀጠልም ለጥናቱ ማካሄጃ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ በመጨረሻም ባለቤቴን ወ/ሮ እታገኝ ሰዉነትንና ልጆቼን ፣ ናሆም እና ቢታንያ ፍሬስብሐትን ለአላማዬ መሳካት ብርታት ሆነዉኛልና ላመሰግናቸዉ እወዳለሁ፡፡

ማውጫ

ምስጋና i

ማውጫ ii

አጠቃሎ iv

ምዕራፍ አንድ 1

መግቢያ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ 1

1.2. የጥናቱ መነሻ 5

1.3. የጥናቱ ዓላማ 6

1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት 6

1.5. የጥናቱ ክልል 7

ምዕራፍ ሁለት 9

ክለሳ ድርሳናት 9

2.1 የዘዬ ምንነት 9

2.2 የዘዬ አይነቶች 11

2.3 የዘዬና የቋንቋ ንጽጽር 13

2.4 ቋንቋን ማስተማርና መማር ከዘዬ ጋር ያለዉ ግንኙነት 15

2.5. ሙያዊ ብቃት 17

2.6. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት 19

ምዕራፍ ሶስት 25

የአጠናን ዘዴ 25

3.1. የጥናቱ ዘዴ 25

3.2. የጥናቱ መረጃ ምንጮች 25

3.3. የናሙና አመራረጥ ዘዴ 25

3.3.1. የትምህርት ቤት ናሙና 25

3.3.2. የክፍል ደረጃ አመራረጥ 26

3.3.3. የመምህራን ንሞና 26

3.3.4. የተማሪ ንሞና 26

3.3.5. የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች 27

3.3.5.1. የጽሁፍ መጠይቅ 27

3.3.5.2. የቃል መጠይቅ 28

3.3.5.3. ሰነድ ፍተሻ 28

3.3.5.4. የቡድን ተኮር ውይይት 29

3.3.5.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ 29

ምዕራፍ አራት 30

የመረጃ ትንተና 30

4.1. ከጽሁፍ መጠይቅና ከቃል መጠይቅ የተገኘው መረጃ ትንተና 30

4.2. ከተማሪዎች የቡድን ውይይትና ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች ትንተና 48

ምዕራፍ አምስት 56

ማጠቀለያና አስተያየት 56

5.1. ማጠቃለያ 56

5.2. አስተያየት 59

ዋቢ መጻህፍት 60

አባሪዎች 65

አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ ዘያዊ ልዩነቶቹና መምህራንና ተማሪዎች ስለ ዘዬ ያላቸዉ ግንዛቤ ቋንቋዉን በማስተማር መማር ሂደት የሚያሳድሩትን ተጽእኖ መመርመር ነዉ፡፡ለጥናቱ ዓላማ በናሙናነት የተመረጡት አራት ትምህርት ቤቶች ናቸዉ፡፡እነዚህም የሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት ፣የብስራት፣ የፊልጰስና የእዉቀት ወገኔ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸዉ፡፡በነዚህ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ ለመረጃ ሰጭነት የተለዩት የክፍል ደረጃዎች 7ኛ ፣ 9ኛ፣ እና 11ኛ ክፍሎች ናቸዉ፡፡8ኛ 10ኛ እና 12ኛ ክፍሎች የጥናቱ መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት የዓመቱን የትምህርት ጊዜ አጠናቀዉ ስለነበር በትምህርት ገበታቸዉ ላይ ሊገኙ ባለመቻላቸዉ አልተካተቱም፡፡ስለሆነም ከ8ኛ፣ ከ9ኛ እና ከ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በቀላል የንሞና ዘዴ 270 ተማሪዎች ተለይተዉ የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሁሉም (25) የአማርኛ መምህራን በግኝት ናሙና ስልት ተካተዉ መረጃ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡መረጃዉም በጽሁፍና በቃል መጠይቆች፣ በቡድን ተኮር ዉይይትና በሰነድ ፍተሻ አማካኝነት ተሰብስቦ ትንተና ተደርጎበታል፡፡ በዚህ መሰረት የተተነተነዉ የጥናቱ መረጃ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡ ተጠኚ መምህራንና ተማሪዎች ዘዬን በተመለከተ ያላቸዉ ግንዛቤ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም በመሆኑ የተለያዩ የአማርኛ ቋንቋ ዘዬዎችን የሚናገሩ መምህራንና ተማሪዎች እርስበርሳቸዉ ቋንቋዉን በማስተማር መማር ሂደት ዉስጥ ቀበልኛ ንግግርን ምክንያት ባደረገ አለመግባባትና መናናቅ ዉስጥ የገቡበት ሁኔታ መኖሩ ተረጋግጧል ፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ዘዬዎች መካከል ስነድምጻዊ ፣ስነምእላዳዊና ስነፍቻዊ ልዩነቶች በመኖራቸዉ በተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ላይ የራሳቸዉን ተጽእኖ ማሳደራቸዉን ተጠኚዎቹ የሰጡት መረጃ አመላክቷል፡፡ እንዲሁም አንዳንድ መምህራን ቀበልኛ ዘዬ ተናጋሪ ተማሪዎችን ለማስተካከል የሚጠቀሙበት ዘዴ የተማሪዎችን ሞራል ያልጠበቀ መሆኑ ታዉቋል፡፡ በሌላ በኩል በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር አዎንታዊ ተጽዕኖም እንዳለዉ ጥናቱ አመላክቷል፡፡ ተጠኚ መምህራን እንዳስረዱት ዘዬ በፈጠራ ስራዎች ዉስጥ ከገጸባህርያት ንግግር በመነሳት መቼትን ለመለየትና ጭብጥን ለማመላከት የጎላ ጠቀሜታአለዉ ብለዋል፡፡ ከሰጡት ምላሽ መረዳት የሚቻለዉም በቋንቋዉ ዉስጥ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር አዎንታዊም አሉታዊም ተጽዕኖዎች ያሏቸዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም በጥናቱ የታዩ አሉታዊ ችግሮች ይቀረፉ ዘንድ መምህራንና ተማሪዎች ዘዬን በተመለከተ የተሻለ ግንዘቤ ኖሯቸዉ የመቻቻል ባህልን በማዳበር መማር ማስተማሩን በጤናማ ሁኔታ ይመሩት ዘንድ የሚመለከታቸዉ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ቢያዘጋጁ የተሻለ ይሆናል፡፡ መምህራንም በበኩላቸዉ መደበኛ ባልሆኑ የአማርኛ ዘዬዎች የሚጠቀሙ ተማሪዎችን በአንዴ መደበኛዉን ዘዬ እንዲላመዱት ማድረግ ስለማይቻል ቀስበቀስ ተገቢዉን ድጋፍና ክትትል ሊያደርጉላቸዉ ይገባል፡፡ የቋንቋዉን ቀበልኛ ንግግሮች ተጠቃሚ የሆኑ መምህራንም ፣ተማሪዎች ሳቁብን አፌዙብን በሚል አላስፈላጊ ንትርክና ሽኩቻ ዉስጥ ሳይገቡ ይልቁንም ተማሪዎችን በልጦ በመገኘት በቋንቋ ዉስጥ ዘዬን ጨምሮ ሌሎች ስነልሳናዊ ልዩነቶች አይቀሬና ተፈጥሯዊ መሆናቸዉን ለማስረዳት መሞከር ይኖርባቸዋል፡፡

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ

የአንድ ቋንቋ ተጠቃሚ የሆኑ ማህበረሰቦች በሚኖሯቸዉ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ልዩነቶች የተነሳ የቋንቋ አጠቃቀማቸዉም ሊለያይ እንደሚችል በማህበረሰባዊ ዕዉቀታችን የምንገነዘበዉ ተጨባጭ እዉነታ ነዉ፡፡ የቋንቋ እና ማህበረሰብ ተመራማሪዎችም በተለያዩ ጽሁፎቻቸዉ ለማስረዳት የሞከሩት ይህንኑ ሀቅ ነዉ፡፡ JennY (1982 ፣124-127)፣ Cristen (1987፣37-48)፣ Sesnan (1997፣90) የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት ሊፈጠር የሚችለዉ በተለያዩ ምክንያቶች መሆኑን ገልጸዋል ፡፡ ምሁራኑ ካሰፈሩት መረጃ መገንዘብ የሚቻለዉም ዕድሜ ፣ጾታ ፣የትምህርት ደረጃ ፣ሙያ ፣መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ በአንድ ቋንቋ ተገልጋዮች መካከል የአጠቃቀም ልነት ሊያስከትሉ የሚችሉ ዐበይት ምክንያቶች መሆናቸዉን ነዉ፡፡ Crutten፥ (1986፣137)ም እንዲሁ ይህንኑ ሀሳብ በሚያጠናክር ሁኔታ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ የነበሩ ማህበረሰቦች በተለያዩ ምክንያቶች መነሻ የቋንቋ አጠቃቀማቸዉን በመቀያየር አንድ ቋንቋ አያሌ ዘዬዎች /anumber of dialects /እንዲኖሩት ሊያደርጉ ይችላሉ ይሉናል፡፡

በእርግጥ ቋንቋ የመግባቢያ አይነተኛ መሳሪያ እንደ መሆኑ መጠን ሰዎች ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ ፍላጎታቸዉን ለማሟላት ሲሉ በተለያዩ አዉዶች ዉስጥ በቋንቋ አማካኝነት ተግባቦትን ይከዉናሉ፡፡የተግባቦት አዉዶች በሚፈቅዷቸዉ ተጨባጭ ሁኔታዎች መሰረት ደግሞ የቋንቋ አጠቃቀም ስልታቸዉን በመቀያየር ዘዬዎችን ይፈጥራሉ ፡፡ በዚህ አግባብ የተፈጠሩት ዘዬዎችም በማህበረሰቡ ንግግራዊም ሆነ ጽሁፋዊ ቋንቋ ዉስጥ ተካተዉ ለአገልግሎት ይበቃሉ፡፡ ዘዬዎች በአንድ ቋንቋ ይገለገሉ የነበሩ ማህበረሰቦች ከፍ ሲል በተጠቀሱት ምክንያቶች መኖር የተነሳ የፈጠሯቸዉ የመግባቢያ ስልቶች በመሆናቸዉ መግባባትን ጨርሶ ሊገድቡ አይችሉም፡፡ሆኖም በመጠኑም ቢሆን የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነቶችን ሊፈጥሩ እንደሚችሉ የምሁራኑ መረጃ በዉል ያስገነዝባል፡፡ በአንድ ቋንቋ ወስጥ ሊኖሩ ከሚችሉ የአጠቃቀም ልዩነቶች አንዱ ዘዬ ነዉ፤ ዘዬ የሌለዉ ቋንቋ ሊኖር አይችልም Cheshire(2007፣22)፡፡

በቋንቋ የጥናት መስክ የስነትምህርትም ሆነ የስነልሳን ምሁራንን ቀልብ ከሚስቡ ጉዳዮች መካከል ዘዬ አንዱ ሆኖ ሳለ በትምህርት ዘርፍ የሚፈለገዉን ያህል ትኩረት እንዳልተሰጠዉ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ለአብነትም Mengstu (2011፣1-3) Frazr(2000 :347)፣እና Schiling(2008፡4)ን ጠቅሰዉ እንደገለጹት የስነልሳን ምሁራን በመጥፋት ላይ የሚገኙ ቋንቋዎችን ለማጥናት ለመተንተንና ለመሰነድ ያደረጉት ሙከራ አበረታች ቢሆንም ለዘዬዎች ግን ትኩረት እንዳልሰጡ አስገንዝበዋል፡፡ Wondimu (2015፣ 18) በበኩላቸዉ (Wolfram (1990)ን በዋቢነት ጠቅሰዉ እንዳስረዱት (ከ1960ዎቹና ከ1970ዎቹ) ጀምሮ የነበረዉ በትምህርት ፖሊሲዉ ዘዬን ጨምሮ ለሌሎች የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነቶች ትኩረት ያለመስጠት ሁኔታ አሁን ድረስ እንዳልተቀረፈ ጠቁመዋል፡፡Hazen (2001) ያቀረቡት ሀተታም እንዲሁ ከመደበኛዉ ዘዬ ባለፈ ለቀበልኛ ዘዬዎች ትኩረት ባለመሰጠቱ ተጠቃሚዎቹ ራሳቸዉ ማህበረሰባዊ ድጋፍ ወዳለዉ መደበኛ ዘዬ የማዘንበል ፍላጎታቸዉ እያደገ መምጣቱን አስገንዝበዋል፡፡ ከላይ የተመለከትናቸዉ የምሁራን ሃሳቦች እነደሚያስረዱት ስነልሳናዊ አጠይቆትን ባላገናዘበ ሁኔታ አንድም በፖለቲካ፣ ካልሆነም በማህበረሰባዊ ምክንያቶች የቋንቋ አጠቃቀም-ልዩነትን /Language Varities/ በእኩል ደረጃ ያለመመልከት ችግር ጎልቶ ይስተዋላል፡፡ Murphy (20 12፣25-28) የአመለካከት ክፍተቱን በተመለከተ ሲያስረዱ፦" ... ሰፊዉ ማህበረሰብ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞች መኖርን ስህተት አድርጎ ይመለከታል፤ለዚህ እሳቤ መስፋፋት ምክንያቱ ደግሞ የግንዛቤ አጥረት መሆኑ ይታወቃል "ብለዋል፡፡

በማህበራዊ ስነልሳን ዘርፍ የተሰማሩ የመስኩ ምሁራን ቋንቋንና አጠቃላይ የቋንቋ መገለጫ ባህርያትን በተመለከተ በተጠቃሚዉ ማህበረሰብ ግንዛቤ ለመፍጠር ሰፊ ጊዜ ወስደዉ ብዙ ጽፈዋል ብዙ መረጀዎችን አደራጅተዋል፡፡ይሁን እንጅ ከቋንቋ ጋር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ያህል ትስስር ያለዉን ዘዬን በተመለከተ የምናገኛቸዉ መረጃዎች ግንዛቤ ለማግኘት በቂ ናቸዉ ለማለት አያስችሉም፡፡ Mengstu (2011 ፣5)ባቀረቡት ጥናት Tadmor (2004)ን በዋቢነት ጠቅሰዉ ሲያስረዱ፣ በአለማችን ዘዬዎችን በማጥናት፣ በመተንተንና በመሰነድ ረገድ ያለዉ ትኩረት አነስተኛ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ አክለዉም ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ ሙያተኞች አያሌ መጻህፍትና መጣጥፎችን ስለቋንቋ መዳከምና መጥፋት በሰፊዉ የመጻፋቸዉን ያህል ዘዬን በተመለከተ ግን በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ ስለመኖሩ እስኪዘነጋ ችላ ያሉበት ሑኔታ መስተዋሉን ገልጸዋል፡፡እንደተባለዉም ዘዬ በመዘንጋቱ ምክንያት ዘያዊ አጠቃቀም እየተዳከመና በአስገራሚ ሁኔታ እየተለወጠ ከቋንቋዎች መጥፋት ጋርም አብሮ እየጠፋ መሄዱ አልቀረም፡፡ በሌላ በኩልም ማህበረሰቡም ስለዘዬ ያለዉ ግንዛቤ እንዲቀንስ በር

ከፍቷል፡፡ይህም በመሆኑ በዘዬዎች መካከል ብልጫ እንዳለና የራስን ከፍ አድርጎ በአንጻሩ የሌሎችን ደግሞ ዝቅ አድርጎ የመመልከት አዝማሚያ ይታያል፡፡ Mengstu (2011) በጥናታቸዉ እንዳመለከቱት አማርኛ ቋንቋ ካሉት የጎጃም ፣የጎንደር ፣የወሎ ፣ የሸዋ እና የአዲስ አበባ ዘዬዎች መካከል የአዲስ አበባዉን ዘዬ አስበልጦ የማየት እና ሌሎችን ደግሞ ዝቅ አድርጎ የመመልከት ሁኔታ አለ፡፡ችግሩ በዚህም ሳያበቃ ከመደበኛዉ ዘዬ ዉጭ ያሉትን ዘዬዎች የሚናገሩ ማህበረሰቦች ትክክለኛዉን የአማርኛ ቋንቋ ዘዬ መጠቀም ያልቻሉ አድርጎ የመቁጠር ሁኔታም ጎልቶ ይታያል፡፡እዚህ ላይ መታየት ያለበት ዋናዉ ነጥብ መደበኛዉ ዘዬ ለምን ተቀባይነት ኖረዉ? የሚለዉ ሳይሆን ምሁራን ለአብትም /Ginn 2005)፣ (Murphy 2012)፣ Mengstu(2011)መደበኛ ያልሆኑ ክልላዊ ዘዬዎችም የልማዳዊ ጥበቦች ፣ስነጽሁፎችና ትዉፊቶች መፍለቂያ በመሆናቸዉ ለመደበኛዉ ዘዬ ብቻ ትኩረት በመስጠት ሌሎቹ እንዲዳከሙ መሆን የለባቸዉም የሚለዉ ገዥ ሃሰብ ነዉ፡፡ዘዬዎች ከስነጽሑፍነትና ከትዉፊትነትም ባለፈ የማንነት መገለጫዎችም ናቸዉ፡፡ (ባዬ 2000፣xi) ይህንን ሀሳብ ሲያስረዱ ". . .ዴዴብ የሚለዉን ወሎዬ አልበልቶም ከሚለዉ ጎጃሜ፣ባኤላ የሚለዉን መንዜ የግዳስ ጨቅሎችን ከዉናቸዉ ከሚለዉ ጎንደሬ በቃል አመራረጡና አጠቃቀሙ መለየት ይቻላል፡፡" ብለዋል፡፡ ከላይ ከተመለከትናቸዉ ሀሳቦች እንደምንረዳዉ በአንድ ቋንቋ ዉስጥ የሚፈጠሩ የተለያዩ ቀበልኛ አነጋገሮች የተፈጠሩበት የራሳቸዉ የሆነ ጠቀሜታ ያላቸዉ በመሆኑ መጥፋት ስለሌለባቸዉ ልንታደጋቸዉ ይገባል፡፡ ለችግሩ እልባት ለማስገኘት ሲታሰብ የመጀመሪያዉ ነጥብ ሊሆን የሚችለዉ ደግሞ እንደ (Murphy (2012፣28)ማብራሪያ/ገለጻ/ ማህበረሰባዊ ግንዛቤ መፍጠር ነዉ፡፡ የዚህ ጥናት አቀራቢም በማስተማር ስራ በቆየባቸዉ ጥቂት የማይባሉ ጊዜያት ተማሪዎችንና መምህራንን ጨምሮ ሰፊዉ ማህበረሰብ በዘዬ አጠቃቀምና እንዲሁም በቀበልኛ ተጠቃሚዎች ላይ ያለዉ አመለካከት የተዛባ መሆኑን መታዘብ ችሏል፡፡የጥናቱ አቅራቢ የጎጃም ዘዬ በሚነገርበት አካባቢ ያደገና የተማረ እንደመሆኑ መጠን እንደ አንድ ቀበልኛ ንግግር ተጠቃሚ መደበኛዉ የአማርኛ ዘዬ በሚነገርበት የአዲስ አበባ ከተማ ማህበረሰብ ጋር /ተማሪዎችን ጨምሮ/ አብሮ በመኖር መስተጋብር ያጋጥሙት የነበሩ ችግሮች ይህን ጥናት ለማካሄድ መነሻ ሆነዉታል፡፡

አጥኚዉ ይህን ጥናት ለማካሄድ ሲወስን በመጀመሪያ በተመሳሳይ ርእሰ ጉዳይ የተካሄዱ ቀደምት ስራዎችን ለመዳሰስ ሞክሯል፡፡በዚህም መሰረት በቀጥታም በተዘዋዋሪም ዘዬን በተመለከተ የቀረቡ የተወሰኑ ስራዎችን ማግኘት ችሏል፡፡በአማርኛ ቋንቋ የቀረቡ ጥናቶች በምዕራፍ ሁለት በቀደምት ስራዎች ቅኝት ክፍል ተተንትነዉ የቀረቡ በመሆኑ በዚህ ክፍል በእንግሊዝኛ ቋንቋ የቀረቡ ስራዎችን ብቻ እንመለከታለን፡፡ Murphy (2012) "ዘያዊ ግንዛቤን

በኮሌጅ ደረጃ በድርሰት ትምህርት ክፍለ ጊዜ ማስተማር "በሚል ርዕስ ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ በመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች ተተኳሪነት ጥናት አካሂደዋል፡፡ተጠኚዎቹ ስለማህበራዊ ስነልሳን በክፍል ዉስጥ በተግባር ትምህርቱ እየተሰጣቸዉ ግንዛቤአቸዉም እየተገመገመ ተማሪዎች ዘዬን በተመለከተ ያሳዩት የነበረዉ የተዛባ አመለካከት እየተሻሻለ መሄዱና ዘዬዎችንና የየዘዬዎቹን ተጠቃሚዎች በእኩል ዐይን ወደማየት ደረጃ መድረስ መቻላቸዉን በጥናቱ አመልክተዋል፡፡በጥናቱ ተማሪዎች የግንዛቤ ክፍተት ያለባቸዉ መሆን አለመሆኑን በክፍል ወስጥ ትምህርቱ ተካትተዉ በሚቀርቡ የተለያዩ ተግባራት እየተፈተሸ ራሳቸዉ ተማሪዎቹም የመፈትሄ ሀሳቦችን እንዲያመነጩ እየተደረገ የተሻለ ግንዛቤ ለማስጨበጥ መቻሉን ጥናቱ ያስረዳል፡፡

Schuchi (2013) በበኩላቸዉ"የባንግላ" ዘዬ እንግሊዝኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት የሚኖረዉ ተጽእኖ" በሚል ርእስ ጥናት አካሂደዋል፡፡በጥናቱም ዘዬ እና እንግሊዝኛን ማስተማር ፣የዘዬ ብያኔ ፣ቋንቋ? ወይስ ዘዬ?፣ መደበኛ እንግሊዝኛ ፣የንበት ደረጃ ፣ዘዬዎች ፣በባንግላዲሽ ዉስጥ የሚሉት ርእሰ ጉዳዮች በዝርዝር ተብራርተዉ ቀርበዋል፡፡የጥናቱ ዉጤት እንዳመለከተዉ በባንግላ ዘዬ አፍ -ፈት ተማሪዎች እንግሊዝኛን ለመማር የአፍ መፍቻ ቋንቋቸዉ ተግዳሮት እንደሆነባቸዉ ተጠቅሷል፡፡

በሌላ በኩል Snell & Andreiws (2014)" ዘዬና ቅላጼ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በማንበብ ሂደት ተጽዕኖዉ ምን ይመስላል?" በሚል ርዕሰ ጉዳይ ጥናት አካሂደዋል፡፡በምርምር ስራቸዉም የንግግር አንግሊዝኛ ከጽሁፍ እንግሊዝኛ ይልቅ ተለዋዋጭነት አንደሚታይበት አስረድተዋል፡፡ በሁለቱ የክሂል አጠቃቀሞች መካከል ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት እንደሌለ በጥናቱ መረጋገጡ ተጠቁሟል፡፡ ህጻናትና ወጣቶች በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ የዘዬ አጠቃቀሞች እንደ አስፈላጊነታቸዉ ሁለቱንም ስልቶች እያቀያየሩ መጠቀም የሚችሉ መሆናቸዉ ተጠቁሟል፡፡ በንግግር እንግሊዝኛ አጠቃቀምና በጽህፈት እንግሊዝኛ አጠቃቀሞች መካከል ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለመኖሩን ጥናቱ ማሳየቱን ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡ በክፍል ዉስጥ በሚሰጥ ትምህርት ዉጤታማ ለመሆን ተማሪዎች የሚያደርጉትን ጥረት ለቀበልኛ ዘዬና ለቅላጼ /Dialect &Accente የሚሰጠዉ አሉተዊ ግምትና እንዲሁም መምህራን የሚሰጡት ተገቢ ያልሆነ ምላሽ በተማሪዎች ዉጤት ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽእኖ የሚፈጥር መሆኑ በጥናቱ ተጠቅሷል፡፡

በመጨረሻ የምንመለከተዉ" ዘዬ ተናጋሪነት በትምህርት ላይ የሚኖረዉ ዉጤት /effect/" በሚል ርእስ Yuksin & Van (2014) የቀረቡት ስራ ነዉ ፡፡ ምሁራኑ በዚህ ጥናት ዘዬ

በተማሪዎች ትምህርት አቀባበል ላይ የሚያስከትለዉን ጫና ፈትሸዋል፡፡የጥናቱ ዉጤትም ዘዬ ለቋንቋ ትምህርት አቀባበል አሉታዊ ተጽዕኖ ያለዉ ሲሆን፣ ከሂሳብ ትምህርት አቀባበል ጋር ደግሞ ምንም ግንኙነት የሌለዉ መሆኑን ጠቁሟል፡፡

ከላይ በቅደም ተከተል የተመለከትናቸዉ ስራዎች ከዚህ ጥናት ጋር የሚቀራረቡት ዘዬንና ትምህርትን አስተሳስረዉ የተካሄዱ ሥራዎች መሆናቸዉ ነዉ፡፡ሁሉም ጥናቶች ዘዬ በትምህርት መስክ እንደ አጠቃላይ፣ በተለይ ደግሞ የቋንቋን ትምህርት በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ሊኖሩት ስለሚችሉጠቀሜታዎችና እንዲሁም ተጽዕኖዎች በስፋት የተነተኑ መረጃዎቸን የያዙ በመሆናቸዉም ለዚህስራ ግብአት በመሆን አገልግለዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር ይህ ጥናት በአንድ ቋንቋ (በአማርኛ) ዉስጥ ያሉ ዘዬዎች ቋንቋዉን በመማር ማስተማር ሂደት የሚኖራቸዉን ተጽዕኖ የሚፈትሽ በመሆኑ፣ ዘዬን ሁለተኛ ቋንቋን በማስተማር መማር ሂደት ጋር አስተሳስረዉ ካጠኑት ስራዎች ይለያል ፡፡በተጨማሪም ይህ ስራ በተጠኝነት የተለዩ መምህራንና ተማሪዎች ዘዬን በተመለተ ያላቸዉን ግንዛቤም ስለሚፈትሽ ከነዚህ ጥናቶች ይለያል፡፡

1.2. የጥናቱ መነሻ

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በሚሊየም ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ በፊልጶስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በዕውቀት ወገኔ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤትና በብስራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ነው፡፡ ስለሆነም ጥናቱ በተጠቀሱት ትምህርት ቤቶቸ ተተኳሪነት የአማርኛ ቋንቋ ዘያዊ ልዩነቶቹና ተማሪዎችና መምህራን ስለዘዬ ያላቸው ግንዛቤ ቋንቋውን በማስተማርና መማር ሂደት የሚያሳድሩትን ተጽእኖ በመፈተሽ ላይ ያተኩራል፡፡ የዚህ ስራ አቅራቢ ይህን ርዕስ ሊመርጥ የቻለባቸው ሶስት አበይት ምክንያቶች አሉ እነዚህም፦

- አጥኚው አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስራ በቆየባቸው አስራ ሁለት ዓመታት የስራ ልምዱ የአማርኛ ቋንቋ ልዩ ልዩ ዘዬዎች ከአካባቢ አካባቢ ስለሚለያዩ፣ በመምህራንም ሆነ በተማሪዎች ዘንድ የሚያሳድሩትን አንዳንድ የተራክቦ ተግዳሮቶች በማስተዋሉ በጉዳዩ ላይ ጥናት ለማካሄድ ፍላጎት ሊያድርበት ችሏል፡፡
- አጥኚዉ ለኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን፣“አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ” በሚል በአዲስ መልክ የታተሙ የአማርኛ መጽሐፎችን ከመምህራኑ ጋር ለማላመድ ተፈልጎ ይሰጥ

በነበረው ስልጠና በአሰልጣኝነት ተሳትፎ ነበር፡፡በስልጠናዉ ወቅት አንዳንድ መምህራን ሀሳባቸውን በንግግር ሲገልጹ ቀበልኛ ዘዬዎችን አብዝተው ሲጠቀሙ በማስተዋሉ መደበኛውን ዘዬ በማስተማር ሂደት ሊያጋጥማቸዉ የሚችለዉን ችግር ለመዳሰስ በመሻት በዚህ ርእስ ጥናትና ምርምር ለማካሄድ ተነሳስቷል፡፡

- በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም በዚህ ርዕስ የተጠኑ ስራዎች ባለመኖራቸዉ ክፍተት በመሙላት ረገድ ቅንጣት ታህል አስተዋጽኦ ስለሚኖረዉ ይህ ጥናት ይካሄድ ዘንድ ለአጥኚዉ መነሻ ምክንያት ሆኗል፡፡

1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ ዘያዊ ልዩነቶቹና ተማሪዎችና መምህራን ስለአማርኛ ዘዬዎች ያላቸው ግንዛቤ ቋንቋውን በማስተማርና መማር ሂደት የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ መመርመር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ ስራ የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎችም ይኖሩታል፡፡እነዚህም፡-

- ተጠኚዎች ስለዘዬ ያላቸዉን ግንዛቤ መፈተሽ፣
- ዘያዊ ልዩነት በመምህራንና በተማሪዎች ተግባቦት የሚያሳድረውን ተጽዕኖ መመርመር፣
- በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር ቋንቋዉን በማስተማር መማር ሂደት የሚኖራቸዉን ተጽዕኖዎቸ ማሳየት፣
- መምህራን ቀበልኛ ዘዬ ተናጋሪ ተማሪዎችን ለማረም የሚሞክሩበትን የግብረመልስ አሰጣጥ ሁኔታ መፈተሽ፣
- አማርኛ ቋንቋ በማስተማር መማር ሂደት ዘዬን አስመልክቶ ለሚታዩ ችግሮች መወሰድ የሚኖርባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦቸ መጠቆም የሚሉት ናቸዉ፡፡

1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት በተነደፈለት ዓላማ መሰረት ተካሂዶ ዳር ሲደርስ ያስገኛቸዋል ተብሎ የሚ ገመቱት ጠቀሜታዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡፡

ሀ. የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር መማሩ ሂደት የተሻለ ሁኔታ ለመፍጠር የራሱ ሚና ይኖረዋል፡፡

ለ. በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችና መምህራን ወደ አማርኛ ቋንቋ መደበኛ ዘዬዎች ትኩረት እንዲያደርጉ ተጽዕኖ የመፍጠር ሚና ይጫወታል ፡፡

ሐ. ጥናቱ ለመምህራንና ተማሪዎች በቋንቋው ውስጥ ስለሚ ገኙ ዘያዊ ልዩነቶች ሰፊ ግንዛቤ ስለሚፈጥር ሁለቱንም ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡

መ. ይህን ጥናት የማንበብ ዕድሉ ለሚያጋጥማቸው የስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች በአጠቃላይ፣ እና ለአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች በተለይ፣ ቋንቋና ዘዬን አስመልክቶ መደረግ /መታቀድ/ ስለሚገባቸው አንዳንድ ጉዳዮች መጠነኛ አመላካች መንገዶችን ወይም ጥቆማዎችን ይሰጣል፡፡

ሠ. በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ሰፊና ጥልቅ ጥናት ማካሄድ ለሚፈልጉ ወገኖች እንደመነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

1.5. የጥናቱ ክልል

የዚህ ጥናት ትኩረት የአማርኛ ቋንቋ ዘያዊ ልዩነቶቹና ተማሪዎችና መምህራን ስለዘዬ ያላቸውን ግንዛቤ መመርመር ነዉ፡፡ ይህን ለማድረግም አማርኛን በማስተማር መማር ሂደት በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኙ የመሰረተ ዕድገት፣ የዕውቀት ወገኔ፣ የፊልጶስ እና የሚሊኒየም ፪ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች በዓላማ ናሙና በተጠኝነት ተመርጠዋል፡፡ በነዚህ አራት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ መምህራንና ተማሪዎች የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ ምንም እንኳን መረጃ ሰፋ አድርጎ ለመሰብሰብ ሌሎች መሰል ተቋማትንም ማካተቱ የበለጠ ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል ቢገመትም ይህን ለማድረግ አልተሞከረም፡፡ ምክንያቱም አጥኚው ይህንን ጥናት የሚያካሂደው መደበኛ የማስተምር ስራውን እያካሄደ ጎንበጎን ባለው ትርፍ ጊዜ በመሆኑ፣ በነበሩበት የጊዜ፣ የገንዘብና የአቅም ውሱንነቶች የተነሳ ከፍሲል ስማቸው ከተዘረዘሩ ተቋማት ውጪ ሌሎችን አላካተተም፡፡፡ በአጭሩ የፊልጶሥ፣ የመሰረተ ዕድገትና የብስራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና የሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች በጥናቱ የተተኮረባቸው ተቋማት ናቸው፡፡በሶስቱም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመረጃ ሰጪነት የተሳተፉት የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ ናቸው፡፡፡ ምክንያቱም ከመጀመሪያ እርከን

(ከ1ኛ-5ኛ ክፍል) ተማሪዎች ይልቅ የተሻለ መረጃ ሊገኝ የሚችለው በሁለተኛዉ እርከን ከ(5-8)ከሚማሩ ተማሪዎች ነዉ በሚል ስለታሰበ ነው፡፡፡ይህም ሆኖ፣ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ያልተካተቱበት ምክንያት ደግሞ መረጃው በሚሰበሰብበት ወቅት የዓመቱን የትምህርት ጊዜ አጠናቀው የ8ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናን ለመውሰድ በመጠባበቅ ላይ ስነበሩ ነው፡፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መካከል የ10ኛ እና የ12ና ክፍል ተማሪዎችም የዓመቱን ትምህርት አጠናቀው የብሔራዊ ፈተናውን ለመውሰድ በዝግጅት ላይ የነበሩ በመሆኑ በዚህ ጥናት አልተሳተፉም፡፡፡ በመሆኑም መረጃ የተሰበሰበው በተራ የዕጣ ናሙና ስልት ከተለዩት የ9ኛ እና የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ ነው ፡፡

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት

2.1 የዘዬ ምንነት

በቃላዊውም ሆነበጽሁፋዊው የቋንቋ ተግባቦት አንድን ቋንቋ የሚጠቀሙ ማኅበረሰቦች የሚያሳዩዋቸው የአጠቃቀም ስልት ልዩነቶች አሉ፡፡ እነዚህን ልዩነቶች የመስኩ ምሁራን ዘያዊ ልዩነቶች /dialectal variations/ በሚል ጽንሰ ሐሳብ ይገልጿቸዋል፡፡

ከቋንቋ አጠቃቀም አኳያ የሚከ4t/ሰት ልዩነትን አስመልክቶ የተለያዩ መረጃዎችን ለመስጠት የሞከሩ የዘርፉ ጠበብቶች በሀተታቸው የዘዬን ምንነት ሳይቀር ተንትነው ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ለአብነት ይሆኑን ዘንድ የተወሰኑትን ቀጥሎ እንመልከት፡፡

Harding & Philip (1996፣ 37) ዘዬን ሲገልጹ በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚታይ (ከድምጽ፣ ከምዕላድ፣ ከቃላት…) አኳያ ልዩነት የሚያሳዩ ምናልባት ከተናጋሪዎች የብዙ ጊዜ መራራቅና ግንኙነት መቋረጥ የተነሳ ወደተለያዩ ቋንቋዎች ሊያድጉ የሚችሉ የአነጋገር ስልቶቸንን ሊያካትት እንደሚችል አስረድተዋል፡፡

Chambers &Trudgil (2004፣5) በበኩላቸዉ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ብያኔ በሚያጎለብት መልኩ ዘዬ በአንድ ቋንቋ ተጠቃሚዎቸ መካከል በድምጾቸ፣ በቃላት ፣ በሰዋስዉ እንዲሁም በፍች ደረጃ የሚታይ ተግባቦታዊ ልዩነት መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

ከቀረበው ብያኔ የምንገነዘበው በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚታዩ የአነጋገር ልዩነቶች በቋንቋዉ የተለያዩ መዋቅሮች ሊከሰቱ የሚቸሉ መሆናቸዉን ነዉ ፡፡ ምንም እንኳ ልዩነቶች ተግባቦትን ሊገድቡ የሚቸሉ ባይሆኑም ግዝፈት ነስተዉ ሊታዩ የሚቸሉባቸዉ ደረጃዎቸ ከላይ እንደተገለጹት ከትንሹ የቋንቋ አሀድ ከድምጽ ጀምሮ ሊታዩ የሚቸሉ መሆናቸዉን ነዉ፡፡

Columas (2005፣112)ም እንዲሁ ዘዬ ማለት በድምጽ ስርአታቸው በቃላትና አልፎ አልፎም በአረፍተ ነገር አገባባቸው አኳያ አንዳቸው ካንዳቸው በትንሹ የሚለዩ የአንድ ቋንቋ ዘርፎችን የሚመለከት የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችል አስረድተዋል፡፡

Richards, Platt & Weber (1985) ዘዬን አስመልክቶ ሲያብራሩ ዘዬ ሕዝቦች ቋንቋን የሚጠቀሙበት መንገድ መሆኑን ጠቅሰው ተናጋሪዎቹ ዘዬን ሲጠቀሙም የተለያዩ የመጠቀሚያ ቅጥንብሮች/ Patterns/ እንዳሏቸው አመላክተዋል፡፡ ከነዚህ መከሰቻዎች

መካከልም (ንበት፣ የአነጋገር ቅላፄ፣ ቃላትና ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች) በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

Morshed (2006፣94)ደግሞ የሕዝቦች የቋንቋ አጠቃቀም በኢመደበኛና በመደበኛ አጠቃቀም ፈርጆች ሊታይ ይችላል ይሉናል፡፤ ይሄዉም መደበኛ ቋንቋ ከጫፍ ጫፍ በአንድ ሃገር ውስጥ ሊያገለግል ሲችል፣ ዘዬ ከአካባቢ ወይም ከማህበረሰብ አንፃር ተወስኖ ሊታይ የሚችል ነው በማለት ዘዬን ከቋንቋ አነጻጽረዉ ለማየት ሞክረዋል፡፡

ይህ ከፍ ሲል የተመለከትነው ሐሳብ እንደሚያመላክተው አንድ ቋንቋ በተጠቃሚዎቹ ዘንድ በመደበኛ ደረጃ እና መደበኛ ባለሆነ መልኩ ግልጋሎት ሊሰጥ የሚችል ነው፡፡፡ መደበኛው የቋንቋ ተጠቃሚውን በተመሳሳይ ሁኔታ ሊያግባባ የሚችል ሲሆን፣ቀበልኛዉ አጠቃቀም ግን ከቃላት ፍቺ፣ ከንበት ወይም ከሰዋስው አንጻር መጠነኛ ተግባቦታዊ ልዩነት የሚታይበት ነው፡ሊባል ይችላል፡፡

Groves(2008፣8)በበኩላቸዉ በዘዬና በቋንቋ መካከል ያለዉን ልዩነት በቀላሉ ለመረዳት እንደሚያስቸግር አስገንዝበዋል፡፡አክለዉም የሁለቱን ልዩነት ለመገንዘብ የሚደረገዉ ሙከራ ሁለቱ የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነቶች ከሚሰጡት ጠቀሜታ አንጻር መታየት የሚችል ነዉ ብለዋል፡፡ምክንያቱን ሲያስረዱም የሁለቱን ልዩነት ለመገንዘብ ተናጋሪዎቹ ሃሳባቸዉን ያለምንም ችግር መለዋወጥና መግባባት ከቻሉ ሁለቱ ወገኖች የአንድ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬ ተናጋሪዎች ተደርገዉ ሊታዩ ይቸላሉ፡፡በሌላ በኩል በሁለቱ ተጠቃሚዎች መካከል በሚኖረዉ ተግባቦት ሃሳብ ለሃሳብ መለዋወጡ አሰቸጋሪ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ እንደ Groves ሀተታ ለመግባቢያነት የተጠቀሙት በተለያዩ ቋንቋዎች እንጅ በዘዬዎች አልነበረም ማለት ነዉ፡፡

እስካሁን በተከታታይ የተመለከትናቸው ማብራሪያዎች ስለዘዬ ምንነት የቀረቡበትን አግባብ

ስንመለከት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ላይ ጥናትና ምርምር ካካሄዱ ምሁራን ምንጮች የተገኙ ናቸው፡፡፡ ከዚህ በመቀጠል ይህ ጥናት የሚያጠነጥነው በአማርኛ ቋንቋ ዘዬዎች ላይ እንደመሆኑ መጠን የዘዬን ምንነት ከአማርኛ ቋንቋ አንፃር ለማስገንዘብ የተሞከረበትን ተከታዩን ብያኔ እንመልከት፡፡

ዘሪሁን (1992፣ 94) አንድ ቋንቋ በሚነገርበት አካባቢ ልዩነት ምክንያት የተለያዩ ዘዬዎች ሊኖሩት እንደሚችሉ አስረድተዋል፡፡አክለዉም አማርኛ ቋንቋ ያሉትን ክልላዊ ዘዬዎች በምሳሌነት ተጠቅመው ለማስገንዘብ ሞክረዋል፡፡ ይኸዉም ቋንቋው አማርኛ ተናጋሪ በሆኑ

አካባቢዎች የሚነገሩ ልዩ ልዩ ዘዬዎች ያሉት ሲሆን የጎንደርና የሸዋ ፤እንዲሁም የወሎና የጎጃም ቋንቋ በሚል ተለምዷዊ አጠራር መጥራት የተለመደ መሆኑን ገልጸዋል።

ዘሪሁን ያቀረቡት ብያኔ ቀደም ሲል ከተመለከትናቸው በሌሎች ምሁራን ከቀረቡት ብያኔዎች አንፃር ሲታይ በአማርኛ ቋንቋ ላይ በመመሥረትና የቋንቋውን የተለያዩ ዘዬዎች በማሳወቅ ጭምር የቀረበ በመሆኑ መጠነኛ ልዩነት ይታይበታል። ይሁን እንጅ የዘዬን ምንነት ለማስገንዘብ ታልሞ ከፍ ሲል ከተለያዩ ምሁራን ምንጮች ተቀንጭበዉ ከቀረቡት ብያኔዎች በአንድም ይባል በሌላ የሚመርጧቸዉ ቃላት እና የሚጠቀሟቸው አረፍተ ነገሮች ይለያዩ ካልሆነ በስተቀር የሚያጠነጥኑት በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ነው ማለት ይቻላል። ሁሉም ብያኔዎች ዘዬን ሲያብራሩ በአንድ ቋንቋ ውስጥ ከቅላፄ፣ ከቃላት ፍቺ፣ እንዲሁም ከሰዋስው አንፃር ወዘተ ሊታይ የሚችል የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት መሆኑን በማሳየት ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ከሚያትቱትቁምነገር አንጻር ተመሳስሎ እንጅ ልዩነት የላቸዉም።

2.2 የዘዬ አይነቶች

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ዘዬ ሲባል የአንድ ቋንቋ ተጠቃሚ በሆኑ በተለያዩ መልክዓምድራዊ ክልሎችና መደቦች ወይም የማህበረሰቡ ክፍሎች መካከል ያለ የአነጋገር ልዩነት ነው። ይህ ልዩነት በግለሰብ ደረጃ፣ በማኀበረሰብ ደረጃ አልያም በአካባቢ ደረጃ ተወስኖ ሊታይ የሚችል እንደሆነ በመስኩ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ያስረዳሉ። በዚህም መሰረት በግለሰብ ደረጃ የሚታየውን ዘዬ ግለዘዬ /idolect/፣ በማህበረሰብ ደረጃ የሚታየውን ዘዬ ደግሞ ማኀበራዊ ዘዬ (sociolect)፣ እንዲሁም በአካባቢ ተወስኖ የሚገኘውን ዘዬ ደግሞ አካባቢያዊ (geolect) በሚል ሥያሜ መጥራት የተለመደ መሆኑን በሙያዉ ምሁራን የቀረቡ ገለፃዎችና ማብራሪያዎች ያስረዳሉ።በተለያዩ ምንጮች ከቀረቡ መረጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው የዘዬ አይነቶች በሶስት ተከፍለው መታየት የሚችሉ ናቸው። እነዚህም ግለዘዬ፣ ማህበራዊ ዘዬና አካባቢያዊ ዘዬ የሚባሉት ናቸው።

ሀ. ግለዘዬ /idolect:-

ግለ-ዘዬ ቃሉ በቁሙ የያዘዉ ጽንሰ ሀሳብ እንደሚያመለክተዉ እያንዳንዱ ግለሰብ በግሉ የሚያሳየዉ የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ነዉ ሊባል ይችላል።ለግለሰቡ ለራሱ ብዙም የማይታወቅ ነገር ግን ለሌሎች ሰዎቸ በግልጽ ሊታይ የሚቸል የማንነት ማሳያ /መታወቂያ የቋንቋ አጠቃቀም ዘዴ ነዉ ። እንደ ባዬ (2000፣ xi) ገለፃ ግለዘዬ የአንድን ግለሰብ ንግግር ብሎም ማንነት የሚመለከት፣ ከግለሰቡ የንግግር ፍሬሐሳብ፣ ከአነጋገሩ ለዛ፣ ከቃላት

አመራረጡ፣ ከድመፅ አወራረዱ አንፃር ስለ ግለሰቡ አንዳንድ ነገሮችን ከሞላጎደል በትክክል መናገር የሚያስችል ነዉ ማለት ይቻላል፡፡ Arndt (2000 ፣129) እና ሌሎች በበኩላቸው ግለዘዬ ከአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረቦች መካከል የግለሰቦችን የቋንቋ አጠቃቀም ከድምጽ ይዘት እና እንዲሁም ከአካላዊ ሁኔታዎች አንፃር ተመልክቶ የግለሰቡን ማንነት ለያሳይ የሚችል የቋንቋ አጠቃቀም ስልት መሆኑን ለማሳየት ሞክረዋል፡፡

ለ. ማኅበራዊ ዘዬ /sociolect/

ማህበራዊ ዘዬ የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ከማህበረሰብ አንፃር የሚቃኝበት /የሚተነተንበት/ ነው ማለት ይቻላል፡ በተለያዩ የመስኩ ምሁራን የቀረቡ ብያኔዎችም የሚያመለክቱት ይህንኑ ማህበረሰብ ተኮርነቱን ነዉ፡፡ ማሳያ ይሆኑን ዘንድ እስኪ ጥቂቶቹን ለመመልከት እንሞክር ፦ wardaugh (2010፣23) የማህበራዊ ዘዬን ምንነት ሲያስረዱ" ማህበራዊ ደረጃን /Social Position/ ፣መሰረት ያደረገ በስራ፣ በመኖሪያ አካባቢ፣በገቢ መጠን፣በባህላዊ አዉድ፣በእምነትና በሌሎች መሰል ተቀራራቢ የሆኑ ማሕበረሰቦቸ የጋራ ፍላጎትን ለማሟላት በሚፈልጉበት አዉድ ዉስጥ የሚገለገሉበት የዘዬ አይነት መሆኑን ለማስገንዘብ ሞክረዋል፡፡

Hudson (1996፣23-25)፣ ቋንቋ ተናጋሪ በሆነ ህብረተሰብ ውስጥ በሚኖረው ማህበረሰባዊ ክፍፍል /የፆታ፣ የእድሜ፣ የሙያ ወዘተ) ሳቢያ በሚፈጠሩ ጥቃቅን ልዩነቶችና በባህል ተፅዕኖ ምክንያት በአንድ የማህበረሰብ ክፍል መካከል የሚታይ የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ወይም ዘዴ ነዉ ብለዉታል፡፡አብነት (2007፣ 204-205)ም እንዲሁ ማህበራዊ ዘዬ /ቀበልኛ /በመደብ፣ በትምህርት ደረጃ፣በዕድሜ በጾታ፣በትምህርት ደረጃና በሌሎች ማህበራዊ መለኪያዎቸ ምክንያት በአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎቸ መካከል የሚታይ የአጠቃቀም ልዩነት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ከላይ የተመለከትናቸዉ ሁሉም ገለጻዎች እንዳመለከቱት ማህበራዊ ዘዬ ጋርዮሻዊነትን በሚፈጥሩ የተለያዩ ማህበረ- ታሪካዊ ፣ማህበረ-ፖለቲካዊ ጉዳዮች ምክንያት በተሰባሰቡ የአንድ ቋንቋ ተገልጋዮች መካከል የሚታይ የቋንቋ አጠቃቀም ስልት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

ሐ. አካባቢያዊ ዘዬ

አካባቢያዊ ዘዬ ሌላኛው መጠሪያዉ መልክዓ ምድራዊ ዘዬ ነው፡፡ ይህ ዘዬ በማህበራዊ ሥነልሳን የጥናት መስክ የሚተኮር ሲሆን Gupta (1997፣19) እና የአብነት (2007፣ 203) ገለፃ እንደሚያስረዳው የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ የነበሩ ማኅበረሰቦች በመልክዓ ምድራዊ መራራቅ ምክንያት በመጠኑም እንኳ ቢሆን የቋንቋ አጠቃቀማቸው አንደኛው አካባቢ ከሌላኛው አካባቢ

ለየት ያለና ያፈነገጠ የሚመስል የቋንቋ አጠቃቀም ስልት የሚፈጥሩበትን ሁኔታ የሚመለከት ዘዬ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ባዬ(2000, i) ያሰፈሩት ብያኔም መልክዓ ምድራዊ ዘዬ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች በወንዝና በተራራ ተለይተው ራቅ ባለ ሌላ አካባቢ ከሚኖሩ የዚያው ቋንቋ ተናጋሪዎች በአነጋገር ዘያቸው ተለይተው ቋንቋን ሲጠቀሙ የሚደመጡበት አግባብ አካባቢያዊ ዘዬ ተብሎ ሊጠራ እንደሚችል ያስገነዝባል።

Crutten (1986፣139) ያሰፈሩትን ሀተታ ስንመለከት ደግሞ ህዝቦች በጆግራፊያዊ አቀማመጥ መራራቅ የተነሳ በቋንቋ አጠቃቀማቸው ከብዙ ቁጥር አመልካች ግድፈት፣ ከመስተዋድዶች ግድፈት፣ ከባለቤትና ግስ ትስስር ልዩነት፣ ከአሉታዊ ሀሳቦች አጠቃቀም ወዘተ አኳያ የሚስተዋል የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት አካባቢያዊ ዘዬ በሚል እንደሚታወቅ እንረዳለን፡፧

በአንድ ቋንቋ ተጠቃሚ ማህበረሰቦች መካከል የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት መስተዋሉ አይቀሬና የተለመደ ባህርይ መሆኑን ነው ከፍ ሲል በተከታታይ ከተመለከትናቸው ገለፃዎች መረዳት የሚቻለው ።ክስተቱ የተለመደ ወደፊትም በዚሁ አግባብ ሊቀጥል የሚችል የቋንቋ አጠቃቀም ገጽታ መሆኑን ነው ተከታዩ የ(Crystal 1997, 32) መረጃም የሚያጸናው ።እንደ እርሳቸው ግንዛቤ ከሆነ ግለሰቦች (ቡድኖች) ቋንቋን በመጠቀም ሂደት በየትኛውም ቦታና ጊዜ ቢሆን በንበት፣ በቃላት ፍቺ፣ በሰዋስው፣ በስነ-ምዕላድና በስነ-ድምጸ ልሳን ረገድ የሚያሳዩት የአጠቃቀም ልዩነት እንደሚኖር መታወቅ አለበት።

በአጠቃላይ በአንድ ቋንቋ ተጠቃሚ ማህበረሰቦች መካከል የሚስተዋል የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት በግለሰብ ደረጃም፣ በቤተሰብ ደረጃም፣ አሊያም ሰፋ ሲል ደግሞ በአካባቢ ደረጃም እንደሚከሰት በሊቀስነልሳናት እምነት አይቀሬ ጉዳይ ነዉ ። ይህም ልዩነት በመስኩ ሙያዊ አጠራር መሰረት ዘያዊ ልዩነት /dialectal variation/የሚባለዉ ነዉ።

2.3 የዘዬና የቋንቋ ንጽጽር

ለሙያው ቅርበት ያላቸው ወገኖች ለአብነትም wolfram (2008፣ 88-100) Hudson (1996፣3o-33) በዘዬና በቋንቋ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በአግባቡ ለይቶ ለማሳየት የሚደረገዉ ሙከራ ቀላል እንደማይሆን ያስረዳሉ። ይሁን እንጅ ከሙያው ራቅ ያሉና እንዲሁም በቋንቋ ትምህርት ግንዛቤው የሌላቸው ወገኖች ሁለቱን ጽንሰ ሐሳቦች ማለትም ቋንቋና ዘዬን በተለምዶ በአንድ የመፈረጅና ተመሳሳይ አድርጎ የመውሰድ ሁኔታ ይታይባቸዋል።ተከታዩ ሃሳብ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ስለሆነ ቁም ነገሩን እነሆ! ዘሪሁን

(1992፣94) በቋንቋ እና በዘዬ መካከል ያለዉን ልዩነት በዉል ባለመገንዘብ ምክንያት የአማርኛ ቋንቋን ልዩልዩ ክልላዊ ዘዬዎች የጎጃም አማርኛ ፣የጎንደር አማርኛ፣የወሎ አማርኛ፣ እና የሸዋ አማርኛ በሚል ክልላዊ ዘዬዎቹን ቋንቋ ብሎ የመጥራት ሁኔታ በሀገራችን ማህበረሰብ ዘንድ በጣም የተለመደና ተዘዉታሪ አነጋገር ነዉ ይሉናል።

ይሁን እንጅ ሊቃነስነልሳናት ለአብነትም Wardhaugh(201o ፣25-26) ሁለቱን ጽንሰ ሀሳቦች ማለትም ቋንቋን ዘዬን ለመለየት መታየት የሚገባቸዉ ነጥቦች እንዳሉ ያስረዳሉ።አክለዉም መስፈርት ያሏቸዉን ነጥቦች በመውሰድ "… ቋንቋ የሚባለዉ በመደበኛነት የምንጠቀምበት የቋንቋ ቅርጽ፣ ለትምህርትና ለመገናኛ ብዙሀን ተግባር የምንጠቀመው፣ በመዝገበ ቃላት ውስጥ በዋና ምድብነት የሚያገለግል፣ የማህበረሰባዊ ባህላዊና አልፎአልፎም ፖለቲካዊ ክብር ወይም ዋጋ የተቸረው ነው ።"በሚል ገልጸዉታል ። በሌላ በኩል ዘዬን ሲያብራሩ ደግሞ ዘዬ ህዝቦች ቋንቋን የሚጠቀሙበት ስልት፣ መንገድ ወይም ዘዴ ነው የሚል እንድምታ አዘል ሀተታ Wardaf አቅርበዋል።

እንደ Hudson(1996 ፣43), ገለፃ ዘዬ ሁለት መከሰቻ ዘውጎች አሉት። እነዚህም መደበኛ ዘዬ (ቋንቋ) እና መደበኛ ያልሆነ ዘዬ ናቸው ።ምሁራን ከሚያቀርቡት ሀተታ አንጻር ስንመለከት ሁለቱም በቋንቋ ውስጥ ያሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች/ የማይነጣጠሉ ናቸዉ ሊባሉ ይችላሉ። መደበኛው ዘዬ ምሁራን የሚጠቀሙበትን ፣ጋዜጦች ላይ የሚጻፍበትንና ትምህርት የሚሰጥበትን የሚመለከት ነው ። በአንጻሩ ቀበልኛዉ ዘዬ ደግሞ መደበኛውን ዘዬ ለመግለጽ ከተሞከረባቸው ገለጻዎች የተለየና ቋንቋውን በመደበኛ ሁኔታ ሳይሆን መደበኛ ባልሆነ የአጠቃቀም ስልት በግል (በቡድን) ወይም በአካባቢ አንድን ቋንቋ በልዩ ልዩ መንገዶች የመጠቀምን ሁኔታ እንደሚመለከት wardhaugh (2010, 33)ያሰፈሩት ገለጻ ያመለክታል ።

በሌላ በኩል እንደ ትምህርት ሚኒስቴር መረጃ በቋንቋና ዘዬ መካከል ስላለው መስተጋብር በስፋትና በጥልቀት ለማስረዳት በሚሞከርበት ጊዜ የቋንቋ ተናጋሪው እንደ አንድ ትኩረት የሚቸረው አካል ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል።የሄዉም ተከታዩ ቅንጭብ ሃሳብ እንደሚያስረዳዉ፦

> … አንድ የንግግር አይነት ራሱን የቻለ ቋንቋ ወይም የአንድ ሌላ ቋንቋ ዘዬ መሆኑን በሚያወላዳ መልኩ መናገር ይቻላል። ሁለት የተለያዩ የንግግር አይነት ተናጋሪዎች የየራሳቸዉን የንግግር አይነት በመጠቀም ሀሳባቸዉን መለዋወጥ ከቻሉ ሁለቱ የንግግር አይነቶች የአንድ ቋንቋ

ዘዬዎች ናቸዉ ይባላል፡፡መግባባት ካልቻሉ ደግሞ ሁለቱ የንግግር አይነቶች ሁለት ቋንቋዎች ተደርገዉ ይቆጠራሉ፡፡ ትምህርት ሚኒስቴር (2004፣ 3)፡፡

ከቀረበዉ ጥቅስ እንደምንመለከተዉ ዘዬና ቋንቋን ለመለየት ሁለት የተለያዩ የንግግር አይነት የሚጠቀሙ ወገኖች እርስበርስ መግባባት መቻል አለመቻላቸዉ እንደመስፈርት ሊወሰድ መቻሉን ነዉ፡፡ጉዳዩን በተጨባጭ ለማየት ተከታዩን ጥቅስ እንመልት፦ "… አንድ የጎጃም ገበሬና አንድ የአዲስ አበባ ሰው የየቀያቸውን ዘዬ በመጠቀም መግባባት ይችላሉ፤ በእርግጥ አንዱ ከሚናገረው ውስጥ ሌላው የማያውቃቸው የተወሰኑ ቃላት (አገላለጾች) ሊኖሩ ይችላሉ… እነዚህ አጠቃቀሞች ግን አዲስ አበቤውንም ሆነ ጎጃሜውን ፈጽሞ መግባባት እስከማይችሉበት ደረጃ የሚያደርሱ አይደሉም፤ ምክንያቱም ወሱን ናቸውና" ት/ሚ (2004፣3)፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የአንድ ቋንቋ ተጠቃሚ ማህበረሰቦች በተለያዩ ምክንያቶች የቋንቋ አጠቃቀማቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ ወይም ከቦታ ወደ ቦታ ሲኬድ መጠነኛ ልዩነት ማሳየታቸዉ እሙን ነዉ፡፡ ሆኖም ይህ በአንድ ቋንቋ ተጠቃሚ ማህበረሰቦች መካከል የሚኖረው የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት በጊዜ ብዛትም ሆነ በቦታ ርቀት እየሰፋ በሄደ ቁጥር የልዩነት መጠኑ እየሰፋ ሄዶ ተጠቃሚዎቹ መግባባት ወደማይችልበት ደረጃ ላይ ሊደርስ እንደሚችልም የስነልሳን ሙያተኞች ያረጋገጡት ሀቅ ነው፡፡ ይህንን ክስተትም ዘዬ ወደ ቋንቋ የተሸጋገረበት ሂደት አድርገው ይቆጥሩታል፡፡

በአጠቃላይ ከፍ ሲል በተከታታይ ከቀረቡት ሐሳቦች መገንዘብ እንደሚቻለው ቋንቋና ዘዬ እንደ አንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ሊታዩ የሚችሉ የማይነጣጠሉ የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነቶች ናቸዉ ብሎ መዉሰድ ይቻላል፡፡

2.4 ቋንቋን ማስተማርና መማር ከዘዬ ጋር ያለዉ ግንኙነት

የቋንቋ ትምህርት የሚሰጥባቸዉ የራሱ የሁኑ ዓላማዎች አሉት ፡፡ እንደ ትምህርት ሚኒስቴር (2004 ፣1) ፣ ደበበ (1996፣3)መረጃዎች ተማሪዉ በሚማረዉ የአማርኛ ቋንቋ አራቱን ክሂሎችና ሁለቱን የዕዉቀት ዘርፎች ማለትም የስነ-ጽሁፍንና የስነልሳን ግንዛቤዎችን ለማሳደግ ታልሞ ትምህርቱ በየደረጃዉ ይቀርባል ፡፡ባዩ (2000፣xxi)በበኩላቸዉ ¨ከማንኛዉም የክሂሎት ትምህርት በስተጀርባ ማንኛዉም የቋንቋ ተማሪ ሊገነዘበዉ የሚገባ ጥልቅና ረቂቅ የሆነ ዕዉቀት አለ ይሉናል፤ የሰዋስዉን ዉስብስብነትና አመራማሪነት ለማስረዳት በመሻት፡፡በእርግጥ ከቋንቋ ትምህርት በስተጀርባ ስነልሳንና ስነጽሁፍንም ማሰብ ተገቢነት

አለዉ ፡፡ስነጽሁፍ በዘርፉ የማይናቅ ሚና እንዳለዉ ቢታወቅም ስነልሳን ደግሞ ከዚያም በላይ ቋንቋን ለማወቅ ለመረዳትና ለመተንተን የላቀ ድረሻ አለዉ፡፡ከስነ ልሳን ዘርፎች አንዱ የሆነዉ ማህበራዊ ስነልሳን በቋንቋና ማኅበረሰብ መካከል ያለዉን መስተጋብር ያጠናል፡፡ የስነልሳን ዕዉቀት በአንድ ቋንቋ ዉስጥ የሚታዩ ማህበረሰባዊ የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነቶችን ለመግለጽ ፣ለማብራራት ሚናዉ የጎላ ነዉ Hudson (1996፣20-22):: እንደ Hudson መረጃ ዘዬ ፣ቅላጼ ፣ ሙያነክ ቃላት ፣ ክሪዎል፣ ፒጅን የመሳሰሉት በቋንቋ ትምህርት ዉስጥ ትኩረት የሚደረግባቸዉ ርእሰ ጉዳዮች በማህበራዊ ስነልሳን ዘርፍ ይጠናሉ፡፡

ከፍ ሲል ለመጠቆም እንደ ተሞከረዉ የቋንቋ ትምህርት ከማዳመጥ ከመናገር ከማንበብና ከመጻፍ ክሂሎቸ ጋር የስነጽሁፍና የስነልሳን ዕዉቀቶቸንም ያካትታል፡፡በመሆኑም ዘዬም እንደ አንድ የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት ስልት በቋንቋ ትምህርት ዉስጥ ትኩረት ሊቸረዉ የሚገባ ይዘት ነዉ ፤ምክንያቱም ዘዬን መማር ወይም ማጥናት ለቋንቋ ትምህርት የሚያስገኛቸዉ የራሱ የሆኑ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡ Hazen (2001፤1-3) ያሰፈሩት ሃሳብ እንደሚያስገነዝበዉ ዘዬን ማወቅ ወይም መረዳት ለቋንቋዉ ትምህርት የሚያስገኘዉ ጠቀሜታ አለዉ፡፡ ይሄዉም በሃሳብ ደረጃ ቋንቋ በክልል ወይም በማህበረሰብ ደረጃ እንዴት ሊለያይ እንደሚቸል ተማሪዎች ከተማሩ፣ ካወቁና ከተረዱ ቢያንስ ሁለት ዐበይት የቋንቋ ዕዉቀቶችን ወደ መገንዘብ ደረጃ ይመጣሉ፡፡ ከነዚህም የመጀመሪያዉ ቋንቋ በየጊዜዉ ተለዋዋጭ መሆኑን (የተለዋዋጭነት ባህርይ ያለዉ መሆኑን) መረዳት ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ የቋንቋ አገልግሎት ከማህበረሰብ ማንነት ጋር የተሳሰረ መሆኑን መገንዘብ ነዉ፡፡የቋንቋ ለዉጥ ወይም ብዝሀ- ዘዬነት ቋንቋ በየጊዜዉ ተለዋዋጭ የመሆኑን እዉነታ አመላካቸ ናቸዉ ፡፡በመሆኑም በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦቸ ተመሳሳይ ማህበረሰባዊ ማንነት ያላቸዉ ህዝቦቸ ተመሳሳይ ዘዬዎቸን ይናገራሉ ፤የአንድ ቋንቋ የተለያዩ ልማዶቸን/norms/ይጋራሉ Hazen (2001)::

ከላይ የተመለከትነዉ መረጃ እንደሚያመላክተዉ የቋንቋ ትምህርት ዘዬን ጨምሮ የቋንቋ ስነልሳናዊ ለዉጦቸን ከመማር ዉጭ ሊሆን አይቸልም ባዬ (2000፣xxv) እንደሚያስገነዝቡት የቋንቋ ትምህርት ሲባል ስርአት ብቻ ወይም ክህሎት ብቻ አይደለም፤የአጠቃቀምና የስርአትም ቅንጅት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ እንደባየ ማስረጃ የቋንቋ አጠቃቀም በአብዛኛዉ ማህበራዊና ባህላዊ ሆኖ ስርአቱ ደግሞ አዕምሯዊና ማህበራዊ ነዉ፡፡

ከቀረበዉ ገለጻ የምንረዳዉ የቋንቋ ትምህርት የቋንቋዉን ሳይንሳዊ ትንታኔ ከማህበረሰባዊዉ አዉድ ጋር አስተሳስሮ የሚሄድ መሆኑንና ከዚህም በላይ በማህበረሰብ ዉስጥ ቋንቋ አጠቃቀምን መሰረት ያደረጉ ለዉጦችንም የሚዋጅ መሆኑን ነዉ ፡፡

2.5. ሙያዊ ብቃት

አንድን ሙያን የሚጠይቅ ተግባር በሚፈለገውና በሚጠበቀው መንገድ በብቃት ለማከናወን በመስኩ ሰልጥኖ ብቁ ሙያተኛ ሆኖ የመገኘቱ ሁኔታ አጠያያቂ ጉዳይ ሊሆን አይችልም፡፡ መማር ማስተማርንም በስኬት ለመምራት ሲታሰብ የሙያው ስነምግባር ከሚፈልጋቸው ቅድመ-ሁኔታዎች መካከል በዘርፉ የሰለጠኑ ብቁ ሙያተኞች የመኖራቸው ጉዳይ አንዱ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡በመሆኑም የቋንቋ መምህርም የቋንቋ ትምህርትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ይችል ዘንድ የተሰለፈበት ሙያ የሚፈልጋቸዉን የሙያ ብቃቶች አሟልቶ መገኘት ይኖርበታል፡፡ ከቋንቋ መምህሩ የሚጠበቅን ሙያዊ ብቃት አስመልክቶ Lado (1964፣ 8)እንዳሰፈሩት ከሆነ የቋንቋ መምህራን ቢያንስ ብጤዎቻቸዉ በደረሱበት ደረጃ ልክ ሰልጥነዉ እና ሙያዊ ብቃት አካብተዉ መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡ እኒህ ምሁር አክለዉም ከምሁራን በሚጠበቅ የቋንቋ አጠቃቀም ደረጃ ልክ መምህራን ንግግራቸዉን ከሁኔታዎችና ከተግባቦቶች ጋር ማላመድ (ማቀናጀት) የሚጠበቅባቸዉ መሆኑንም በአጽንኦት አስገንዝበዋል ፡፡በሌላ በኩል የቋንቋ መምህራን ቋንቋን በማስተማር መማር ሂደት ዉስጥ ግንዛቤ ሊኖራቸዉና ትኩረት ሊሰጡባቸዉ ይገባል ተብለዉ ከተዘረዘሩት ነጥቦች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡Takle(2000፣250)እና Lado(1964፣8) ያቀረቧቸዉ ሀተታዎች እንድምታ እንደሚያስገነዝበዉ ምንም እንኳዋ አንድ ቋንቋ ነጠላ ተግባቦታዊ፣ ስልት ለማከናወን ቢያስችልም መምህሩ የቋንቋዉን የተለያዩ ዘዬዎች፣እና እንዲሁም በዘዬዎች መካከል ሊኖር ስለሚችለዉ በጎ ያልሆነ ዉድድር /dialectal prejudice/፣የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነቶቸ /linguistic variations/ ስለመደበኛ ቋንቋ /Languge Standaredaization/ በዉል መገንዘብ ይጠበቅበታል፡፡

Folk (1978 ፣407)፣ Holmes (1992፣365)፣ Lado (1964፣8) ያሰፈሩት ማብራሪያ የሚያመለክተዉ ደግሞ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ጽንሰ ሐሳቦች ዘርዘር ባለ ሁኔታ ሲታዩ እንደሚከተለው ሊብራሩ ወይም ሊገለጹ የሚችሉ ናቸው፡፡፡

ሀ. ስነልሳናዊ ልዩነት /Lingustic variation/

በቋንቋ አጠቃቀም ሂደት ግለሰቦችም ይሁኑ በድኖች የሚያሳዩዋቸው የአጠቃቀም ልዩነቶች እንደሚኖሩ ይታመናል፡፡እነዚህ ልዩነቶች ከማህበራዊ ስነልሳን ሳይንስ እይታ አንጻር አይቀሬና ተፈጥሯዊ ናቸዉ፡፡ እነዚህ በየትኛዉም ቋንቋ ዉስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ የአጠቃቀም ልዩነቶቹ በተለያዩ ምክንያቶች የሚመጡ ናቸው (Holmes, 2001፣ 263-269) እንዳሰፈሩት ከማህበራዊ ደረጃ፣ ከፆታ፣ ከዕድሜ ከዘር ፣ በማልክዓምድራዊ አቀማመጥ፣ ከሥራ (ሙያ)፣ እና ከኢኮኖሚ ደረጃ ልዩነቶች የተነሳ የሚከሰቱ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በስነልሳን ረገድ የሚታይ ልዩነት ሲነሳ መዘንጋት የሌለበት ሌላው ነጥብ የልዩነቶቹ አይነት ነው፡፡ Lado (1964, 17) እና Folk (1978) እንዱሁም (Hudson 1980) ለማስገንዘብ እንደሞከሩት የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት በግለሰብ ደረጃ፣ በአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች መካከል ወይም የተለያዩ ቋንቋዎችን በሚናገሩ ማኅበረሰቦች መካከል መታየት የሚችል ነው፡፡

ለ. ለዘዬ በጎ ያልሆነ አመለካከት/dialectal prejudice/

ይህ ክስተት በተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች መካከል የራስን ቋንቋ ወይም የራስን ዘዬ ከፍ አድርጎ የማየትና የሌሎችን ደግሞ ዝቅ አድርጎ የማየት፣ መቻቻልን በመዘንጋት ቋንቋን መሰረት ያደረገ ጥላቻ ማሳየት የተለመደ ነገር እንደሆነ አስገንዝበዋል፡፡አክለዉም የቋንቋ ሙያተኞች የቋንቋዎችን እኩልነት ሳይንሳዊ እውነታዎችን በተጠቃሚዎች አእምሮ በማስረጽ ችግሩን መቅረፍ ስለሚቻል ለዚሁ ተግባር መትጋት እንደሚገባቸው (folk 1978, (Holmes 1992) (Lado (1964) በውል ያስገነዝባሉ፡፡

ሐ. መደበኛነት፡-

በዓለማችን የሰዉ ልጅ የሚገለገልባቸዉ አያሌ ቋንቋዎች ይገኛሉ ፡፡እነዚህ ልዩልዩ ቋንቋዎች እንደየተጠቃሚዉ ማህበረሰብ ባህል ፣አስተሳሰብና የአኗኗር ዘይቤ የሚለያዩባቸዉ ሁኔታዎች የመኖራቸዉን ያህል ስነልሳናዊ ባህርያቸዉ ደግሞ አንድ ያደርጋቸዋል ፡፡ለምሳሌ ሁሉም ቋንቋዎች በስነልሳናዊ ባህርያቸዉ የአጠቃቀም ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡ ዘዬ ከልዩነቶቹ መካከል አንዱ ነዉ፡፡የሙያዉ ጠበብቶች ዘዬን መደበኛ እና መደበኛ ያልሆነ በሚል ይፈርጁታል፡፡ለምሳሌ Wardaugh (2010፣ 32) መደበኛዉን ዘዬ ከስነልሳናዊ እሳቤዉም በላይ ማህበራዊ ፣ ባህላዊ አልፎአልፎም ፖለቲካዊ ዋጋ ያለዉ ፣ለትምህርት ለመገናኛ ብዙሀን፣ለቢሮ ተግባራት ፣ለፍትህ አገልገሎት ወዘተ ተመራጭነት ያለዉ ፣እንዲሁም ሰፊ ማህበረሰባዊ ድጋፍ የተቸረዉና ትክክለኛ ተብሎ የሚታመን እንደሆነ Hudson(1996

21)ያቀረቡት ዝርዝር ሃሳብ ያስረዳል፡፡ አንድ ዘዬ መደበኛ ሊሆን የሚችለዉ በታሪክ አጋጣሚ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡Zelalm (2007፣449)፣Milroy (1999፣76)፣ Wardaugh(1992 ፣174)እንዳስፈሩት ሃሰብ ከሆነ በአንድ አጋጣሚ ዘዬ ወደመደበኛ ዘዬነት ሊቀየር ይችላል ፤ይህም ሲባል በተጠቃሚዉ በአብዛኛዉ ማህበረሰብ ተቀባይነት ወዳለዉ" ኮድ " ተለወጠ ማለት ነዉ፡፡

ከላይ በተከታታይ ከቀረቡት ሶስት ንኡሳን ርእሶች መገንዘብ የሚቻለዉ ቋንቋን በማስተማር ሂደት መምህራን ግንዛቤያ ቸዉን አሳድገዉ ለመገኘት ሙያቸዉ ከሚፈልገዉ ቋንቋ ነክ ጉዳዮች መካከል አንዱ ስነልሳናዊ ልዩነት /Lingustic Variation/ መሆኑን ነዉ ፡፡

2.6. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎቸ ላይ የተጠኑ ቀደምት ስራዎቸን በማፈላለግ ለመቃኘት በተደረገዉ ሙከራ መሰረት የተወሰኑ ጥናቶችን ማግኘት ተችሏል፡፡በመሆኑም እነዚህን ስራዎች በቀረቡበት የጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት በማደራጀት እያንዳንዱ ጥናት ከዚህ ስራ ጋር ያለዉን ተመሳስሎና ልዩነት በመንቀስ ለዚህ ስራ ግብአት የሚሆኑ መረጃዎቸን ለማግኘት ጥረት ተደርጓል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የተፈተሸዉ ጥናት ደግሞ Zelalem (2007) "The Amharic Dialects Revisted"በሚል ርእስ ያቀረቡት ዳሰሳዊ ጥናት ነዉ፡፡ የጥናቱ አቅራቢ በዚህ ስራቸዉ በአማርኛ ቋንቋ ዉስጥ የሚገኙ በዉል የሚታወቁ የዘዬ አይነቶቸን እንደገና በመዳሰስ ዝርዝር ጉዳዮችን ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ይኄዉም በአማርኛ ቋንቋ ዘየዎችን በተመለከተ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥናት የተካሄደዉ በ1955 ዓ.ም በአብርሀም ደመወዝ መሆኑን ለመጠቆም ሞክረዋል ፡፡በዚህ የመጀመሪያ ጥናትም አብርሀም ያቀረቡት ስለጎንደር ዘዬ ሲሆን በጥናቱ የጎንደር አካባቢ ዘዬን ከመደበኛዉ የአዲስ አበባ ዘዬ ጋር በማነጻጸር ልዩነታቸዉ ለማሳየት መሞከሩን የዘላለም ሀተታ አመላክቷል ፡፡በማሳያነት ከቀረቡ ምሳሌዎቸ መካከልም ተከታዮቹ ይገኙበታል፡፡

የአዲስ አበባ ዘዬ	**ጎንደርኛ ዘዬ**
ቤቱ -ሂድ-ኦ-አል	ቤቱ-ን-ሂድ-ኦ-አል
ከክፉ አዳነን	ከክፉ አዳነነ

ምጣድ	ምኅኅ
ልበላ ነዉ	ልበላ ነኝ
ቃሪያ	ቄጦ
ወጣ	ተሰቀለ

ዘላለም የአብርሀምን ጥናት ሲዳስሱ ያቀረቡት ይህ ከፍ ሲል የቀረበዉ ማሳያ የጎንደር ቀበልኛ የቋንቋ አጠቃቀም ከአዲስ አበባዉ መደበኛ ዘዬ አጠቃቀም ጋር ሲነጻጸር የድምጽ ፣የምእላድና የፍች ለዉጥ እንደሚታይበት አመላክቷል፡፡ይሄዉም ከፍቺ አኳያ ሲታይ በመደበኛዉ ዘዬ "ምጣድ" የተሰኘዉ ቁስ በጎንደር ቀበልኛ አጠቃቀም " ምኅኅ "በሚል ተቀይሯል፡፡በተመሳሳይ ሁኔታ" ወጣ "የሚለዉ ቃል "ተሰቀለ" ወደሚለዉ የቀበልኛ አነጋገር /ዘዬ/ ተለዉጦ ይታያል ፡፡ የቃሪያ መደበኛ ፍችም እንዲሁ" ቄጦ" በሚል ቀበልኛ ቃል ተቀይሯል፡፡ ከዚህ የምናስተዉለዉ በመደበኛዉ የአዲስ አበባ ዘዬ እና መደበኛ ባልሆነዉ የወሎ ዘዬ መካከል በቃላት ፍች ደረጃ ልዩነት መኖሩን ነዉ ፡፡በሌላ በኩል በምእላድ ደረጃም በመደበኛዉ አጠቃቀምና መደበኛ ባልሆነዉ የዘዬ አጠቃቀም ልነቶች ተስተዉለዋል፡፡በምርምር ስራዉ ከቀረቡት ምሳሌዎቸ እንደምንመለከተዉ " ወደቤቱ ሄደ " የሚለዉ መደበኛና ተለምዷዊዉ የመስተወድድ አጠቃቀም በቀበልኛዉ አጠቃቀም "ቤቱን ሄደ፡፡" በሚል አገላለጸ" ወደ"የሚለዉን መስተዋድድ "ን" ተከታዉ ገብታለች፡ ፡በመሆኑም በመደበኛዉ ዘዬ አጠቃቀም የተሳቢ አመልካቸነት ሙያ የነበራት ምላድ "ን" በጎንደርኛዉ ቀበልኛ አጠቃቀም የመሥተዋድድነት ተገባርን ስትወጣ ትታያለቸ፡፡ እንዲሁም የሶስተኛ መደብ ብዙ ቁጥር አመልካቸ ተሳቢን ታመለክት የነበረቸዉ መእላድ" ን " በጎንደርኛዉ ቀበልኛ ዘዬ ሳድሳዊ ባህርይዋን ለዉጣ ራሱን የሚደግም ግእዝ ቅርጽን የተላበሰ ምእላድ ሆናለቸ፡፡

ዘላለም በጥናታቸዉ እንዳቀረቡት መረጃ ከሆነ የአማርኛ ቋንቋ ዘዬዎችን በተመለከተ ጥናት የተካሄደዉ ከ14 ዓመት ቆይታ በኋላ (በ1969) ዓ.ም. ነበረ፡፡ይሄዉም አምሳሉ አክሊሉን ጨምሮ ፍስሃ ሲሳይ ፣ጌታቸዉ ሐይሌ ፣ሀብተማርያም ማርቆስ ፣ሀይሉ ፋላስ እና ሰይፉ መታፈሪያ በተባሉ ምሁራን አማካኝነት እንደነበረ ተጠቅሷል፡፡በነኝህ ምሁራን አማካኝነት የተጠናዉ ጥናት በ11973 ዓ .ም ዉጤቱ ይፋ ተደርጎ ከተገኙ ቁምነገሮቸ መካከል የአዲስ አበባዉ አማርኛ መደበኛዉ ዘዬ ተደርጎ እንዲታይ ያስቻሉትን አበይት ነጥቦቸ የሚያስረዳዉ ቁም ነገር እንደሚገኝበት Zlalme በጥናታቸዉ ገልጸዉታል፡፡እኚህ ምሁር አክለዉም አዲስ አበባ በ(1884) ዓ.ም የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ሆና በመመረጧ የተለያዩ የአማርኛ ዘየዎቸን

የሚናገሩ ማህበረሰቦች ወደአዲስ አበባ መሳባቸዉና አዲስ አበባ የሚነገረዉ አማርኛ ቀስበቀስ እየተስፋፋ በሚሄደዉ የህዝብ ቁጥር ልክ መነገር መጀመሩና ለትምህርትም ተግባር መዋሉ መደበኛ ዘዬ ተደርጎ እንዲወሰድ ያስቻለዉ መሆኑን ገልጸዋል ።

በሌላ በኩል በአማርኛ ቋንቋ ዉስጥ ከአዲስ አበባዉ ዘዬ ጎን ለጎን በቋንቋዉ ተጠቃሚ ህዝቦች መካከል ግልጋሎት ላይ የዋሉት የጎጃም የጎንደር የወሎ አና የሸዋ ዘዬዎች መሆናቸዉን በመጥቀስ ዘዬዎቹ የሚያሳዩትን ልዩነት ለማሳየት መሞከር Zelalm (2007) ያቀረቡት ስራ ዋና ትኩረት ነበር። ለአብነትም" እዚህ " የሚለዉ መደበኛዉ የአዲስ አበባዉ ዘዬ በወሎዉ አጠቃቀም(እይህ /እዝህ/ በሚል የተወሰኑ የድምፅ ለዉጦችን አድርጎ /እዝዝኢህ/ የሚለው እዝዝእህ (እይይህእ) ተለውጦ መቅረብ መቻሉ ተጠቅሷል።ከምሳሌዉም የፊት አናባቢ የነበረቸዉ" ኢ"ወደ ሳድስ አናባቢ "እ" እንዲሁም በመደበኛዉ ዘዬ ሹልክል፣ነዛሪ፣የድድ ድምጽ የነበረቸዉ "ዚ" ወደ ከፊል አናባቢ፣ ነዛሪ ፣የላንቃ "ይ" ድምጽ (የድድ ድምጽ ከፊት አናባቢ በመጎራበትዋ ምክንያት ወደላንቃ ድምጽ) ተቀይራለች።

በሌላኛዉ ምሳሌም እንዲሁ በአዲስ አበባዉ መደበኛ ዘዬ /ድኽግግ/ የሚለዉ ቃል/ ድኤግግ/ በሚል የወሎ ቀበልኛ ቃል ተቀይሮ መነገሩን ለማሳየት ተሞክሯል። በምሳሌዎቹ የምንመለከተዉ በቀረቡት ሁለቱ የዘዬ አይነቶቸ መካከል የድምጽ ለዉጥ መኖሩን ነዉ።

Zelalem (2007) ሀብተማርያም እና ሌሎችን በዋቢነት በመጥቀስ የጎጃም ዘዬን ጥቂት ገጽታዎች እንደሚከተለዉ ለመዳሰስ ሞክረዋል። በጎጃም ዘዬ (" ከ" ወደ " ተ") የሚቀየርበት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ (ከዚህም--------- ተዚህም) ፣ ከሄድኩበት ------ተሄድኩበት ፣ (ከመጣ---------ተመጣ) የሚሉት ይገኙበታል። እንዲሁም በምስራቅ ጎጃም አካባቢ (" ከ" በ " ጨ") ፤ ("ገ" ደግሞ በ "ጀ") ተቀይረዉ የሚቀርቡበት ሁኔታ መኖሩን ገብሬ(1990)ን በዋቢነት ጠቅሰዉ Zelalem አስገንዝበዋል።ተከታዮቹ ምሳሌዎቸ የዚህ ማሳያዎቸ ናቸዉ።

/ምኽክኢንኣ / ⟹/ምኽችችኢንኣ/ ፣ /ክኢልአ/ ⟹/ቸኢልአ/፣ /ግኤትኣ / ⟹ጅኤትኣ /፣ /ግኤትኦቸ / /ጅኤትኦች/ የሚሉት ይገኙበታል።በመጨረሻ Zelalem አምስቱንም የአማርኛ ዘዬዎች ያነጻጸሩበትን ማሳያ በማሳረጊያነት እንመልከት።

ተናባቢ ድምጾቸ ከሚያሳዩት ቦታ ቅየራ አንጻር ለዉጦቸ እንደሚከተለዉ ይታያሉ፦

አ/አበባ	ጎጃም	ጎንደር	ሸዋ	ወሎ
ሰጠመ	ሰመጠ	ሰመጠ	ሰጠመ	ሰመጠ
ድጋፍ	ግዳፍ	ድጋፍ	ድጋፍ	ግዳፍ
ማክሰኞ	ማስከኞ	ማስከኞ	ማክሰኞ	ማስከኞ

በምሳሌ አንድ ላይ የአዲስ አበባ ዘዬ እና የሸዋ ዘዬዎች የሚያሳዩት የተናባቢዎች ቦታ ቅየራ ተመሳሳይ ሲሆን በጎጃም በጎንደር እና በወሎ ዘዬዎች መካከልም ቀደም ከገለጽነዉ ከአዲስ አበባዉና ከሸዋዉ ዘዬ በተለዬ ተመሳስሎ ይታይባቸዋል፡፡በአምስቱ የአማርኛ ዘየዎች መካከል የሚታይ የቃላት አጠቃቀም ልዩነት ደግሞ የ Getahun (1983) መረጃ ዋቢ በማድረግ Zelalem እንደሚከተለዉ አስፍረዉታል፡፡

አ/አበባ	ጎጀም	ጎንደር	ሸዋ	ወሎ
ቃሪያ	ቁጦ	ቁጦ	ቃሪያ	ቁጦ
ጭራ	ጅራት	ጅራት	ጭራ	ጭራ
ቢራቢሮ	ቢራቢሮ	ቢራቢሮ	ቢራቢሮ	አምባቡራ
እንዴ!	ኧረ!	ኧረ !	እንዴ!	ኧረ!
ልጅ	ጉብል	ኩታራ	ልጅ	ልጅ
ክፍ	ብስ	ብስ	ክፍ	ክፍ
አስብ	አስብ	እሰብ	አስብ	አስብ
መቀስ	መቁረጭት	መቁረጭት	መቀስ	መቁረጭት
ወር አበባ	አደፍ/ደም	ደም	ወርአበባ	አደፍ/ደም
አክምባሎ	ሙግድ	ሙግድ	አክምባሎ	ሙግድ
ጨዉ	አሻቦ	አሻቦ	ጨዉ	አሻቦ

ከፍ ሲል ከቀረበዉ መረጃ ለመመልከት እንደምንችለዉ የአማርኛ ቋንቋ ዘያዊ ልዩነቶችን ስንመለከት በስፋት የሚስተዋለዉ ልዩነታቸዉ በቃላት ትርጉም ላይ ነዉ ማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም በስነድምጽ ደረጃም እንዲሁ ልዩነቶች ይታያሉ ፡፡በሌላ በኩል ደግሞ በምእላድና በሰዋስዉ ደረጃ የሚታዩ ልዩነቶችንም እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ በጎንደር እና በጎጃም ዘዬዎች መካከል /ክኧንንኧግግርኧኝ/--ትኧንንግኧርኧኝ/ ፣ (ክኧዘዘኢህ /----/ትኧዘዘኢህ/) በመሳሰሉት አገላለጾች /ክ --ት/ የመቀየሩ ሁኔታን የማመላከት ስነድምፃዊ ባህሪ በወሎ እና በጎጃም

ዘዬዎች መካከል የሚስተዋል በሌሎች ዘየዎች ግን የማይታይ ባህሪ መሆኑን ዘላለም ባቀረቡት ዳሰሳዊ ጥናት ገልጸዋል።

የዘላለም ጥናትና ይህ ጥናት የሚመሳሰሉት ሁለቱም ስራዎች የአማርኛ ቋንቋ ዘዬዎችን በተመለከተ ገለጻ ወይም ማብራሪያ በማካተታቸዉ ሲሆን ፤ ልዩነታቸዉ ደግሞ ይህ ጥናት የአማርኛ ዘዬዎች ቋንቋዉን በመማር ማስተማር ሂደት የሚኖራቸዉን ተጽእኖ በመመርመር ላይ ያተኮረ በመሆኑና እንዲሁም መምህራንና ተማሪዎች ስለዘዬ ያላቸዉን ግንዘቤ በመፈተሽ ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ የትኩረት አቅጣጫ ቸዉ ያለያያቸዋል።

በሁለተኛ ደረጃ የተቃኘዉ ጥናት ደግሞ /Wondimu (2015)" ዘዬዎች በትምህርት ዘርፍ ያላቸዉ ጠቀሜታና ዘዬ በተማሪዎች መማር ዉጤታማነት ላይ የሚኖረዉ ተጽእኖ " በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት ነዉ። የወንድሙ ስራና ይህ ጥናት ተመሳስሎም ልዩነትም አላቸዉ። ተመሳስሏቸዉን ስንመለከት ሁለቱም ጥናቶች ዘዬ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚኖረዉን ተጽእኖ በመፈተሽ ላይ ማተኮራቸዉ ፣እንዲሁም ዘዬን የተመለከተ ዝርዝር መረጃን ለመቅረብ በመመሞከራቸዉ ይመሳሰላሉ ።ከዚህ ባሻገር የወንድሙ ስራ በጥናቱ የመግቢያ ክፍል በስፋት እንደተብራራዉ ዘዬን ጨምሮ በተለያዩ ተማሪዎች በሚናገሯቸዉ የቋንቋ ስነልሳናዊ ልዩነቶች ትምህርት እንዲቀርብ ቢደረግ ተማሪዎች ሙሉ አቅማቸዉን ተጠቀመዉ እንዲማሩ በር ስለሚከፍትላቸዉ በትምህርታቸዉ የጠለቀ ዕዉቀት ሊጨብጡ እንደሚችሉ በዝርዝር ስለሚያብራራ ፣ እንዲሁም ዘዬ አጠቃላይ በትምህርት መስክ ሊያስገኝ የሚችለዉን ጠቀሜታ የሚዳስስ በመሆኑ ዘዬን ከአንድ ቋንቋ /አማርኛ/አንጻር ብቻ ከሚመለከተዉ ከዚህ ጥናት ጋር ይለያያል።በተጨማሪም ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ ዘያዊ ልዩነቶቹ ቋንቋዉን በማስተማር መማር ሂደት ዉስጥ የሚኖራቸዉን ተጽዕኖ የሚፈትሽ በመሆኑ፣እንዲሁም መምህራንና ተማሪዎች ስለ ዘዬ ያላቸዉ ግንዛቤ አማርኛን በማስተማር መማር ሂደት የሚኖረዉን ተጽዕኖ የሚዳስስ በመሆኑ ከወንድሙ ጥናት ይለያል።

በሶስተኛ ደረጃ የተቃኘዉ ስራ ደግሞ ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ሲሆን ይህ ስራ "Docmentation &Describtion Of Amharic Dialects" በሚል ርእስ Menegstu (2011) ያቀረቡት ጥናት ነዉ። የመንግስቱ ጥናት ከዚህ ስራ ጋር የሚመሳሰለዉ በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎች ትኩረት በማድረግ በዘዬ ምንነት፣ በዘዬና በቋንቋ ግንኙነትና እንዲሁም ልዩነት ላይ ሰፋ ያለ መረጃ አካቶ በመገኘቱ ነዉ። ሁለቱ ጥናቶች የሚለያዩባቸዉን ነጥቦች ስንመለከት ደግሞ የመንግስቱ ስራ የአማርኛ ቀበልኛ ንግግሮች በመደበኛዉ ዘዬ እየተዋጡ በመሄድ ላይ በመሆናቸዉ ጨርሰዉ ከመጥፋታቸዉ በፊት

ተሰንደዉ በመረጃነት ሊቀመጡ እንደሚገባ በአጽንኦት ያስረዳል፡፡ በተጨማሪም የመንግስቱ ስራ የአማርኛ ቋንቋ ዘዬዎች ከቴክኖሎጅ መስፋፋት ጋር እንዲሁም ከዘመናዊነት መስፋፋት ጋር ተያይዞ በመጣ ለዉጥ ምክንያት ትኩረት ተነፍገዉ በመጥፋት ላይ በመሆናቸዉ ልንታደጋቸዉ ይገባል በሚል ነጥብ ላይ ያትታል፡፡ በአንጻሩ ይህ ጥናት ጥኩረት ያደረገዉ የአማርኛ ቋንቋ ዘዬዎቹና መምህራንና ተማሪዎች ስለዘዬ ያላቸዉ ግንዛቤ ቋንቋዉን በመማር ማስተማር ሂደት የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ በመመርመር ያተኮረ በመሆኑ የትኩረት አቅጣጫ ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በቅደም ተከተል የተመለከትናቸዉ ጥናቶች የአማርኛ ዘዬዎችን ምንነት ፣ልዩነት ፣ የልዩነቶቹን መገለጫዎች በማሳየት ላይ ያተኮሩ በመሆናቸዉ ያካተቱት መረጃ ከዚህ ጥናት መረጃ ጋር የሚመሳሰልበት ሁኔታ ቢኖርም ይህ ስራ የአማርኛ ቋንቋ ዘዬዎቹ ቋንቋዉን ለማስተማር በሚያሳድሩት ተጽዕኖ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ደግሞ ከፍ ሲል ከተዘረዘሩት ጥናቶች ይለያል፡፡

ምዕራፍ ሶስት

የአጠናን ዘዴ

3.1. የጥናቱ ዘዴ

የተሰበሰቡትን መረጃዎች አደራጅቶ ለመግለጽ (ለመተንተን) አይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴዎችን በጥናቱ ለመጠቀም ተሞክሯል፡፡ ይኸውም በጽሁፍ መጠይቅ አማካኝት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በቁጥርና በመቶኛ ስሌት ለመተንተን ሲባል መጠናዊ የምርምር ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቁጥርና በመቶኛ የተቀመጡ መረጃዎችና ከቃል መጠይቅና ከቡድን ውይይት እንዲሁም ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች ገለፃ ስለሚያስፈልጋቸው አይነታዊ የምርምር ስልት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

3.2. የጥናቱ መረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት የተካሄደው በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ በ2010 ዓ.ም. በመማር ማስተማር ላይ በሚገኙ የ7ኛ፣ የ9ኛ እና የ11ኛ ክፍል ተማሪዎችና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ሲሆን መረጃ በመስጠት የተሳተፉትም መምህራንና ተማሪዎች ናቸው፡፡

3.3. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

3.3.1.የትምህርት ቤት ናሙና

ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ ታስቦ የተመረጡት አራት ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ አራቱም በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 እና 12 ውስጥ የሚገኙ ተጎራባች ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ የተመረጡትም በአመቺ ንሞና ስልት ነው፡፡ ይኸውም ሶስቱ ትምህርት ቤቶች አጥኚው መደበኛ ስራውን ከሚያካሂድበት የሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት አካባቢ የሚገኙ በመሆናቸውና በነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንም የቋንቋዉን ልዩልዩ ዘዬዎች ተናጋሪ መሆናቸውን አጥኚው በተለያዩ አጋጣሚዎች (ለአብነትም በስብሰባ፣ በስልጠና፣ በልምድ ልዉዉጥ … ግንኙነቶች ለመረዳት ችሏል፡፡) ስለሆነም ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ለማግኘት ያስችላሉ በሚል ዓላማ አራቱን ትምህርት ቤቶች በተጠኚነት ለይቷል፡፡

3.3.2. የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ጥናቱ ከሚመለከታቸው አራት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተጠኚነት የተለዩት የክፍል ደረጃዎች 7ና፣ 9ኛ እና 11ኛ ክፍል ብቻ ናቸው፡፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ከሶስቱ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተሻለ መረጃ ይሰጣሉ በሚል የተመረጡት የሁለተኛ እርከን የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ነበሩ፡፤ ይሁን እንጅ የጥናቱ መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የዓመቱን የትምህርት ጊዜ አጠናቀው ክልላዊ ፈተናውን ለመውሰድ በዝግጅት ላይ የነበሩ በመሆኑ መረጃ ለመስጠት አልቻሉም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት የ10ኛ እና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችም የዓመቱን የትምህርት ዘመን ይህ መረጃ ከመሰብሰቡ አስቀድሞ በማጠናቀቃቸው በመረጃ ሰጪነት አልተካተቱም፡፡ ስለሆነም መረጃ በመስጠት የተሳተፉት ቀደም ሲል እንደተገለጸው የ7ኛ፣ የ9ኛ እና የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡

3.3.3.የመምህራን ንሞና

የመምህራን ተጠኚዎችን በተመለከተ የአራቱም ትምህርት ቤቶች ሁሉም የአማርኛ መምህራን በመረጃ ሰጪነት ተሳትፈዋል፡፤ ይህም የሆነበት ምክንያት ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም የሚሊኒየም ትምህርት ቤት ዘጠኝ መምህራን፣ የፊልጶስ ትምህርት ቤት አምስት መምህራን፣ የዕውቀት ወገኔ ትምህርት ቤት ስድስት መምህራንና የብስራት ትምህርት ቤት አምስት መምህራን በጠቅላላ ሃያ አምስት መምህራን በጥናቱ ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡

3.3.4.የተማሪ ንሞና

ለዚህ ጥናት በመረጃ ሰጪነት የተለዩ ተማሪዎች ከአራት ትቤቶች የተመረጡ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ከእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ማለትም (ከ7ኛ፣ ከ9ኛ፣ ከ11ኛ) የክፍል ደረጃዎች የጠቅላላ ተማሪዎችን ቁጥር ሃያ በመቶ ለመውሰድ ተሞክሯል፡፡ ዝርዝር የናሙና አወሳሰዱን ከተከታዩ ሰንጠረዥ ይመለከቷል፡፡

ተ/ቁ	የት/ቤቶች ዝርዝር	የክ/ደረጃ	የክፍሉ ተማሪ ብዛት	ሃያበመቶ ስሌት
1	ዕውቀት ወገኔ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት	7ኛ ክፍል	367	73.4%
2	ፊልጶስ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት	7ኛ ክፍል	222	44.4%
3	ብስራት የመጀ/ደ/ት/ቤት	7ኛ ክፍል	401	80.2%
4	ሚሊኒየም፪ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት	9ኛ	360	72%
		11ኛ ክፍል	240	48%
	ጠቅላላ የተማሪዎች ድምር		1590	318%

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መመልከት እንደሚቻለው የተማሪ ተጠኚዎች ከጠቅላላ አካላዩ 1590 ተማሪዎች መካከል በተራ ዕጣ ንሞና ዘዴ በየክፍሉ ከተመደቡ ተማሪዎች 20%ቱን በመለየት ከጠቅላላ አካላዩ 1590ዎች መካከል 318 ተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡

3.3.5. የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት ወሳኝ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብና የመረጃዉን አስተማማኝነትም ለማሳደግ ሲባል አራት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ስራ ላይ ውለዋል፡፤ እነዚህም የጽሁፍ መጠይቅ፣ የቃል መጠይቅ፣ የሰነድ ፍተሻና የቡድን ውይይት ናቸዉ ፡፡ በአጠቃላይ የጽሁፍ መጠይቅ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ያገለገለ ሲሆን የቃል መጠይቅ ሰነድ ፍተሻና የቡድን ውይይት ደግሞ በአጋዥነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

3.3.5.1. የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ በጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎችና መምህራን የቀረበ ሲሆን በመጀመሪያ የመጠይቁን ትክክለኛነት በአማካሪ መምህር ለማስገምገም ተሞክሯል፡፡ ትክክለኛነቱ ከታመነበት በኋላም በተጠኚዎች እንዲሞላ ተደርጓል፡፡ ይኸውም ለዚህ ጥናት በተለዩ አራቱም ትምህርት ቤቶች አማርኛን ለሚያስተምሩ ሁሉም 25(100%) መምህራን) ለእያንዳንዳቸው 16 ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ሁሉም በትክክል ሞልተው መልሰዋል፡፡ ከአስራ ስድስቱ ጥያቄዎች መካከከል ሶስቱ ክፍት ጥያቄዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ አስራ ሶስቱ ደግሞ ዝግ ጥያቄዎች ናቸዉ፡፡፡በሌላ በኩል ለተማሪዎች የቀረቡ

የጽሁፍ መጠይቆችን በተመለከተ ደግሞ ከአጠቃላይ አከላይ ናሙና 1590 የአራት ትምህርት ቤት ተማሪዎች መካከል ለዚህ ጥናት በናሙና ለተለዩ 318 ተማሪዎች መጠይቁ ደርሷቸው እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡የመጠይቁን ይዘት በተመለከተ ደግሞ ስምንት ዝግና ሶስት ክፍት ጥያቄዎች በጠቅላላው እያንዳንዳቸው አስራ አንድ አንስራ አንድ ጥያቄዎችን እንዲሞሉ ከተደረጉ 318 ተማሪዎች መካከል በትክክል ሞልተው የመለሱ 270 ተማሪዎች ብቻ ናቸው፡፡ 27 ተማሪዎች ሙሉ ለሙሉ መጠይቁን ሳይመልሱ ቀርተዋል፡፡ እንዲሁም 21 ተማሪዎች ደግሞ ያሰፈሩት መረጃ ትክክለኛ ሆኖ ባለመገኘቱ ከጥናቱ ውጪ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

3.3.5.2. የቃል መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቁን ከሞሉ ሃያ አምስት መምህራን መካከል ስድስት መምህራን ተመርጠዉ ለእያንዳንዳቸዉ አስር አስር ጥያቄዎች ቀርበዉላቸዉ ምላሽ ሰጥተዉባቸዋል ፡፡እነዚህ መምህራን ተለይተዉ በቃለ መጠይቁ እንዲሳተፉ የተደረገበት ምክንያት አጥኚዉ ከተማሪዎችና ከመምህራን ባገኘዉ ጥቆማ መሰረት የአማርኛ ቀበልኛ ዘዬዎቻቸዉን በተደጋጋሚ ሲጠቀሙባቸዉ የሚደመጡ መሆናቸዉን በማወቁ ተጨማሪ የተሻለ መረጃ ለማግኘት በመፈለጉ ነዉ፡፡ በተጨማሪም በጽሁፍ መጠይቁ መምህራን ያቀረቡትን ምላሽ ተጨባጭነት (ቃለ ምልልስ ሰፋ ያለ ዉይይትን ስለሚፈቅድ) በማመሳከር ረገድ የጎላ ሚና ስላለዉ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል ለመላሹም ሆነ ለተመራማሪዉ ሃሳብን በነጻነት ለማንሸራሸር ስለሚያስችል (ያለዉ 2006፣180) ነጻ (ልቅ) ቃለ መጠይቅ ተግባር ላይ ዉሏል፡፡የመጠይቁን አቀራረብ በተመለከተ ደግሞ አስር ጥቄዎችን ያካተተ፣ በአማካሪ መምህር የተገመገመ፣ አስቀድሞ የተደራጀ የቃለመጠይቅ ቅጽን አጥኚዉ በቀጠሮ ቀን ይዞ በመገኘት ለእያንዳንዳቸዉ በንባብ ለማቅረብ ሞክሯል፡፡ ያቀረቡትን ምላሽም በጥያቄዉ ወረቀት ላይ በጥንቃቄ በጽሁፍ ለማስፈር ተሞክሯል፡፡

3.3.5.3. ሰነድ ፍተሻ

በዚህ ጥናት ሰነድ ፍተሻ አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ አገልግሏል፡፡ በሰነድ ፍተሻዉ አማካኝነት በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆኑ የክፍል ደረጃዎች ማለትም ከ7ኛ -12ኛ ክፍል በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መጻሕፍት ውስጥ ከቋንቋው ትምህርት ይዘቶች ጋር ምን ያህል ስለዘዬ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚያስችሉ ርዕሶች እንደተካተቱ ለመዳሰስ

ተሞክሯል፡የዘዬ ይዘቶቹ እንደ አንድ ይዘት መነሳት ብቻም ሳይሆን ምንያህል በየክፍል ደረጃዎች በስፋት እንደተካተቱ ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡

በሌላ በኩል የተማሪዎችን ደብተርና የመምህራንን ማስታወሻ ደብተሮች በመፈተሸ ዘያዊ ርዕሰ ጉዳዮች ለጥናቱ በተመረጡ የክፍል ደረጃዎች መካተት /አለመካተታቸዉንና እንዲሁም ተማሪዎችና መምህራን በጽሁፍ በሚጠቀሙበት ቋንቋ የየትኛው የአማርኛ ቋንቋ ዘዬ እንደተንጸባረቀ ለመለየት ተሞክሯል የተገኘው መረጃም በዚህ ጥናት የመረጃ ትንተና ክፍል ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

3.3.5.4. የቡድን ተኮር ውይይት

ቡድን ተኮር ውይይት በዚህ ጥናት ከተመረጡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አንዱ ሲሆን ከተማሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ ዉሏል፡፡ በቡድን የተደረገው ውይይት 60 ተማሪዎችን ያቀፈ ሲሆን በሶስት ዙር ተካሂዷል፡፡ እያንዳንዱ ዙር 20 ተማሪዎችን ያሳተፈ ሲሆን አጥኚዉ ዉይይቱን በመደገፍ ስኬታማ እንዲሆን ያላሳለሰ ጥረት አድርጓል፡፡ተማሪዎቹ የተመረጡት በዓላማ ናሙና ሲሆን ፡አማርኛ መምህራን

በመረጣዉ ተግባር እንዲሳተፉ ተደርጓል፡ይኼዉም መምህራኑ ከሚያስተምሯቸዉ ተማሪዎች መካከል በትምህርት አቀባበላቸዉ የተሻሉ ሆነዉ ተገቢ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ተብለዉ የተመሰከረላቸዉና በአማርኛ ቋንቋ ቀበልኛ ዘዬዎቸ ይጠቀማሉ /ይገለገላሉ/ በሚል በአስተማሪዎቻቸዉ የተለዩ ተማሪዎች በዉይይቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

3.3.5.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ለዚህ ጥናት የተመረጠው ዋናዉ የምርምር ዘዴ አይነታዊ ምርምር ሲሆን በአጋዥነትም መጠናዊ ምርምር ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በመሆኑም ከመምህራንና ተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ፣ ከመምህራን በቃል መጠይቅ እንዲሁም ከተማሪዎች የቡድን ውይይትና ከሰነድ ፍተሻ የተሰበሰበዉ መረጃ በአይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴዎች ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

ምዕራፍ አራት

የመረጃ ትንተና

4.1. ከጽሁፍ መጠይቅና ከቃል መጠይቅ የተገኘው መረጃ ትንተና

ጥያቄ1. እርስዎ የየትኛው የአማርኛ ቋንቋ ዘዬ ተናጋሪ ነዎት? በሚል የቀረበላቸውን ጥያቄ ሲመልሱ 11 መምህራን ማለትም (44%)ቱ መላሾች የጎጃም ዘዬ እንደሚናገሩ አስረድተዋል። ሶስት መምህራን (12%) መላሾች ደግሞ የወሎ ዘዬ ተናጋሪ እንደሆኑ ገልጸዋል። አራት መምህራን (16%) መላሾች ደግሞ የጎንደር ዘዬን እንደሚናገሩ አስረድተዋል፡ስድስት መምህራን(24%)ቱ በበኩላቸዉ ደግሞ የአዲስ አበባዉን የአማርኛ ቋንቋ ዘዬ እንደሚናገሩ ገልፀዋል። አንድ ብቸኛ 1(4.%)መምህር የሸዋን ዘዬ እናገራለሁ ብለዋል። የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተዉ ተጠኚዎቹ ከቁጥር ብልጫ አንጻር በቅደም ተከተል የጎጃም ፣የአዲስ አበባ፣የጎንደር፣ የወሎና የሸዋ ዘዬዎችን የሚናገሩ መሆናቸዉ ታዉቋል። ተማሪዎችም በበኩላቸዉ የአማርኛ መምህርህ/ሽ በንግግራቸዉ የትኛዉን የቋንቋዉን ዘዬ በስፋት ይናገራሉ? ተብለዉ ተጠይቀዉ መልስ ሰጥተዋል። የሰጡት ምላሽ በደረጃ ሲታይም 132(48.9 %) መላሾች መምህራችን የአዲስ አበባዉን ዘዬ ይናገራሉ ብለዋል፣ 87 (32.2 %) መላሾች ደግሞ የጎጃም ዘዬ ይናገራሉ ብለዋል። 33 (12.2)ተማሪዎቸ በበኩላቸዉ መምህራች የጎንደርን ዘዬ ያዘወትራሉ ብለዋል ቀሪዎቹ 12 (4.4 %)ተማሪዎቸ ደግሞ መልስ ሳይሰጡ ቀርተዋል።የተማሪዎቸን ምላሽና የመምህራኑን ምላሽ ለማነጻጸር ስንሞክር በተማሪዎች ምላሽ መሰረት ብዙ ቁጥር ያላቸዉ መምህራን በደረጃ ሲዘረዘሩ አዲሳበብኛ፣ ጎጃምኛና ጎንደርኛ ዘዬ ተናጋሪዎቸ ናቸዉ።የመምህራን ምላሽ የጎጃም ዘዬ ተናጋሪ መምህራን ቁጥር የመጀመሪያዉን ደረጃ እንደሚይዙ ያመለከተበት ሁኔታ ቢኖርም በተማሪዎቸ ምላሽ ግን የአዲስ አበባ ዘዬ ተናጋሪ የሆኑ መምህራን ከሁሉም ብልጫ እንዳላቸዉ ተመልክቷል ።በሌላ በኩል የወሎ እና የሸዋ ዘዬ ተናጋሪ መምህራን መኖራቸዉን የተማሪዎች መረጃ አያሳይም። መምህራንና ተማሪዎች የሰጡት መልስ ሊለያይ የቻለዉ በተለያዩ ምክንያቶች ሊሆን እንደሚቻል ቢገመትም ሊቀርቡ ከሚችሉ ምክንያቶች አንዱ ተማሪዎቹ ስለዘዬ ያላቸዉ ግንዛቤ አናሳ መሆን ነዉ ሊባል ይችላል።ምክንያቱም የወሎና የሸዋ ዘዬዎችን የሚናገሩ መምህራን መኖራቸዉን መምህራኑ ራሳቸዉ የገለጹ ቢሆንም ተማሪዎች ግን መለየት አልቻሉም ።በሌላ በኩል ምላሽ መስጠት ያልቻሉ ጥቂት(12)ተማሪዎች መኖራቸዉም እንዲሁ ከግንዛቤ ክፍተት የተነሳ የሚሉትን ከማጣት የመነጨ ነዉ ሊባል

ስለሚችል ነዉ፡፡ያም ሆነ ይህ ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኘዉ መረጃ የሚያሳየዉ ለዚህ ጥናት የተለዩት መምህራን ቁጥራቸዉ ይብዛም ይነስ የአማርኛ ቋንቋን ልዩ ልዩ ዘዬዎቸን የሚናገሩ ሆነዉ መገኘታቸዉን ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ ዘያዊ ልዩነቶቸ ቋንቋዉን በማስተማር መማር ሂደት የሚኖራቸዉን ተጽዕኖ ለመመርመር የተነደፈዉን ዓላማ ለማሳካት ያስቸላል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ተማሪዎች ራሳቸዉ አንተ/አንቺ / የየትኛዉ የአማርኛ ዘዬ ተናጋሪ ነህ ?/ ነሽ ? ተብለዉ ተጠይቀዉ 103(38%) መላሾች የአዲስ አበባ ዘዬ ተናጋሪዎች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡27(10%) ተማሪዎች ደግሞ የጎጃም ዘዬ የሚናገሩ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡ 17 (6.3 %) ተማሪዎች ደግሞ የጎንደር ዘዬ እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል፡፡) 12(4.5%)ቱ ተማሪዎች ደግሞ የወሎን የአማርኛ ዘዬ እንደሚናገሩ አስረድተዋል፡፡ እንዲሁም 8 (2.9%) ተማሪዎች ደግሞ የሸዋን የአማርኛ ዘዬ እንናገራለን ብለዋል ፡፡ ከፍተኛ አሀዝ ያላቸው ተማሪዎች መደበኛውን የአዲስ አበባ ዘዬ የሚናገሩ ናቸዉ፡፡ ቀሪዎቹ ተማሪዎች በቅደም ተከተል የጎጃምኛ፣የጎንደርኛ፣ የወሎኛና የሸዋ ዘዬዎችን በመናገር በደረጃ ይቀመጣሉ፡፡ እዚህ ላይ መታየት ያለበት ሌላው ነጥብ ተጠኚ ተማሪዎች በሙሉ የአማርኛ ቋንቋ አፍ -ፈት ተናጋሪዎች ብቻ ባለመሆናቸው ቀሪውን (38%) የሚይዙት የኦሮምኛና ሌሎች የደቡብ ቋንቋዎችን የሚናገሩ መሆናቸዉን ነዉ፡፡

ከላይ የተመለከትነዉ መረጃ የሚያሳየዉ በመምህራንም በተማሪዎቸም በኩል አምስት ዓይነት የቋንቋዉ ዘዬዎች የሚነገሩ መሆናቸዉን ነዉ ፡፡ይህ ደግሞ ቋንቋዉን ለማስተማርም ሆነ ለመማር የሚደረገዉን ጥረት በመፈታተን ረገድ ሚና እንዳለዉ መረጃዎቸ ያሳያሉ፡፡ለአብነትም በዚህ ጥናት ታላሚ የሆኑ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎቸ ዘያዊ ልዩነቶቹ መደበኛዉን ዘዬ በመማርና በማስተማር ሂደቱ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ መሆናቸዉን ገልጸዋል፡፡ በቃለ ምልልሱ የተሳተፉ 6(100%)ተጠኚ መምህራን መደበኛዉን ዘዬ ለማስተማር በምንሞክርበት ጊዜ ተማሪዎች በቅላጼያቸን እንዲሁም በምንጠቀማቸዉ አንዳንድ ያልተለመዱ ቀበልኛ ቃላት ፍች የተነሳ ስለሚስቁብንና ስለሚሳለቁብን ያሰብነዉን (የተዘጋጀንበትን) ትምህርት ሳናስተምር እንቀራለን በማለት አስረድተዋል፡፡ ቀበልኛ ዘዬ ተናጋሪ የሆኑ ተማሪዎቸም በበኩላቸዉ መደበኛዉን ዘዬ ለመማር ቀበልኛ ዘያችን ጣልቃ እየገባ እንቸገራለን ብለዋል፡፡ በተለይ የንግግር ክሂልንና የጽህፈት ክሂልን ለመማር የቀበልኛ ዘዬ ጣልቃ ገብነት ጎላ ብሎ አንደሚታይም አስረድተዋል፡፡ በተጨማሪም በክፍል ቋንቋዉን በመማር ማስተማር ሂደት ቀበልኛ ንግግር በሚደመጥበት ጊዜ የክፍል ተማሪዎቹ አቀባበል

ምን ሊሆን እንደሚችል እንዲያስረዱ ተጠይቀዉ ሲመልሱ 96 (72.5)ተማሪዎች ፈገግ ይላሉ ብለዋል፡፡ 54 (20%) ተማሪዎች ደግሞ ይጠቃቀሳሉ (ይጠቋቆማሉ) በሚል መልሰዋል፡፡ 13(43%)ቱ ደግሞ ያዳመጧቸዉን ቃላት ወይም ሀረጋት ይጽፏቸዋል ብለዋል፡፡ 7 (2.3%) መላሾች ደግሞ መልስ ሳይሰጡ ቀርተዋል፡፡ ከፍ ሲል ከተመለከትነዉ መረጃ የምንረዳዉ ነገር በአማርኛ ቋንቋ ዉስጥ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር ቋንቋዉን በማስተማር መማር ሂደት ይብዛም ይነስም የራሳቸዉ ተጽዕኖ ያላቸዉ መሆኑን ነዉ፡፡

ጥያቄ 3፣ እርስዎ የተለያዩ የአማርኛ ዘዬዎችን መናገር የማይችሉ ሆነዉ ነገር ግን በየክፍሉ የሚያስተምሯቸዉ ተማሪዎች ደግሞ የተለያዩ የአማርኛ ዘዬዎችን የሚናገሩ ከሆነ ከመደበኛው ዘዬ ውጪ በሌሎች ቀበልኛዎች የሚጠቀሙ ተማሪዎች በክፍል ዉስጥ የሚሉትን፣ የሚፅፉትን እንዲሁም ሲያነቡ የሚያስደምጧቸዉን ድምጾች መረዳት የሚችሉባቸው ብልሃቶች ምንምን ናቸዉ ? በሚል የቀረበላቸዉን ጥያቄ እንዲያስረዱ መምህራን ተጠይቀው ሲገልጹ ተከታዩን ሐሳብ አስፍረዋል፡፡ 7 መምህራን(28%)ቱ አውድን ወይም አገባብን በመጠቀም የተማሪዎቻቸውን ቀበልኛ ንግግር ሊገነዘቡ እንደሚሞክሩ ገልፀዋል፡፡ አራት መላሾች ማለትም (16%)ቱ ደግሞ ችግር ካጋጠማቸው በሌሎች ጓደኞቻቸው በማስተርጎም እንደሚገለገሉ ገልፀዋል፡፡ 8(32%) መላሾች ደግሞ ከሌሎች መምህራን ጓደኞቻቸው ጋር ዘዬን ጨምሮ በሌሎች ግልፅ ባልሆኑ ነገሮች ላይም እንደሚወያዩ አስረድተዋል፡፡ቀሪዎቹ ስድስት(24%) ተጠኚዎች በበኩላቸዉ የተማሪዎቻቸዉን ዘያዊ ንግግር ለመረዳት ያን ያህል ተቸግረዉ እንደማያውቁ ገልጸዋል፡፡

መምህራኑ ከሰጡት ምላሽ እንደምንገነዘበዉ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚቀርበው የቋንቋዉ ትምህርት የተለያዩ ቀበልኛ አጠቃቀሞችን በሚጠቀሙ ተማሪዎች መኖር የተነሳ አልፎ አልፎ ከመደበኛዉ ቋንቋ ቃላት አጠቃቀም ጎንለጎን ቀበልኛ አጠቃቀሞችም ስለሚነገሩ /ስለሚጻፉ/ መምህራን እነዚህን አጠቃቀሞች ለመረዳት የሚቸገሩበት ሁኔታ አለ፡፡ይሁን እንጅ ችግሩ የተከሰተዉ በአንድ ቋንቋ ዘዬ ተጠቃሚዎች መካከል በመሆኑ ተግባቦቱን ጨርሶ ሊገድበዉ እንደማይችል Cristal (1997፣ 99)፣ (wardhaugh 2010፣29)፣ Thoms (1969, 84, 143) ያስገነዝባሉ፡፡

ለቃለ ምልልሱ ምላሽ የሰጡ 6(100%) መምህራንም በበኩላቸዉ በተማሪዎቻቸዉ ለሚነገሩና ለሚጻፉ ቀበልኛ አጠቃቀሞች ተገቢ የሆነ ግብረ-መልስ እንደሚሰጡ ጠቅሰዉ ዘያዊ አጠቃቀሞቹ ግን ተግባቦትን ጨርሶ አስከ መገደብ አንደማይደርሱ አስረድተዋል፡፡

ጥያቄ 4 ፣በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የአማርኛን መደበኛ ዘዬና እንዲሁም ሌሎች ቀበልኛ አነጋገሮችን የሚጠቀሙ ተማሪዎች እኩል ውጤታማ ናቸው ብሎ መናገር ይቻላል? በሚል የቀረበውን ጥያቄ ሲመልሱ ሁሉም 25(100%)ቱ መላሾች አይቻልም ብለው መልሰዋል። በቡድን ዉይይት የተሳተፉ ተማሪዎችም እንዲሁ ከዚሁ ጥያቄ ጋር ተቀራራቢ የሆነ ጥያቄ ተጠይቀዉ መልስ አስፍረዋል ።ምላሻቸዉም መደበኛ ዘዬ ተናጋሪ ተማሪዎችና መደበኛ ያልሆኑ ዘዬዎችን የሚናገሩ ተማሪዎች በአንድ ላይ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘታቸዉ የመማር ማስተማሩ ሂደት ጤናማ እንዳይሆን የማድረግ ሚና አላቸዉ ብለዋል። ምክንያቶቹን ሲያስረዱ ከዘረዘሯቸዉ ነጥቦች መካከልም የትምህርት አቀባበል ልዩነት እንዲኖር የሚያደረግ የስራ ጫና በመምህራን ላይ ይፈጥራሉ ፣ግብረ መልስ የሚፈልጉ ተግባራት ስለሚበዙ ሰአት ይዛባል ፣ አልፎ አልፎ አላስፈላጊ ንትርክ ሊፈጠር ሥለሚችል ዉጤታማነትን ይቀንሳል ብለዋል።

ከቀረቡ ምላሾቸ መረዳት የሚቻለዉ ተማሪዎቹ የሚናገሯቸዉ ዘዬዎቸ በተለያዩ ቁጥር ፣ ለመምህሩ የግብረ መልስ አሰጣጥና ለተማሪዎቸ የትምህርት አቀባበል መለያየት በር መከፈት መቻሉን ነዉ።እንዲሁም ተማሪዉ አንዱ በሌላዉ ላይ እንዲስቅ ወይም እንዲያፌዝ በር ስለሚከፍት አለመግባባቶቸ ይፈጠራሉ ፤ ይህም በዉጤት ላይ ተጽዕኖ ያስከትላል።

ጥያቄ 5 አራተኛዉን ጥያቄ ተማሪዎች እኩል ዉጤታማ ሊሆኑ አይችሉም ብለው መልሰው ከሆነ ዘያዊ ልዩነት ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት ምን አይነት ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል? በሚል የቀረበዉን ጥያቄ ሲመልሱ መምህራኑ ያቀረቡት ሐሳብ የተለያየ ቢሆንም አጥኚው ከጥያቄው ጋር በቀጥታ ይዛመዳሉ ያላቸውን በመምረጥ እንደሚከተለው ዘርዝሯቸዋል።

ምንም እንኳን ተማሪዎች እኩል ውጤታማ ይሆናሉ ተብሎ ባይደመደምም ተቀራራቢ ውጤት እንዳያስመዘግቡ የቀበልኛ ንግግር ወይም ዘዬ የበኩሉን አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ ሁሉም ተጠኚ መምህራን እንደሚያምኑበት ገልፀዋል።በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ ዘዬ ተናጋሪዎቹ መካከል ሊኖሩ ስለሚችሉ ልዩነቶች ሲያስረዱም የሚከተሉትን ዋና ዋና ሀሳቦች አስፍረዋል። በተማሪዎች መካከል አልፎ አልፎ ለሚፈጠር የእርስበርስ መናናቅ ዘዬ ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል። ይሄዉም (የእኛ አነጋጋር ዘመናዊ ነው፣ የአንተ ፣ የአንቺ፣ የእናንተ ኋላቀር ነው ፤ የገጠሬ አነጋገር ነው ፣መዝገበ ቃላት ላይ የሌለ ነገር ነው ወዘተ) በመባባል ፣ተማሪዎች ሲከራከሩ እንደሚደመጡ መምህራን ምስክርነት ሰጥተዉበታል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ቀበልኛ ንግግር ተጠቃሚዎች በራሳቸው የቋንቋ አጠቃቀም ስልት

“ማን ከማን ያንሳል” በሚል ፋክክር ገታራነትን /Ridigity/ ሊቀጥሉበት፣ አልያም ደግሞ በተቃራኒው ሊያፍሩበትና ሊሸማቀቁበት ስለሚችሉ በክፍል ውስጥ የሚኖራቸውን የቋንቋ ትምህርት ተጋልጦ (ተሳትፎ) ሊቀንሱት ይችላሉ የሚልስጋትም እንዳላቸው መምህራኑ አስረድተዋል፡፡መደበኛ ዘዬ ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎች ቀበልኛ ዘዬዎችን ከሚጠቀሙት ይልቅ በክፍል ውስጥ ለሚቀርበው መደበኛ የቋንቋ ትምህርት ያለምንም መሸማቀቅ በነፃነት ቋንቋዉን ስለሚጠቀሙበት) የተሻለ አቀባበል ያላቸዉ ስለመሆኑ መምህራኑ አስረድተዋል፡ቀበልኛ ዘዬ ተጠቃሚ የሆኑት ተማሪዎች በአንጻሩ በግልም ሆነ በጋራ የሚሰጡ ስራዎችን በተማሪዎች ፊት ወጥቶ ለማቅረብ ፤ በአነጋገሬ ይሳቅብኛል በሚል ምክንያት በሚፈለገዉ መጠን ተሳትፎ ስለማያደርጉ ቀበልኛ የቋንቋ አጠቃቀም ችግር እየፈጠረባቸዉ መሆኑን አንዷት እንስት መምህር ገልጸዋል፡፡ ተጠኚ መምህራኑ አክለዉም በተለይ በንግግር ክሂል እንዲሁም በመጻፍ ክሂል ትምህርቶች ሌላው ቢቀር መደበኛ ቃላትን፣ ድምፆችንና እንዲሁም ሃረጋትን መርጦ በመጠቀም ችሎታቸው መደበኛ ባልሆነዉ ዘዬ የሚገለገሉ ተማሪዎች መደበኛዉን ዘዬ ከሚጠቀሙ ተማሪዎቸ ይልቅ ያነሰ ችሎታ እንደሚታይባቸዉ በሚሰሩአቸዉ የቤት ስራዎችና የክፍል ዉስጥ አቀራረቦች /presentations/ያረጋገጡበት ሁኔታ መኖሩን መምህራኑ ገልጸዋል፡፡

ከፍ ሲል የቀረበዉን ርእሰ ጉዳይ የትኩረት ነጥብ በማድረግ Snell &Andreiw (2014) ጥናት አካሂደዋል፡፡በምርምር ስራቸዉም የመናገርና የመጻፍ ክሂሎችን በማሳደግ ሂደት ክልላዊ ዘዬና ቅላጼ ምን ያህል ተጽእኖ እንዳላቸዉ ፈትሸዉ በምርምሩ የተደረሰባቸዉን ዉጤቶችም እንደሚከተለዉ ይፋ አድርገዋል፡፡

- መናገርና መጻፍን በመማር ዉጤታማ ለመሆን በሚደረገዉ ጥረትና በተማሪዎቸ የቋንቋ ቅድመ ዕዉቀት /background/ መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት እንደሌለዉ በጥናቱ ተገልጸል፣
- መናገርና መጻፍን ለማሳደግ በሚደረገዉ ሙከራ ክልላዊ ዘዬ ከጽህፈት ይልቅ አንጻራዊ በሆነ መልኩ ንግግርን ለማሳደግ በሚደረገዉ ሙከራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳለዉ ተጠቅሷል፡፡ በጥናቱ መረጃ መሰረት ይህ ሊሆን የቻለዉ ምንም እንኳዋ ጉዳዩ ሌላ ሰፊ ጥናት የሚፈልግ ቢሆንም አንደኛዉ ምክንያት የንግግር ክሂል ከጽኅፈት ክሂል ይልቅ ሰዎቸ በማይገነዘቡት ፍጥነት ስለሚቀያየር መሆኑ ተጠቅሷል፡፡

- ለክልላዊ ዘዬና ለቅላጼ ማህበረሰቡ የሚኖረዉ አሉታዊ ዝንበሌና በክፍል ዉስጥ መደበኛ ላልሆኑ ድምጾች በመምህራን የሚሰጠዉ ተገቢ ያልሆነ ግብረ መልስ በተማሪዎቸ ዉጤታማነት ላይ ከባድ ተጽእኖ እንዳለዉም ተጠቁሟል፡ይሄዉም በቂ ገለጻ ሳይቀርብባቸዉ ከተማሪዎች ጽሁፎቸ መደበኛ ያልሆኑ ዘያዊ ቅርጾችን ለማስተካከል መሞከር በተማሪዎቸ ዘንድ መደናገርንና መጨናነቅን የሚያስከትል መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

ከላይ የተመለከትነዉ የጥናት ዉጤት በዚህ ጥናት ከተነሳዉ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ሲነጻጸር መናገርና መጻፍን በመማር ማስተማር ሂደት ዉጤታማ ለመሆን የሚደረገዉ ሙከራ ከተማሪዎች የቋንቋ ልምድ/ቅድመ ዕዉቀት ጋር/ ቀጥተኛ ግንኙነት የለዉም ከሚለዉ ድምዳሜ በስተቀር በሌሎቸ ሃሳቦቸ ላይ ተቃራኒነት አይታይበትም፡፡ምክንያቱም የተማሪዎቸ የቋንቋ ቅድመ ዕወቀት መናገርና መጻፍን ጨምሮ ሌሎች ይዘቶችንም ለመማርና ዉጤታማ ለመሆን ቀጥተኛ ግንኙነት አለዉ በሚል መነሻ ነዉ ይህ ጥናት ዘያዊ ልዩነቶቸ ቋንቋን በመማርና ማስተማር ሂደት የሚኖራቸዉን ተጽእኖ ለመፈተሽ የቀረበዉ፡፡የተማሪዎቸ የቀደመ ቀዉቀት ከሚባሉት አንዱ ዘዬ ነዉ ዘዬ ደግሞ ቋንቋን በመማር ሂደት ተጽዕኖ እንዳለዉ በጥናቶቸ የተረጋገጠበት ሁኔታ አለ፡፡ለአብነትም Hagen(1989፣ 48-61) የቋንቋ ክሂሎችን ተምሮ ዉጤታማ ለመሆን በሚደረገዉ ሙከራ ዘዬ ተጽዕኖ እንደለዉ አስረድተዋል፡፡ Hudson (2001፣ 265)ም እንዲሁ ዘዬ የማንበብ ክሂልን በክፍል ዉስጥ በመማሩ ሂደት ተጽዕኖ ያለዉ ስለመሆኑ በጥናታቸዉ አረጋግጠዋል፡፡በዚህ ጥናት ተሳታፊ የሆኑ መምህራንና ተማሪዎች የሚያቀርቡት መረጃም የሚያመለክተዉ ዘዬ ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት ተጽዕኖ ያለዉ መሆኑን ነዉ፡፡

ለአምስተኛዉ ጥያቄ መምህራኑ የሰጡትን ምላሽ ስንመለከት ደግሞ ፦ መደበኛ ያልሆኑ ቃላትና ሃረጋትን፣ ያልተለመዱ ድምፆችን የሚጠቀሙ ተማሪዎች ብዙዉን ጊዜ ከእድሜ አቻዎቻቸዉ በሚደርስባቸው ሹፈት፣ ሳቅና አሉታዊ ግብረ መልሶች የተነሳ በነፃነት የመማር መብታቸው ጥያቄ ውስጥ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የተወዳዳሪነት መንፈሳቸዉ (ሞራላቸው) እየቀዘቀዘ ሊሄድ ይችላል የሚል ሐሳብ እንዳላቸው ተጠኚ መምህራኑ በዝርዝር አስገንዝበዋል፡፡ከፍ ሲል ለማቅረብ የተሞከረዉ የ(Snell &Andrew 2014)የጥናት ዉጤትም መደበኛ ያልሆነዉን ዘዬ ለሚናገሩ ተማሪዎቸ የሚሰጠዉ ግብረ መልስ አዎንታዊ ካልሆነ የተናጋሪዎቸን ሞራል ክፉኛ እንደሚጎዳዉ አመላክቷል፡፡

ተማሪዎችም በዚሁ ሀሳብ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት በሚል አንተ/ቺ የምትናገረው/ሪው ዘዬ (ቀበልኛ) መደበኛውን የአማርኛ ዘዬ ስትማር/ሪ ጣልቃ በመግባት ተጽዕኖ ያሳድርብሃል/ሻል? እንዴት? በሚል ተጠይቀዋል፡፡ የሰጡት ምላሽም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መደበኛ ያልሆነዉን የአማርኛ ቋንቋ ዘዬ ከሚናገሩ (25.9%) መላሾች መካከል (14%) ተጠኚ ተማሪዎች መጠነኛ ተጽዕኖ አለው ብለዋል፡፡ (6%)ቱ መላሾች ደግሞ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዳለው ገልጸዋል፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መላሾች መጠነኛ ተፅዕኖ እንዳለው ነው የገለጹት፡፡ በአንጻሩ(5.9%) መላሾች በበኩላቸዉ ደግሞ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚያሳድርባቸው አስገንዝበዋል፡፡ተማሪዎቹ የሰጡትን ምላሽ ስንመለከት ቀበልኛ አነጋገር መደበኛ ዘዬን በመማር ሂደት ተጽዕኖ አለው ወደሚል ድምዳሜ የሚወስድ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ይሄዉም ተጽእኖ አለው ካላሉት ጋር ሲደመሩ ተጽዕኖ የለውም ብለው የመለሱት በቁጥር የበለጡ ስለሆኑ ነው፡፡፡

ጥያቄ 6፣ በዚህ ጥያቄ እርስዎን ጨምሮ ሌሎች የአማርኛ መምህራን ለአማርኛ ቋንቋ ዘዬዎች እኩል እይታ (አመለካከት) አላችሁ? የሚል ሃሳብ ቀርቦላቸዉ መልሰ ሰጥተዉበታል፡፡ከመጠይቁ የተገኘዉ ምላሽም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡ተጠኚ መምህራንም ስለዘዬዎች ያላቸውን አመለካከት ለመፈተሸ ታስቦ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ 13 (52%)ቱ መላሽ መምህራን “አዎ” በሚል የመለሱ ሲሆን ቀሪዎቹ (12%) መምህራን ደግሞ ቀበልኛ ንግግርና መደበኛ ዘዬ በቋንቋ ትምህርት ዉስጥ በእኩል ደረጃ ትኩረት ሊደረግባቸዉ ይገባል ብለን አናምንም ብለዋል መምህራኑ አክለዉም ትምህርቱ የሚሰጥበትን መደበኛ ዘዬ እናስቀድማለን፣ቀበልኛ ንግግሮቹ በመመደበኛው የሚሻሻሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት መደበኛዉን ዘዬ አጽንኦት ሰጥተን እናስተምራለን ብለዋል፡፡ በአንጻሩ ዘየዎቹን በእኩል ደረጃ እንመለከታለን ያሉት መላሾች ደግሞ ለምን? በሚል የቀረበውን ጥያቄ ሲመልሱ የየትኛውም ቋንቋ ዓላማው ሰዎችን ማግባባት ማስቻል እስከሆነ ድረስ ሁሉም ዘዬዎች እንዲሁ ማግባባት ስለሚያስችሉ እኩል ናቸው ብለን እናምናለን የሚል ሐሳብ አቅርበዋል፡ መምህራኑ እንደገለጹት በቋንቋ ውስጥ የተለያዩ ዘዬዎች ይኖራሉ፤ እነዚህ ዘዬዎች በቋንቋ ሳይንስ ሲታዩ፤ ቋንቋዎች ሁሉ እኩል ስለሆኑ ዘዬዎችም እኩል የማይሆኑበት ምክንያት አይኖርም ብለዋል፡፡ ከላይ የቀረበው ምላሽ እንደሚያስገነዝበው መምህራን ስለዘዬ ያላቸው ግንዛቤ የተለያዩ መሆኑን ነው፡፡

ከቃለ ምልልስ የተገኘዉ ዉጤት እንዳመለከተዉ ደግሞ በአመዛኙ ዘዬዎችን በእኩል ደረጃ መመልከት ተገቢነት አለዉ ።ለዚህ ሃሳብ ማስረጃ ሲያቀርቡም በቀበልኛ ዘዬ መጠቀምን የኋላ ቀርነት ምልክት አደርገዉ የሚመለከቱ ወገኖች ቢኖሩም እዉነታዉ ከዚህ ዉጭ ነዉ። ምክንያቱም በቋንቋ ሳይንስ ወይም በስነልሳን ዘርፍ ቋንቋዎች ሁሉ እኩል ናቸዉ ፤በመሆኑም በዘዬዎች መካከልም እኩልነት አለ። ዘዬዎችን ማበላለጥ የግንዛቤ ችግር ነዉ ፣ወዘተ የሚሉ ምላሾች በተጠኚ መምህራኑ የተገለፁ ስለመሆኑ በአባሪነት ከዚህ ጥናት መጨረሻ በተካተቱ ወረቀቶቸ ዉስጥ በዝርዝር መቅረባቸዉን ይመለከቷል።

ተማሪዎች በበኩላቸዉ በመደበኛ ዘዬና መደበኛ ባልሆነ ዘዬ መካከል ያለዉን ልዩነት በዉይይት እንዲገመግሙ በተዘዋዋሪ ስለዘዬዎች ያላቸዉን ግንዛቤ እንዲያስረዱ ተጠይቀዉ መልስ ሰጥተዋል።ሆኖም ከቀረቡ ምላሾች መረዳት የተቻለዉ ለመደበኛዉ ዘዬ ከፍተኛ ግምት የመስጠት፤ በአንጻሩ ቀበልኛ ዘዬዎችን ደግሞ ዝቅ አድርጎ የመመልከት ዝንባሌ፣ በተማሪዎቸ የቡድን ዉይይት በስፋት መንጸባረቁ ታወቋል። በተመሳሳይ ሁኔታ ቀበልኛ ተናጋሪዎቹ ራሳቸዉ መደበኛዉን ዘዬ መጠቀም የማይቸሉ ያልሰለጠኑ በተራ መግባቢያ የሚገለገሉ ተደርገዉ የተገለጹበት ሀተታም በዉይይታቸዉ ተካቷል።

ከፍሲል ለማቅረብ እንደተሞከረዉ በዘዬዎች ስነልሳናዊ ባህርይ እኩልነት ላይ የተዛባ አመለካከት አለ። መምህራንም ተማሪዎቸም ካቀረቧቸዉ ምላሾች ማረጋገጥ የሚቻለዉ ይህንኑ የግንዛቤ ክፍተት መኖሩን ነዉ።ይሁን እንጅ በምዕራፍ ሁለት የክለሳ ድረሳን ክፍል ለማሳየት እንደተሞከረዉ ዘዬዎች በአንድ ቋንቋ ዉስጥ የሚገኙ የአጠቃቀም ልዩነቶች ናቸዉ።

Peter (2002) እንዲሁም Schuchi (2013) ያቀረቧቸዉ ሀተታዎች በዉል እንደሚያስረዱት በግንዛቤ ዉሱንነት የተነሳ ቀበልኛ አነጋገሮች በተናጋሪዎቻቸዉ ሳይቀር ለተግባቦት የማይመጥኑ ብልሹ ሰዋስዉና አነባበብ ያላቸዉ ተደርጎ የሚታዩበት ሁኔታ መኖሩ ተጠቅሷል።

ጥያቄ 7፣ የተለያዩ ቀበልኛ ተናጋሪ የሆኑ ተማሪዎች በሚናገሩት ዘዬ ይሳቅበናል (እንናቃለን) ሳይሉ ምን ያህል በልበ ሙሉነትና በኩራት በክፍል ዉስጥ እንደሚጠቀሙበት እንዲያስረዱ ተጠይቀዉ መምህራን መልስ ሰጥተውበታል። ይኼውም 3(12%) መምህራን ሁልጊዜም በነፃነት በዘያቸው ይጠቀማሉ ብለዋል፡ 4 (16 %) መላሾች ደግሞ አልፎ አልፎ ይጠቀሙበታል ብለው መልስ ሰጥተዋል። ቀሪዎቹ 8 (32%)ቱ መላሾች በበኩላቸው በቀበልኛ

ንግግር ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎች ፈጽሞ በዚያቸው ኮርተው በነፃነት ሲጠቀሙባቸው አይታዩም ብለዋል። ከዚህም የምንረዳው ተማሪዎች ቀበልኛ የቋንቋ አጠቃቀማቸውን በነፃነት የማይጠቀሙበትና የሚሸማቀቁበት መሆኑን ነው።። ይህ ደግሞ ተማሪዎቹን በመማር ማስተማሩ ሂደት ፍዝ ተሳታፊ /passive participant/ እንዲሆኑ የማድረግ ተፅዕኖ ያስከትላል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ተማሪዎቹም ይህንን ጥያቄ ተጠይቀዉ መልስ ሰጥተዉበታል። ይሄዉም 89 (32.9 %)ተማሪዎች ሁልጊዜ በነጻነት ይጠቀሙበታል ብለዉ መልሰዋል። 104 (38.5%) ተማሪዎች ደግሞ አልፎ አልፎ የሚለዉን መልስ መርጠዋል። ቀሪዎች 132(71.5) በበኩላቸዉ ደግሞ ቀበልኛ ተጠቃሚ ተማሪዎች ሳይፈሩ በነጻነት በቀበልኛ ዘያቸዉ ሲጠቀሙባቸዉ እነደማይታዩ አስረድተዋል። ከቀረበዉ መረጃ መረዳት የሚቻለዉ በቀበልኛ ዘዬ መጠቀም የኂላ ቀርነትና የሌሎች መሰል መገለጫዎች ምልክት ተደርጎ ሚታይበት ሁኔታ በተማሪዎቹ መካከልም መኖሩን ነዉ።

በተማሪዎች ተፈጥሯዊ ዘዬ ትምህርቱን ማቅረብ ጠቀሜታው የጎላ እንደሆነwondimu (2015፣14) ያቀረቡት ገለጻ ያስረዳል።ይሄዉም ተማሪዎች ተፈጥሯዊ በሆነው ዘያቸው እንዲማሩ ከተደረገ ማህበራዊ፣ አእምሯዊና ስነልቡናዊ እንዲሁም ስነልሳናዊ ዕድገታቸው ይፋጠናል። ሆኖም ተማሪዎች በሚናገሯቸው ዘዬዎች በነፃነት መጠቀም አለመቻላቸዉ እነዚህን ከላይ የተመለከትናቸዉን ጠቀሜታዎች ሁሉ የሚያሳጧቸው መሆኑ አያጠያይቅም። ይሁን እንጅ በሁሉም ዘዬዎች ትምህርቱ ይቅረብ ከተባለ ብክነትን ስለሚያስከትል የቋንቋ ትምህርት አሰጣጡ በመደበኛዉ ዘዬ ላይ አተኩሮ ቀበልኛ ንግግሮችም በቋንቋ ዘርፍ የትምህርቱ አካል መሆናቸዉ ሳይዘነጋ በመደበኛዉ ዘዬ ዉስጥ እነደ አንድ የስነ ልሳን ለዉጥ; Lingustic Varity/ መጠናት፣ መገለጽ፣ መተንተን ያለባቸዉ መሆኑን ተጠኚ መምህራኑም ሆነ ተማሪዎች የዘነጉበት ሁኔታ ተሰተዉሏል።

ተጠኚ ተማሪዎች ቀበልኛ ዘዬ የምትናገር/ሪ ከሆንክ ሽ መደበኛን ዘዬ ለመማር ምን ያሕል ተጽዕኖ ያሳድርብሀል /ሻል የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸዉ ሲመልሱ 7(2.3%) መላሾች በከፍተኛ ደረጃ ብለዋል።31 (11.5%)ተማሪዎች ደግሞ ተጽዕኖዉ በመካከለኛ ደረጃ ሊታይ የሚችል ነዉ ብለዋል። ቀሪዎቹ 232(85.9%)መለሾች ደግሞ ምንም አይነት ተጽዕኖ ኢያመጣብንም ብለዉ መልሰዋል ።ይሁን አንጅ በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳን ክፍል የቀረቡ የመስኩ ምሁራን ማስረጃዎች ቀበልኛ ንግግር መደበኛዉን ዘዬ ለመማር በሚደረገዉ እንቅስቃሴ የሚያሳድረዉ የራሱ የሆኑ ተጽዕኖዎች እንዳሉት አስገንዝበዋል ።በሌላ በኩል ቃለመጠይቅ

የተደረገላቸዉ መምህራን አና እንዲሁም ከፍ ሲል እንደተመለከትነዉ ለሰባተኛዉ ጥያቄ መልስ የሰጡ አነስተኛ ቁጥር ያላቸዉ ተማሪዎችም ያስረዱት አሉታዊ ተጽዕኖ ያለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ከቀረበዉ ምላሽ እንደተመለከትነዉ ብዙ ቁጥር ያላቸዉ መላሾቸ ቀበልኛ ዘያቸዉ መደበኛዉን ዘዬ ለመማር በሚያደርጉት ጥረት ሁሉ፣ ምንም አይነት ተጽዕኖ እንደማያደርግባቸዉ ነዉ የገለጹት፡፡

ጥያቄ 8፣ በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎችን የሚናገሩ ተማሪዎች ተደጋግፈዉና ተከባብረው ትምህርታቸውን ይከታተሉ ዘንድ ከመምህራንና ከተማሪዎች ምን ይጠበቃል? ይህንን ጥያቄ ተጠኚዎች ሲመልሱ ዋና ዋና ነጥቦች በሚል ያስፈሯቸው ሀሳቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ዘዬን መሰረት ያደረጉ አለመግባባቶቸ የሚፈጠሩት አልፎ አልፎ ሲሆን መንስኤዎቹ ደግሞ በአመዛኙ በግንዛቤ አጥረትና አልፎ አልፎም ንግግርን መሰረት ባደረገ ሁኔታ ለቀልድ ተብሎ በሚነገሩ "የፉገራ " ስድቦቸ ለምሳሌ (ቆምጨዉ፣ዴሴ፣ ዴምበኛ፣ ማር! !ማር ! ማር) እና ሌሎች ከቋንቋ ትምህርት ዉጭ በሆኑ አውዶች የሚከሰቱ በመሆናቸዉ መምህራን የተማሪዎችን ግንዛቤ የማሳደግ ሰፊ ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል የሚሉ ሃሳቦችና እንዲሁም ተማሪዎችም የራሳቸው የቋንቋ አጠቃቀም ስልት በሌሎች ዘንድ ይታወቅላቸውና ይከበርላቸው ዘንድ የአቻዎቻቸውን ዘዬ ማክበር ይጠበቅባቸዋል ፣መምህራን ዘዬን ጨምሮ በሌሎች የቋንቋ አጠቃቀም ስልቶች ላይ ግንዛቤ በማሳደግ ተማሪዎቻቸውን በተሟላ ድገፍ ማገዝ ይጠበቅባቸዋል የሚሉ ገንቢ ሃሳቦችን የያዙ ምላሾች ተሰንዝረዋል፡፡

ከዚህ የምንረዳው በትምህርት ቤቶች አካባቢ ለትምህርት የተመረጠውን ቋንቋ ከማሳደግ ተልዕኮ አንፃር ትኩረት የሚሰጠው ለመደበኛው ዘዬ ነው፡፡ ሆኖም በቀበልኛ ንግግር የሚጠቀሙ ተማሪዎችም መደበኛውን ዘዬ ለምደው ቀበልኛ አጠቃቀምን እስካላሻሻሉ ድረስ ግለዘያቸውን መጠቀማቸው አይቀሬ ጉዳይ በመሆኑ ቀበልኛ አጠቃቀምን የሚያጣጥሉ፣ የሚያንኳስሱ ወገኖች እንዳይኖሩ የሚያስችል ግንዛቤ በተማሪዎችና በመምህራን አካባቢ መፈጠር ያለበት መሆኑን ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ቀበልኛ ተናጋሪዎችን መጠቋቆሚያ የማድረግ አዝማሚያ ስለሚኖር በተማሪዎች መካከል አለመግባባት ይፈጠር ዘንድ በር ይከፍታል፡፡

ጥያቄ 9፣ የተለያዩ የአማርኛ ቋንቋ ቀበልኛ ተናጋሪዎች በቋንቋዉ የትኛውን የትምህርት ይዘት ሲማሩ የበለጠ ይቸገራሉ?

ሀ ማዳመጥን ለ. መናገርን ሐ. ማንበብን መ. መፃፍን ሠ. ሰዋስውን?

ቀበልኛ ዘዬ ተናጋሪዎች መደበኛውን ዘዬ ለመማር በሚሞክሩበት ጊዜ በቀላሉ ለመማር የማይችሉት የትኛውን የቋንቋ ትምህርት ይዘት እንደሆነ ለማወቅ ተፈልጎ የቀረበውን ይህንን ጥያቄ ተጠኚዎች እንደየራሳቸው ገጠመኝና ተሞክሮ መልሰውታል፡፡ ይኸውም 12(48%) መላሾች ሰዋስውን ለመማር ይቸገራሉ ብለዋል፣ ሌሎች አምስት (20%)ቱ መላሽ መምህራን በበኩላቸው ከመደበኛ ዘዬ ተናጋሪ ዉጭ የሆኑ ተማሪዎች መደበኛውን ቋንቋ ሲማሩ የበለጠ ችግር የሚያጋጥማቸው የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ሲማሩ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ እነዚህ መምህራን እንዳሰፈሩት ማብራሪያ ከሆነ ተማሪዎቹ ንባብ በሚያነቡበት ጊዜ ወይም የቃል ጥያቄ በሚያቀርቡበትና ጥያቄ በሚመልሱበት ጊዜ ከተለመደው የቋንቋው ድምጾች የተለዩ ድምጾችን ስለሚጠቀሙ የክፍሉ ተማሪዎች እነዚህን እንግዳ ድምጾች ወይም ቃላት ሲሰሙ ስለሚስቁባቸው እንደልባቸው እንዳይናገሩ ወይም ጮክ ብለው ንባብ እንዳያነቡ የሚያደርግ ይሉኝታ ይይዛቸውና ዝምታን ይመርጣሉ ብለዋል፡፡ ከነዚህ አምስት መላሾች መካከል አንዲት እንስት መምህርት ስታስረዳ አንዳንድ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሀሳብ ሲያቀርቡ ወይም ንባብ ሲያነቡ የክፍሉን ተማሪዎች እንዲስቁ የሚያነሳሱ በቃላት ዉስጥ የሚገኙ አንዳንድ ድምጾችን ቀይረዉ (ዲርሰት፣ ልቦለዲ፣ ከእንግድህ ወድህ፣ እዝህም ሆነ እዛ፣ ዛዲያማ፣ ኀላስ…) የመሳሰሉትን አገላለጾች በሚጠቀሟቸዉ ቃላት ዉስጥ ቀላቅለዉ ስለሚናገሩ ክፍሉ እንዳይረበሽ በሚል ምክንያት ተማሪዎች እጅ ቢያወጡም እንኳዋን እድል የማይሰጧቸው መምህራን መኖራቸውን አስረድተዋል፡፡

ሌሎች 4(16%) መምህራን በበኩላቸው ቀበልኛ ተናጋሪ መሆን መደበኛ ዘዬን ለመማር እዚህ ግባ የሚባል ተጽዕኖ የለውም፡፡ ማዳመጥን መናገርን ማንበብን መፃፍን እንዲሁም ሰዋሰውን እንደማንኛውም ቋንቋ ተጠቃሚ መማር ይችላሉ የሚል እንደምታ አዘል ሐሳብ አቅርበዋል፡፡

ቀሪዎቹ 4 (16%) መምህራን ደግሞ ቀበልኛ ተናጋሪዎች መናገርና መጻፍን ለመማር እንደሚቸገሩ ገልፀዋል፡፡ይሄዉም መምህራኑ በምክንያትነት እንዳቀረቡት ሃሳብ ከሆነ የዘዬ ልዩነት በአብዛኛው በቃላት ፍቺ ደረጃ፣ በድምጾች ለዉጥ ደረጃ የሚታይ በመሆኑ ድምጾችን (ቃላትን) ለመጥራት ወይም ለመጻፍ ሲሞክር ቀበልኛ አገላለጽ ጎልቶ ስለሚወጣ በዚህ ምክንያት መቸገሩ አንደሚከሰት አስረድተዋል ፡፡

ከቃለ ምልልስ የተገኘዉን ዉጤት ስንመለከት ደግሞ 2(33.3) መላሾቸ የጎላ ልዩነት አለ ማለት አይቻልም የሚል መልስ አላቸዉ፡፡3(50%)መላሾቸ በመናገር ክሂል ላይ ልዩነት ሊታይ አንደሚቸል አስረጅዎችን አቅርበዋል፡፡ 1(4%) ተጠኚ በበኩላቸዉ በመጻፍና በማንበብ ክሂል ትምህርቶች ላይ ችግር እንደሚገጥማቸዉ አስረድተዋል፡፡

በአጠቃላይ ተጠኚ መምህራኑ ያቀረቡት ሃሳብ እንዳመላከተዉ ተማሪዎች ሲናገሩም ሆነ ሲጽፉ የሚገለገሉባቸዉን ቀበልኛ አጠቃቀሞች ለማስተካከል በተለይ በጽሁፍ ግብረመልስ በበቂ ሁኔታ ለመስጠት ከክፍለ ጊዜ እጥረት አንጻርም ይባል ከተግባሩ አስልችነት አንጻር አዳጋች ነዉ፡፡ በመሆኑም ቀበልኛ ዘዬ ተናጋሪነት መደበኛ ቋንቋን በመማርም በማስተማርም ሂደት ይብዛም ይነስ የራሱ የሆነ ተጽእኖ ያለው መሆኑን መረዳት ይቻላል ፡ተጠኚ መምህራንም የየራሳቸውን ገጠመኝ በመግለጽ ለማሳየት የሞከሩት ይህንኑ ሀቅ ነው፡፡

9ኛዉን ጥያቄ ተማሪዎችም መልስ እንዲሰጡበት ተጠየቀዉ ፣85(31%) ተጠኚዎች ሁሉንም የቋንቋው ትምህርት ዓላማዎች በመማሩ ሂደት ቀበልኛ ንግግር የሚያሳድራቸው ተጽዕኖዎች መኖራቸውን አስረድተዋል፡73 (27%) መላሾች በበኩላቸው በመደበኛው ዘዬ ትምህርት ውጤታማ ለመሆን ቀበልኛ ንግግር ተጽዕኖ አለው ብለው እንደማያምኑ ገልፀዋል፡፡ (16/5.9%) መላሾች በበበኩላቸው በመናገርና በመፃፍ ክሂሎች ላይ ተጽዕኖ እንዳለዉና ቀበልኛ ተናጋሪዎች በነዚህ ሁለት ክሂሎች አቀባበል ላይ ዉጤታማ ለመሆን እንደሚቸገሩ ለመግለጽ ሞክረዋል፡፡ 96(35%)ተጠኙዎች መልስ አላሰፈሩም ፡፡ ከመምህራንና ከተማሪዎች መልስ በመነሳት የተለያዩ የአማርኛ ቋንቋ ቀበልኛ ንግግር ተጠቃሚዎች የቋንቋዉን ትምህርት ዓላማዎችን በመማሩ ሂደት ችግር እንደሚያጋጥማቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ሆኖም በየትኛዉ የትምህርት ይዘት የበለጠ እንደሚቸገሩ ተጨባጭ የሆነ መረጃ አለ ለማለት አይቻልም፡፡

ጥያቄ 10፣ መምህራን የተማሪዎችን ፈተናም ሆነ የክፍልና የቤት ስራዎችን ሲያርሙ ትኩረት የሚያደርጉት ምን ላይ እንደሆነእንዲያስረዱ የምርጫ ጥያቄ ቀርቦላቸዉ ሲመልሱ ከ50 % በላይ መምህራን ማለትም 17 (68%)ቱ መላሾች ለትምህርቱ ይዘት ብቻ ትኩረት እንደሚሰጡ ገልፀዋል፡፡ተማሪዎቹ የተጠየቁትን ተገንዝበው መመለስ ከቻሉ የተጠቀሙበት ቋንቋ በመደበኛ ዘዬ የቀረበ ይሁን አይሁን ነጥብ አያስቀንስባቸዉም በማለት ብዙ ቁጥር ያላቸዉ መምህራን መልሰ ሰጥተዋል፡፡ ሌሎች 6 (24%)ቱ መምህራን ደግሞ ለቋንቋ አጠቃቀማቸው እና ለትምህርቱ ይዘትም ትኩረት እንደሚሰጡ ገልጸዉ ነጥብ ሲሰጡም ከነዚህ ትኩረቶች አንፃር መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ቀሪዎቹ ሁለት መምህራን ለዚህ ጥያቄ መልስ አላሰፈሩም፡፡

ከቀረበው ምላሽ የምንገነዘበው ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት ተጠኚ መምህራን ቀበልኛ ዘዬ ለሚጠቀሙ ተማሪዎች የተጠየቁትን ጥያቄ እስከመለሱ ድረስ ነጥብ የማይቀንሱባቸው መሆኑን ነው፡፡በአንጻሩ የማይናቅ ቁጥር ያላቸው መምህራን ደግሞ ተማሪዎች ትክክለኛ

መልስ ከመመለሳቸውም በተጨማሪ ለቋንቋ አጠቃቀማቸዉም ዋጋ የማይሰጡ ከሆነ ውጤት የሚቀንሱ መሆናቸዉን የሚያመለክተውን አማራጭ መልስ መርጠዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው መምህራን ቀበልኛ የቋንቋ አጠቃቀምን በመደበኛ ዘዬ ለማስተካከል ያላቸው አቋም/ ግንዛቤ/ ተቀራራቢ አለመሆኑን ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የተወሰኑ መምህራን የተማሪዎች የክፍል ዉስጥ የቋንቋ አጠቃቀማቸው በመደበኛው ዘዬ ብቻ እንዲቀርብ ይፈልጋሉ ማለት ነው፡፤ በአንጻሩ ሌሎች መምህራን ደግሞ ዘያዊ አጠቃቀም የሚጠቀሙ ተማሪዎች ሲኖሩ የፈተና ውጤታቸዉን የሚቀንሱባቸዉ መሆኑን ነው የሰጡት ምላሽ የሚያመላክተው፡፡ይህ ወጥነት የሌለዉ አሰራር በተማሪዎች መማር ላይ መደናገርን የሚፈጥር መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ በተለይ የቀበልኛ አጠቀቀማቸዉን መሰረት ባደረገ አስተራረም ዉጤት የሚቀንሱ መምህራን የተማሪዎችን ተነሳሽነት የሚያዳክም ተገባር አየፈጸሙ መሆኑን ያሰፈሩት ምላሽ ያመለክታል፡፡በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳኑ ክፍል እንደቀረበዉ መምህራን የዘዬ አጠቃቀምን በተመለከተ ግብረ መልስ አሰጣጣቸዉ ምክንያታዊና ወጥነትን በተላበሰ መልኩ ካልቀረበ የተማሪዎችን መማር ከፈፉኛ እንደሚጎዳዉ መታወቅ አለበት፡፡

ጥያቁ 11፣ ተማሪዎች ስለ ቀበልኛ አጠቃቀም ያላቸውን ግንዛቤ ለመፈተሽ ተፈልጎ ስለ አማርኛ ቋንቋ ቀበልኛ አጠቃቀም ያላችሁ ግምትና አመለካከት ምን ይመስላል? በሚል ተጠይቀዋል፡፡ ይህንን ጥያቄ ሲመልሱም (81.8%)ተማሪዎች ተገቢ ናቸው ብሎ የማመንና የመቀበል ሁኔታ እንደሌለ በቀበልኛ ንግግር /ዘዬ/ መጠቀም የገጠሬነት /ባላገርነት/ መገለጫ ተደርጎ የሚታይ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ቀሪዎቹ/(18.2%) መላሾች በበኩላቸው ተገቢ ናቸው ብሎ አምኖ የመቀበል ሁኔታ አለ የሚል መረጃ ሰጥተዋል ፡፡

ከቀረበው ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው በተማሪዎች መካከል ቀበልኛ /ዘያዊ/ ንግግርን ለማዳመጥ ፈቃደኝነት የለም፡፡ አንዱ የሌላውን ቀበልኛ ንግግር ለማድመጥ ፈቃደኛ አይደሉም፡፡ ይህንን ሐሳብ መምህራን እንዴት እንደሚገልጹት ለማወቅ ተፈልጎ ተማሪዎቹ ራሳቸዉ ከሚናገሩት ዘዬ /ቀበልኛ ውጭ ሌሎች የሚናገሯቸውን ዘዬዎች ለማዳመጥ ምን ያህል ፈቃደኛ ናቸው? የሚል ጥያቄ ተጠይቀዋል፡፡ ይህንን ጥያቄ የመለሱበት አግባብም የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ሁልጊዜም ፈቃደኛ ናቸው የሚለዉን አማራጭ መልስ የሰጠ መላሽ የለም፡፡ አልፎ አልፎ የሚለውን የመረጡ መላሾች 13 (52%)መምህራን ናቸዉ፡፡ፈቃደኞች አይደሉም በማለት መልስ የሰጡት ደግሞ 12 (48%) መምህራን ናቸው፡፡ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽና መምህራን የሰጡት ምላሽ ሲገናዘብ በተለያዩ የአማርኛ ቋንቋ ቀበልኛ /ዘዬ/ ተጠቃሚዎች መካከል የማታየው የመቻቻል ልምድ በቂና የተሟላ አለመሆኑን

ነው፡፡ለችግሩ መኖር ግንዛቤ ማነስን ጨምሮ ሌሎች መሰል ምክንያቶች ሊኖሩት ቢችልም ዞሮ ዞሮ የመቻቻል ባህሉ አለመኖር በመማር ማስተማሩ ሂደት የራሱን ተጽዕኖ ማሳደሩ አያጠያይቅም፡፡

6(100%) መምህራንም በበኩላቸዉ በቃለምልልስ ለማስረዳት የሞከሩት ተማሪዎችን ጨምሮ በአብዛኛዉ ማህበረሰብ ቀበልኛ አነጋገርን በተመለከተ የሚሰጡት ቦታ (ግምት) ዝቅተኛ እና የማያበረታታ መሆኑን ነዉ፡፡ ይህንን ሃሳብ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸዉ የመስኩ ምሁራንም የሚጋሩት ስለመሆኑ ምእራፍ ሁለት ዉስጥ ከቀረበዉ መረጃ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ጥያቄ12፣ በቀበልኛ ንግግር አጠቃቀም የተነሳ በተማሪዎች መካከል ወይም በተማሪዎችና በመምህራን መካከል ግጭቶች/ አለመግባባቶች/ ተፈጥረው ያውቃሉ? አጋጥሞት ከሆነ አጠር ያለ ማብራሪያ ይሰጡበት የሚል ነበር፡፡

የአማርኛ ቋንቋ ዘያዊ ልዩነቶች ቋንቋውን በማስተማር መማር ሂደት ተጽእኖ የሚፈጥሩበት ሁኔታ መኖሩን ለመፈተሽ ታስቦ የቀረበላቸውን ይህንን ጥያቄ ሲመልሱ ተጠኚዎች የሰጡትን ምላሽ እነሆ፡፡

ሰባት መምህራን(28%)በተሰጠው ክፍት የመልስ መስጫ ቦታ ላይ ምንም አይነት ሀሳብ አላሰፈሩም፡፡፡14 (56%)መምህራን ጥያቄውን በአዎንታ ተቀብለው ያጋጠሙ ችግሮችን ሲያስረዱ ዋናዉ ትኩረታቸዉ የነበረዉ ለማስተማር መማሩ ሂደት እንቅፋት የሚፈጥር ገደብ አልባ ሳቅ የሚፈጠርበትና ተማሪዎችም በዚህ የተነሳ አልፎ አልፎ አላስፈላጊ የቃላት ምልልስ ዉስጥ የሚገቡበት ሁኔታ እንደሚያጋጥም አስገንዝበዋል፡፡ 1(4%) ተጠኚ በበኩላቸዉ በተማሪዎች መካከል አለመግባባት ተፈጥሮ እንደነበረ ገልጸዋል፡፡ ማሳያዎችን ሲያስረዱም የክፍል አቀራረብ /presentation/ ሲያቀርብ ያሰማቸዉ በነበሩ አንዳንድ ቀበልኛ ቃላት ምክንያት ስቀብኛል በሚል ሰበብ አላስፈላጊ ጸያፍ ስድብ በተማሪዎች ፊት ጓደኛዉን የተሳደበ ተማሪ የተመታበት አጋጣሚ መኖሩን ገልጸዋል፡፡ በሌላ በኩል1(4%)ተጠኚ መምህርት ተማሪዎች በአንድ ለአምስት ወይም በሌሎች የቡድን ስራዎች አንዳንዴ ቀበልኛ ተናጋሪዎችን እንደባለገር (ኊላቀር) በመቁጠር በቡድን አባልነት ላለመቀላቀል የሚሞክሩበት ሁኔታ አንድ አቢይ ችግር መሆኑን አስረድተዋል ፡፡

ሌላ 1(4%)መላሽ ደግሞ የጎጃም ዘዬን አብዝተው በሚጠቀሙ አንድ የትምህርት ክፍል አባል መምህር ክፍለ ጊዜያት ዘዬን ምክንያት ያደረጉ ችግሮች አልፎ አልፎ እንደሚከሰቱ ገልጸዋል፡፡ አክለውም አለመግባባቶቹ በአብዛኛው በመምህሩና በተማሪዎች የመጀመሪያ

የግንኙነት (የትውውቅ ጊዜያት) እንደሚታዩም ጠቁመዉ ከተወሰኑ ወራት በኋላ መላመዱ ስለሚጠነክር ችግሮቹ እየቀነሱ እንደሚሄዱም አስረድተዋል፡፡ እኚህ መላሽ መምህር ጓደኛቸዉ ጎጃምኛ ዘዬን በስፋት በመጠቀሙ ምክንያት "ቆምጨው ! ቆምጩው !"ማር! ማር! ማ ር !" እያሉ ተማሪዎች እንደሚጠሩትም ጠቁመዋል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ አንዲት አንስት መምህር በባልንጀራቸዉ ላይ ስላጋጠመ ችግር ሲያስረዱ፦ በሚናገረው ቀበልኛ ዘዬ ምክንያት በየገባበት ክፍል ከተማሪዎች ጋር የሚጋጭ መምህር መኖሩን ጠቅሰው ፤ ከዕለታት አንድ ቀን ስለተፈጠረ ገጠመኝ ተከታዩን ሐሳብ አስፍረዋል፡፡ በዕለቱ ሶስት ሴት ተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ በተደጋጋሚ በመሳቅ ክፍል ረብሸዋል ተብለው በአማርኛ መምህራቸዉ ተከስሰዉ አስተባባሪዎች ቢሮ ተወስደው ሊገረፉ የነበሩ ሶስት ተማሪዎችን ርእሰ መምህሩ ተከላክለዉ ማስለቀቃቸውን አስታዉሳለሁ፡፡ ¨ ብለዋል፡፡እኚሁ መምህርት አክለዉም ተማሪዎቹ ከተለቀቁ በኋላም ር/መ/ሩን ለምን እንደዚያ እንዳደረጉ የፈረቃ አስተባባሪዎቹ ሲጠይቋቸው "ራሱ እየረበሸ ታዲያ እንዴት ይሁን?" በማለት የመምህሩ ቀበልኛ አነጋገር በተደጋጋሚ ለችግሩ መንስኤ እየሆነ መቸገራቸውን በምሬት የገለፁበትን አጋጣሚ እንደሚያስታዉሱ ገልጸዋል፡፡

በሌላ በኩል የቃለ ምልልስ ተሳታፊዎቸም በዚህ ጥያቄ ላይ ምላሽ እንዲሰጡበት ተደረጓል ፡፡ በመሆኑም ከስድስቱ ተጠኚዎቸ መካከል 4(66.7%) መላሾች ዘዬን ምክንያት ባደረገ ሁኔታ የተፈጠረ አለመግባባት አላጋጠመንም ብለዉ መልሰዋል፡በአንጻሩ 2(33.3%)መምህራን ደግሞ ችግሩ ያጋጠማቸዉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡አንደኛዉ መምህር አለመግባባት አኒዲፈጠር ምክንያት የነበረዉ ቃል" ኮረጆ" የሚል ሲሆን መምህሩ "ቦርሳ" ለማለት ፈልገዉ ኮረጆ ሲሉ በመደመጣቸዉ ተማሪዎች ስለሳቁባቸዉ ተበሳጭተዉ ለድብድብ መጋበዛቸዉን አስረድተዋል፡፡ ሁለተኛዉ ተጠኚ መምህርም እንዲሁ የጎጃም ዘዬን በብዛት የሚጠቀም የትምህርት ክፍል አባላቸዉ ብዙ ጊዜ በዚሁ በቀበልኛ ንግግር ምክንያት ተጣልቶ እንደሚመጣ ገልጸዋል፡፡

ጥያቄ 13፣ተማሪዎቸ እነሱ ከሚናገሩት ዘዬ ወይም ቀበልኛ ዉጭ ሌሎቸ የሚናገሩትን ለማድመጥ ምን ያህል ፈቃደኛ ናቸዉ?

ሀ. ሁልግዜ ለ. አልፎ አልፎ ሐ. ፈቃደኝነት አይታይባቸዉም የሚል ጥያቄ ተጠይቀዋል፡፡ የቋንቋዉን የተለያዩ ዘዬዎች በሚናገሩ ተማሪዎች መካከል ምን ያህል መደማመጥና መከባበር እንዳለ ለማወቅ ተፈልጎ የቀረበዉን ይህንን ጥያቄ ሲመልሱ 13 (52%) መላሾች ሁልጊዜ የሚለዉን መርጠዋል፡፡ 7(28%)መላሾች ደግሞ አልፎ አልፎ የሚል መልስ

ሰጥተዋል፡ ፡ ቀሪዎቹ 5(20%)መምህራን ደግሞ ተማሪዎቹ እርስ በርስ ለመደማመጥ ፈቃደኝነት አይታይባቸዉም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ከላይ የቀረበዉ የተጠኝዎች ምላሽ እንደሚያመለክተዉ ተማሪዎቹ ብዙም የመደማመጥ ችግር የሌለባቸዉ መሆኑን ነዉ፡፡ብዛት ያላቸዉ መምህራን የመረጡት ሁልጊዜ የሚለዉን አማራጭ መልስ በመሆኑ ችግሩ በተማሪዎች ዘንድ ጎልቶ የታዬ እንዳልሆነ የቀረበዉ ምላሽ ያመለክታል፡፡ፈቃደኞች አይደሉም ብለዉ መልስ የሰጡ መምህራን ቁጥራቸዉ ጥቂት (5)ነዉ ስለዚህ ከጠቅላላ ዉ የተጠኝዎች ቁጥር አንጻር ሲታይ የችግሩን ስፋት አያመላክትም፡፡

ጥያቄ 14፣ አንዳንድ ወገኖች ስለቀበልኛ ቋንቋ አጠቃቀም አሉታዊ አመለካከት የሚያሳዩት ለምን ይመስልዎታል?

መምህራኑ ይህንን ጥያቄ የመለሱት ዋናዋና ያሏቸዉን ተከታዮቹን ነጥቦች በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ በማስፈር ነዉ፡፡እነዚህም የዕዉቀት /ግንዛቤ/ማነስ፣ራስን ዘመነኛ አደርጎ ለማሳየት ካለ ፍላጎት፣በሌሎች ፖለቲከዊ፣ኢኮኖሚየዊ፣እና ማህበራዊ ልዩነቶች የተነሳ ፣ባህላዊ ነገሮችን ለማዘመን ካለ ጽኑ ፍላጎት ፣ጥላቻን ከቤተሰብ ወይም ከማህበረሰብ በመዉረስ፣በሌሎች ግፊት በመነዳት፣ካልተማሩ ወገኖች የቋንቋ አጠቃቀም ስልት በልጦ /ልቆ/ለመገኘት ፣ እንደ" ፋራ" ላለመቆጠር የሚሉት በኣብዛኛዎቹ መምህራን በአንድም በሌላ መልኩ የተጠቀሱ ሃሳቦች ናቸው፡፡

ከቀረበዉ ምላሽ መገንዘብ የሚቻለዉ ሰዎች ቀበልኛ ንግግርን ሲሰሙ ለተናጋሪዎቹ የሚሰጡት ግምት አበረታች አለመሆኑን ነዉ ፡፡የችግሩን ምንጭ ስንመረምር ደግሞ አሉታዊ አመለካከት እንዲኖር ያደረጉ ምክንያቶች በአመዛኙ ከቋንቋ ሳይንስ ጋር ግንገኙነት የሌላቸዉ ዉጫዊ ምክንያቶቸ ናቸዉ፡፡ ምክንያቶቹ በዚህ ጥናት በምዕራፍ ሁለት የመስኩ ምሁራን ለአብነትም Lado (1964) ፣ Holmes (1992) ካሰፈሩዋቸዉ ነጥቦች ጋር ተወራራሽነት አላቸዉ ፡፡ይሄዉም ካለማወቅና ከግንዛቤ አጥረት የመነጩ ናቸዉ የሚለዉን ሀሳብ የሚያመላክቱ ናቸዉ፡፡

በዚህ ጥያቄ ላይ ቃለምልልስ ካደረጉ መምህራን የተገኘዉ ምላሽ የሚያሳየዉም ይህንኑ ከፍ ሲል የተመለከትነዉን እዉነታ ነዉ ፡፡ ይሄዉም በግንዛቤ አጥረት አብዛኛዉ ማህበረሰብ የቋንቋዎችን ስነልሳናዊ ባህርይ ባለመገንዘብ ዘዬዎችን አበላልጦ የመመልከት ፣የራስን ከፍ፤ የሌሎችን ደግሞ ዝቅ አድርጎ የመመልከት ችግር እንደሚያሳይ 6(100%) ተጠኚ መምህራን በቃለምልልሱ አስረድተዋል፡፡

ተማሪዎችም በበኩላቸዉ አንዳንድ ወገኖች ለቀበልኛ አነጋገር ያላቸዉ አመለካከት የተዛባ መሆኑን በቡድን ባካሄዱት ዉይይት አስረድተዋል ።የዉይይታቸዉ አጠቃላይ ሀተታ ቀበልኛ ንግግር ላይ ያለዉ ማህበረሰባዊ አይታ መስተካከል የሚገባዉ መሆኑን በአጽንኦት ያመላከተ ነዉ።(በዝርዝር የቀረበዉን ሀተታ ከአባሪ ገጽ ይመለከቷል።)

ጥያቄ 15፣ የአማርኛ ቀበልኛ ዘዬ ተጠቃሚ የሆኑ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች የሚያሳዩአቸዉ የአጠቃቀም ልዩነቶች ከድምጽ፣ከቃል፣ ከምዕላድ አኳያ ምንምን ናቸዉ ማለት ይቻላል በምሳሌዎች አስደግፌዉ ቢያብራሩልኝ? በሚል የቀረበላቸዉን ጥያቄ ሲመልሱ መምህራንና ተማሪዎች ያቀረቡአቸዉ ምላሾች ብዛት አላቸዉ።። ሆኖም ከጥናቱ ዓላማ አንጻር ተገቢነት ያላቸዉን ብቻ አጥኚዉ ለይቶ እንደሚከተለዉ አቅርቧቸዋል።

መደበኛ አጠቃቀም	**ቀበልኛ/ ዘያዊ/ አጠቃቀም**
ይጎዳሀል /ይገጭሀል	ይገድልሀል
መቀስ	መቁረጫት
ችቦ	ዳቦት
ቃሪያ	ቁጦ
ስኒ	ፍንጃል
ዞርበል	ወግድ/ ክላ
እንደገና	እንደገን
ላርመዉ	ልረመዉ
ምጣድ	ምጎጎ
ይህ	ይሃ
ባቄላ	ባኤላ
እንግዲህ	እንግድህ
ጌታዬ	ጄታዬ
አቅም	አዕም
ዱቄት	ዱጨት

ወረቀት	ወረኸት
ቆለምሸሽ	ሞሰብ
ዝቃቅቤ	በሶቢላ
ፈላና	ጭልፋ
ምሽት	ምሽት

ከፍ ሲል የቀረቡት ዘያዊ ቃላት ከመደበኛዉ አጠቃቀም የሚነጥል የፍች ልዩነቶች የሚታይባቸዉ ናቸዉ፡፡ቀጥሎ የተጠቀሱት ደግሞ ከቦታ ቅየራና ከቃላት ፍች አንጻር የሚታይ ልዩነት ያሳያሉ፡፡

በቀበልኛው አጠቃቀም	**በመደበኛው አጠቃቀም**
ጠሀዉ ቅንጭላት ይበሳል ፡፡	(ጸሀዩ በጣም ያቃጥላል ለማለት)
ቅንጭላቱ ላይ ገመሰዉ	(ጭንቅላቱን ፈነከተዉ)
፡መጽሀፉን በኮረጆህ ክተተዉ	(…በቦርሳህ አስገባዉ)
ያበሻ ተማሪ ሳለሁ	የቆሎ ተማሪ በነበረኩበት ጊዜ
ከበሮ	ከረቦ
ዝንጅብል	ጅንጅብል
¨አዉቶብሱ ላይ ሰቀለኝ	አሳፈረኝ

በአጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የቋንቋዉ አጠቃቀም ገጽታዎች የሚያሳዩት በአማርኛ ቋንቋ ቀበልኛ አጠቃቀሞች የድምጽ፣ የምዕላድና የቃላት ፍች ልዩነቶችን የሚታይባቸዉ መሆኑን ነዉ፡፡

16 መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ዉስጥ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር በማስተማር መማሩ ሂደት የሚኖሯቸዉ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎችን እንዲጠቅሱ ተጠይቀዉ እንደሚከተለዉ መልስ ሰጥተዋል፦

በአዎንታዊ ተጽዕኖ ረገድ የተነሱ ነጥቦችን ስንመለከት ማህበራዊነትን የመፍጠር፣ አንዱ የሌላዉን ብሂል እንዲያዉቅ እንዲገነዘብ ተጋልጦ የመፍጠር ሚና አላቸዉ፡፡ የሚል ሃሳብና

በአንድ አካባቢ ለቁሳቀቁስ የሚሰጠዉ ስያሜ በሌላ አካባቢ ከተሰጠዉ የተለዬ መሆኑን ተማሪዉ ሲገነዘብ የቋንቋን ዘፈቀዳዊነት ባህርይ፣ እንዲሁም የቋንቋን የተለዋዋጭነት ባህርይ ይረዳበታል ፤ይማርበታል በሚል የቀረበ ምላሽ አለ፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ዘዬዎች መኖር ስነጽሁፍን ለማስተማር የጎላ ጠቀሜታ አላቸዉ የሚል ሃሳብም ተጠቅሷል ፡፡የቀረበዉ ምሳሌም የተለያዩ ዘዬዎችን የሚናገሩ ገጸባህርያትን በመጠቀም የፈጠራ ድርሰቶችን ጭብጦች ለመጠቆም እንዲሁም መቸቶችን ለመግለጽ ጠቀሜታ እንዳላቸዉ ተጠቅሷል፡፡በሌላ በኩል ዘያዊ አነጋገሮች በንግግራዊ የቋንቋ ተግባቦት ያላቸዉ ሚናም መዘንጋት የለበትም የሚሉ ምላሾች በጠቀሜታ ጎን ተጠቅሰዋል፡፡ በአንጻሩ አሉታዊ ጎናቸዉን በተመለከተ ከፍ ሲል በተለያዩ ጥያቀዎች መነሻ ለማስረዳት ከሞከሩባቸዉ ሃሳቦች የተለዩ ምላሾቸ አልቀረቡም፡፡ የተዘረዘሩት ሃሳቦች የሚያትቱት ተናጋሪዎቻቸዉን እንዳልሰለጠኑ (መደበኛ ዘዬን መናገር እንደማይችሉ) ስለሚያስቆጥሯቸዉ ተማሪዎቸ በነጻነት በክፍል ዉስጥ ሃሳብ እንዳያንሸራሽሩ ቀበልኛ ዘዬዎቻቸዉ ምክንያት ይሆኑባቸዋል ፤በመምህራንና በተማሪዎች መካከል አልፎ አልፎ ለሚፈጠር መናናቅ ወይም አለመግባባት ምክንያት ሆነዉ ይታያሉ የሚል መልዕክት ያላቸዉ ሀሳቦች ተጠቅሰዋል፡፡¨

4.2. ከተማሪዎች የቡድን ውይይትና ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች

በዚህ ጥናት ተማሪዎችም አንድ የመረጃ ምንጭ ናቸዉ፡፡ስለሆነም በዚህ የቡድን ውይይት የተካፈሉ ተማሪዎች የተሻለ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው በአማርኛ መምህሮቻቸው የተመረጡና የአማርኛ ቋንቋ ቀበልኛ ዘዬ ተናጋሪ ናቸው ተብለው የታመነባቸው ናቸው፡፡፡በዚህ አግባብ የተመረጡት ተማሪዎች እንዲወያዩባቸው የተደራጁ ስድስት ነጥቦች ሲሆኑ በነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ከተካሄደዉ ዉይይት የተገኙ ሀሳቦችም እንደሚከተለው ተጨምቀው ቀርበዋል፡፡

የመወያያ ነጥብ 1 ፣ ብዙውን ጊዜ ቋንቋና ዘዬ ሲባል ትሰማላችሁ ለመሆኑ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ሀሳቦች የተነሱ ሲሆን ከነዚህም መካከል አብዛኛዎቹ ጽንሰ ሐሳቡን በተዛባ ሁኔታ መረዳታቸውን የሚያመላክቱ ሆነዉ ተገኝተዋል፡፡ ለአብነትም ዘዬን ከዘይቤ ጋር አመሳስሎ ትንታኔ የመስጠት ሁኔታ በሰፊዉ ታይቷል፡፡ ይሄዉም የዘዬን ምንነት ሲያስረዱ ”ዘዬ በቋንቋዉ ዉስጥ የሚያገለግልግል፣ የቋንቋውን አጠቃቀም ለማሻሻል የሚረዳ ፣በአነፃፃሪ፣ በተለዋጭ ወይም በሰውኛ ዘይቤ ስልት የሚቀርብ አነጋገር ነው፤ ስለሆነም የቋንቋ አንድ ንዑስ ክፍል ተደርጎ ሊታይ የሚችል ነው ”ብለዉታል፡፡በሌላ በኩል

ቋንቋ የዘይቤዎች የፈሊጣዊ አነጋገሮች ወዘተ ስብስብ ነው በሚል የገለጹት ሃሳብም ይገኛል ። እንዲሁም መደበኛዉ ቋንቋ በውስጡ ዘዬን የሚይዝ ሲሆን፣ ዘዬ ግን ቋንቋን ሊያካትት አይችልም። ቋንቋ የሚባለው በጽሁፍና በንግግር የሚቀርበው ሲሆን ዘዬ የሚባለው በንግግር ብቻ የሚያገለግል ነው። ቋንቋ የተማሩ ሰዎችና የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ያላቸዉ ሰዎች የሚጠቀሙበት ሲሆን፣ ዘዬ ግን ያልተማሩ ሰዎች በተለይም ባላገሮች የሚጠቀሙበት ነው የሚሉ ምላሾችን አስፍረዋል።

ለመጀመሪያዉ የመወያያ ጥያቄ ከሰጡት ምላሽ እንደምንመለከተዉ በዘዬና በቋንቋ መካከል ያለውን ልዩነት በውል የተገነዘቡት አለመሆኑን ከገለፃቸዉ መገንዘብ ይቻላል። ከዚህም በተጨማሪ ዘዬ ያልተማሩ ወገኖች በሚናገሩበት ጊዜ የሚከሰት ነው ሚል ሀሳብ የተጠቀሰበት ሁኔታ አለ።

በአጠቃላይ ተወያዮቹ ያቀረቡት መልስ የሚያመለክተዉ ጥቂት የማይባሉ ተማሪዎች ስለዘዬ በቂ ግንዛቤ የሌላቸዉ መሆኑን ነዉ። ለዚህ አይነቱ ክፍተት መፈጠር የተለያዩ ችግሮች ሊኖሩ ቢችሉም የዚህ ጥናት አቅራቢ እንደታዘበዉ ከሆነ ችግሩ መምህራን ተማሪዎቻቸዉን ስለዘዬ በበቂ ሁኔታ ስለማያስተምሩ ነዉ። ይኸውም በጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ ከ7ኛ-12ኛ ክፍል ባሉ የክፍል ደረጃዎች በተማሪው መማሪያ መጻህፍትም ሆነ በመምህሩ መምሪያ ውስጥ ስለዘዬ ተማሪዎቹ ግንዛቤ እንዲያገኙ የሚጋብዙ ይዘቶች አልተካተቱም ቢባል ማጋነን አይሆንም ። ምክንያቱም በሰነድ ፍተሻ ከተዳሰሱት ከ7ኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል በሚገኙ የተማሪው መማሪያ መጻህፍትና አንዲሁም በመምህሩ መምሪያዎች ውስጥ በ11ኛ ክፍል አማርኛ መጽሐፍ ውስጥ ገጽ 82 ከአንድ አጭር ቴክስት ውስጥ ዘዬ መጥ ቃላትንና የሚነገሩበትን አካባቢ እንዲገልፅ የሚያዝዝ መልመጃ ተካቶ ይገኛል። የመልመጃው ይዘት የሚከተለውን ሰንጠረዥ አሟሉ የሚ ል ነው ።

ተ/ቁ	ዘዬ መጥ ቃላት	የሚነገርበት አካባቢ	አቻ ቃል

ከዚህ መልመጃ ባሻገር ሌሎች ዘዬን የሚመለከቱ ርእሰ ጉዳዮች ተካትተዉ የተገኙበት ሁኔታ የለም፡፡ በሌላ በኩል በ12ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ስለዘዬና ቋንቋ ምንነት የሚያስረዳ ርዕሰ ጉዳይ በምንባብ መልክ በምዕራፍ አንድ ላይ (ገፅ 3-4) ቀርቧል፡፡ከነዚህ ሁለት ይዘቶች ውጪ ለተማሪዎችም ሆነ እግረ መንገዱን ለመምህራንም የግንዛቤ ማሳደጊያ መሆን የሚችሉ ቀበልኛ የቋንቋ አጠቃቀሞች የታቀዱበት ሁኔታ የለም፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ በቋንቋዎች መካከል ስለሚታየው ሳይንሳዊ የቋንቋ ልዩልዩ አጠቃቀሞች (ዘዬን) ጨምሮ የሚኖራቸው ግንዛቤ አናሳ ስለሚሆን በአጠቃቀም ረገድ በሚታዩ ልዩነቶች ላይ ሊፈጠር የሚችልን ልዩነት በጸጋ ተቀብሎ በመቻቻል ለመረዳዳትና ለመደጋገፍ የሚያደርጉትን ጥረት እንዳይሰምር ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም ተማሪዎችም መምህራኑም ስለዘዬ የሚኖራቸው ግንዛቤ ይሰፋ ዘንድ፣ ሰፋ ባለሁኔታ በመማሪያ መጽሀፎቹ ውስጥ ቀበልኛ ዘዬንና ሌሎች የቋንቋ ለዉጦችንም የተመለከቱ ይዘቶች በበቂ ሁኔታ ቢካተቱና ተማሪዎቹም የተሻለ ተጋልጦ ቢያገኙ ወደመደበኛ ዘዬ ተጠቃሚነት እስኪሸጋገሩ ባላቸው ነገር እየታገዙ (እየተጠቀሙ) ዉጤታማ እንዲሆኑ የሚረዳቸው ይሆናል፡፡ የመደበኛ ዘዬ ተጠቃሚዎቹም ቀበልኛ የቋንቋ አጠቃቀሞችን እንደ አለመታደልና ኋላቀርነት አይነት ዕጣፋንታዎች ያመጧቸው መስለዉ እንዳይታያቸው የሚያስችል ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡

በሌላ በኩል በሰነድ ፍተሻው ተማሪዎችና መምህራን የአማርኛ ቋንቋ ዘዬዎችን በማስታወሻ ደብተራቸው እንዲሁም በመደበኛ መማሪያ ደብተራቸው ውስጥ በጻፏቸው ጽሁፎች ውስጥ ቀበልኛ ቃላትን፣ ሃረጋትን ወይም አረፍተ ነገሮችን መጠቀማቸውን ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡ ለዚህ ተግባር ከተሰበሰቡ አስራ አንድ የመምህራን ማስታወሻ ደብተሮች መካከል በአራቱ ውስጥ ብቻ የተወሰኑ ቀበልኛ አጠቃቀሞች ታይተዋል፡፡ እነዚህም ተከታዮቹ ናቸው፡፡

(እንግድህ፣ ይለዋልኝ፣ እነዝህ ብቻ ናቸው እንዴ?፣አጭር ልቦለዲ፣ በቤሳ ቆረጠው ፣" የመ ፃፊያ ጊዜና ቦታ ምርጫን በተመለከተ ከግለሰብ ግለሰብ ሊለያይ ይችላል ፤ለምሳሌ "ምሽት" ላይ መፃፍ ሊመቸዉ ይችላል" …፣እንደገን፣ እረሙት ፣ፊታፊት ፣ የሚሉት ይገኙበታል፡፡ ከ25 ተጠኚ መምህራን መካከል ፈቃደኛ ሆነው የማስታወሻ ደብተር አለን ብለው ለሰነድ ፍተሻው መልካም ትብብር ያደረጉት 11 ብቻ ነበሩ፡፡ ከእነዚህ መካከል በአራቱ ቀበልኛ የቋንቋ አጠቃቀም የታየባቸው መሆኑ ታውቋል፡፡ እነዚህም ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው ዘዬዎቹ በጎጃምና በወሎና በጎንደር ቀበልኛዎች ውስጥ ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ከተማሪዎች ከተሰበሰቡ ደብተሮች ውስጥ ቀበልኛ አጠቃቀም የታየባቸውን በቂ ማሳያዎችን ማግኘት አልተቻለም፡፡ በአስራ አንደኛና በአስራ ሁለተኛ ክፍል የተማሪዉ

መማሪያ መጻህፍት ዉስጥ ስለዘዬ በስሱ የቀረቡ መልመጃዎች ሳይቀር በተማሪዎች ደብተር ዉስጥ አልሰፈረም፡፡ይህ ደግሞ መምህራን ስለቀበልኛ ዘዬ ለማስተማር ያላቸዉ ፍላጎት አናሳ መሆኑን አመላካች ነዉ፡፡ በአጠቃይ ለዚህ ጥናት በተለዩ የክፍል ደረጃዎች ቀበልኛ አጠቃቀሞች የደረጃዉን ተማሪዎች ግንዛቤ ለማስጨበጥ በሚያስችል ሁኔታ ተካትተዉ እንደሚገኙ የተጠበቀ ቢሆንም በተጨባጭ የታየው ግን በተቃራኒው ነዉ፡፡ በሌላ በኩል ቀበልኛ ተናጋሪ የሆኑ ተማሪዎችም በደብተራቸዉ ዉስጥ በተጠቀሙት ቋንቋ ዉስጥ ቀበልኛ ቃላትና ሀረጋትን ብዙም አልተጠቀሟቸዉም፡፡ይህ መሆኑ ደግሞ ምናልባትም ቀበልኛ አጠቃቀሞች በአመዛኙ ከጽሁፈት ይልቅ በንግግር ጊዜ በስፋት አገልግሎት ላይ ሊዉሉ እንደሚችሉ ለማጤን የሚጋብዝ ነዉ፡፡በሌላ በኩል በተማሪዎች ደብተር ውስጥ ቀበልኛ አጠቃቀሞች በስፋት ያለመገኘታቸው ምስጢር በአብዛኛው የሚጽፏቸው ጽሁፎች ከመጽሐፍ ቀጥታ የሚገለበጡ በመሆናቸዉና እንዲሁም ከመምህራኑ የሰሌዳ ላይ ጽሁፎች የሚገለበጡ በመሆናቸው ሳይሆን እንደማይቀርም ተገምቷል፡፡ የሆነ ሆኖ ይነስም ይብዛም አንዳንድ ዘያዊ ቃላትን በአረፍተ ነገሮቻቸዉ ዉስጥ ማግኘት ተችሏል፡፡እነዚህም፦ ልጅቱ" አለይ "?፣ ጠሀዩ "ቅንጭላት" ይበሳል፣"ዳቦት" አንዱ የሰዉ ሰራሽ ብርሃን ምንጭ ነዉ ፣አባቴ በማይኖር ጊዜ እንጀራ እናቴን ስለምፈራት የማመሽዉ "እዳሪ" ነበር፡፡

የመወያያ ነጥብ 2 ፣ በመደበኛ ዘዬና በቀበልኛ ንግግር መካከል ያለውን ልዩነት አስረዱ በሚል የቀረበ ጥያቄ ነበር፡፡ ይህንንም ሲያስረዱ እንደገለጹት መደበኛ ዘዬ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሲሆን ቀበልኛዉ ደግሞ በደንብ ያልታወቀ ቋንቋ ነው ፤መደበኛ ዘዬ ብዙ ተናጋሪዎች ያሉት ቋንቋ ሲሆን፣ ቀበልኛው ደግሞ ተናጋሪዎቹ አነስተኛ የሆኑ ናቸው፡፡፡ መደበኛ ዘዬ በከተሞች አካባቢ የሚነገር ቋንቋ ማለት ነው፡ በማለት ያላቸውን ግንዛቤ ለማስረዳት ሞክረዋል፡፡

ከቀረበው ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው ተማሪዎቹ እንደ ቋንቋ ተማሪነታቸው ሁለቱን ጽንሰ ሀሳቦች ጠንቅቀው መገንዘብና ማስረዳት መቻል ያለባቸው ቢሆንም በተጨባጭ ማየት የተቻለዉ ግን በቂ ግንዛቤ የሌላቸው መሆናቸዉን ነው፡፡

የሰነድ ፍተሻው ካተኮረባቸው ነጥቦች መካከል መምህራን ተማሪዎቻቸውን ስለዘዬ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ያዘጋጇቸዉ የተወሰኑ ይዘቶች በማስታወሻ ደብተሮቻቸው ላይ መገኘታቸውን ነበር፡፡ ሆኖም ለፍተሻ በተሰበሰቡት የመምህራን ማስታወሻ ደብተሮች ውስጥ የተጻፈ ነገር አልተገኘም፡፡ ከዚህም የምንረዳው ተማሪዎች ቋንቋውን ሲማሩ ቋንቋው ውስጥ ስላሉ ቀበልኛ አጠቃቀሞቸ የሚሰጧቸው ገለጻ /ማብራሪያ አለመኖሩን ነው፡፡ በሌላ በኩል ይህንኑ ጉዳይ ለመፈተሽ የተማሪዎችን መማሪያ መፃህፍት ከ7ኛ-12ኛ ክፍል ይዘቶችን ለመፈተሽ

በተሞከረበት አጋጣሚ 11ኛ እና 12ኛ ክፍል ላይ የአንድ ክፍለ ጊዜ ትምህርት ሊሸፍን በሚችል ሁኔታ ዘዬን የሚመለከቱ ርዕሰ ጉዳዮች መካተታቸው ተረጋግጧል፡፡ የሆነ ሆኖ መምህራን ትኩረት ሰጥተው ትምህርቱን በተማሪዎቸ ዘንድ እንዲሰርጽ ለማድረግ የማይሞክሩ ከሆነ በመጽሐፍ ላይ መካተቱ ብቻ በቂ ሊሆን አይችልም፡፡ ይህም በመሆኑ ይመስላል ተማሪዎች የሚጠበቀዉን ግንዛቤ አሟልተው ሊገኙ ያልቻሉት፡፡

Murphy (2012፣ 5-8) እንዳቀረቡት ሀተታ ከሆነ ተማሪዎችን ስለዘዬ በቂ ግንዛቤ ማስጨበጥ በቀበልኛ ንግግር እና በመደበኛ ዘዬ አጠቃቀም ላይ የጎላ የመቻቻል ዝንባሌን እንዲያዳብሩ ያግዛቸዋል፤ በአንጻሩ በቂ ግንዛቤ የማይፈጠርላቸዉ ከሆነ ከመምህራን ጋርም ይሁን ከጓደኞቻቸዉ ጋር በጉዳዩ ላይ አለመግባባትና አለመረዳዳት ሊፈጠር ይችላል፡፡ በዚህ ጥናት ለመምህራን ለቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ የተሰጠው ምላሽ ያመለክተውም ይህንኑ ሀቅ ነው፡፡እንደ መምህራኑ ገለጻና ማብራሪያ የተለያዩ ቀበልኛዎችን በሚናገሩ መምህራንና ተማሪዎች መካከል አለመግባባቶች ተከስተው ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው እስከ መባረር ደረጃ የደረሱበት ሁኔታ ተስተዉሏል፡፡

መወያያ ነጥብ 3፣ ከጎጃም፣ ከጎንደር፣ ከወሎ፣ ከሸዋና ከአዲስ አበባ የአማርኛ ቋንቋ ዘያዊ አጠቃቀሞች መካከል የትኛው ዘዬ ደስ ይላል? ወይም ክብር አለው? ለምን? በሚል ለቀረበላቸው የመወያያ ጥያቄ እንደሚከተለው መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከተዘረዘሩት ሁሉ የሚሻለውና ክብር ያለው የአዲስ አበባው ነው በማለት መልሰዋል፡፡ ለምን እንደሚሻል እንዲያስረዱ በተጠየቁት መሰረትም የአዲስ አበባ የአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀም የተስተካከለ በመሆኑ፣ የሰለጠነ ማህበረሰብ የሚጠቀምበት እና በከተማ አካባቢ የሚነገር በመሆኑ የተሻለ እንደሆነ ለማስረዳት ሞክረዋል፡፡

ከዚህ የምንገነዘበው ነገር ቢኖር በማወቅም ይሁን ባለማወቅ መደበኛውን ዘዬ የማስቀደምና ከዚህ ዉጭ ያሉትን የማጣጣል አዝማሚያ(ዝንባሌ) መኖሩን ነው፡፡ የዚህ አይነት ዝንባሌ ደግሞ የቅርብ ጊዜ ገጠመኝ ብቻ ሳይሆን የዋለ ያደረ መሆኑን የመስኩ ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡ለአብነትም Zealem(2007፣2-3)ለአዲስ አበባ ዘዬ የተሻለ ሰፊ ቦታ የመስጠቱ ዝንባሌ የተጀመረው በ1884 ዓ/ም አዲስ አበባ የኢትዮጵ ዋና ከተማ ሆና ከተቆረቆረችበት ጊዜ ጀምሮ እንደነበር አስገንዝበዋል፡፡አክለውም ይህንን ተከትሎም የአዲስ አበባው የአማርኛ ቋንቋ ዘዬ ለመገናኛ ብዙሃን ለትምህርትና ለሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ

ድርጅቶች መገልገያ ሆኖ መቀጠሉ ከሌሎች የአማርኛ ቋንቋ የአጠቃቀም ልዩነቶች በተለዩ የላቀ ሆኖ እንዲታይ አድርጎታል የሚል ሀተታ አቅርበዋል፡፡

መወያያ ነጥብ 4፣ የአማርኛ ቋንቋን የተለያዩ ዘዬዎች የሚናገሩ ተማሪዎች በአንድ ላይ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት ቋንቋዉን በመማር ማስተማር ሂደት ሊኖሩት የሚችሉ አሉታዊ ጎኖች ምንምናቸው?

- በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ሐሳቦች የተሰነዘሩ ሲሆን ዋና ዋና ናቸው በሚል የተመረጡት የሚከተሉት ናቸው፡፡
- የትምህርት አቀባበል ልዩነትን ያስከትላል ስለሆነም ለተማሪዎች ለራሳቸውም ሆነ ለመምህራን የስራ ጫናን ያስከትላል ብለዋል ፡፡
- በሚናገሯቸው ዘዬዎች መለያየት ምክንያት መናናቅ ወይም አለመከባበር ተፈጥሮ ግጭት ውስጥ የሚገባበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡
- መደበኛውን ዘዬ ለማስተማር ጥረት ለሚያደርጉ መምህራን የተማሪዎችን ውጤት ለማረምና ውጤት ለመስጠት ያስቸግራል፤ ምክንያቱም ተማሪዎቹ የሚጠቀሙት ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎችን ያካተተ በመሆኑ ነዉ የሚል ሃሳብም ሰንዝረዋል፡፡
- እንግዳ/ ያልተለመዱ ድምጾችን፣ ቃላትን፣ ሃረጋትን በቀበልኛ የቋንቋ አጠቃቀማቸው ስለሚጠቀሙባቸው እነዚህን ለማረምና ለማስተካከል መምህራን ስራ ስለሚበዛባቸው ማስተማር መማሩን አሰልቺ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ለመምህራን መደበኛውን አጠቃቀም ከኢመደበኛው አጠቃቀም ለይቶ ማስተካከያና እርማት ለመስጠት ስራ ጫና ይፈጥራል፡፡
- ቀበልኛ ተናጋሪ የሆኑ ተማሪዎች በሚያሰሟቸው አንዳንድ ንግግሮች መምህራንና ሌሎች ተማሪዎች ሲስቁ የተናጋሪዎቹ ሞራል ሊነካ ስለሚችል በትምህርት አቀባበላቸው ላይ ጫና ያስከትላል ፡፡
- ቀበልኛ ዘዬ ተጠቃሚዎች በቁጥር ትንሽ በመሆናቸዉ ቀበልኛ በማይጠቀሙት ብዙ ቁጥር ባላቸዉ ተናጋሪዎች ይዋጣሉ ቀበልኛ ዘያቸዉ ጥሩ ተናጋሪ እንዳልሆኑ ያስመስላቸዋል የሚሉት ምላሾች ዋናዋናዎቹ ናቸዉ ፡፡

እንደተባለውም የተለያዩ የአንድ ቋንቋ ዘዬዎችን የሚናገሩ ተማሪዎችን ለማስተማር በሚደረገው ሙከራ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ የተለያዩ ችግሮች ማጋጠማቸዉ የማይቀር ስለመሆኑ በመስኩ ላይ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ያስገነዝባሉ።እንደ Hofstetter (2003) ሀተታ ዘያዊ ልዩነት አንዱ በተማሪዎች ምዘና ተግባር ላይ የክፍተት ምንጭ (Source of measurement error)ነዉ።Snell.& Andrews (2014) በበኩላቸው ዘያዊ ልዩነት የንባብና የጸህፈት ክሂሎችን ለማሳደግ በሚደረገው ሙከራ ላይከሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች አንዱ መሆኑን አስረድተዋል።

በአጠቃላይ ከተጠኚ ተማሪዎች የተገኘው መረጃም ሆነ በመስኩ ጥናት ካደረጉ ምሁራን መጣጥፎች የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው ዘያዊ ልዩነት ቋንቋን በማስተማር መማር ሂደት ላይ የራሱ የሆኑ ተፅዕኖዎችን ሊያሳድር የመቻሉን ጉዳይ ነው።

መወያያ ነጥብ 5፣ አንዳንድ ወገኖች ለቀበልኛ ንግግር ያላቸው አመለካከት የተዛባና ሚዛናዊነት የጎደለው ሆኖ ይታያል። ይህ አይነቱ አመለካከት ከምን የሚመነጭ ይመስላችኋል? ለተጠኚ መምህራን በቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ ውስጥ ስድስተኛው ጥያቄ መምህራንና ተማሪዎች በቀበልኛ የቋንቋ አጠቃቀም ላይ ያላቸውን አመለካከት እንዲያስረዱ ተጠይቀው ነበር። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መምህራን አሉታዊ አመለካከት እንዳላቸው ገልጸዋል ።በተመሳሳይ መልኩ ተማሪዎችም በአመዛኙ ቀበልኛ አጠቃቀምን በበጎ ጎን እንደማይመለከቱት ይልቁንም የባላገርነት መገለጫ አድርገው እንደሚቆጥሩት አስረድተዋል።

በዚህ ለውይይት በቀረበው ጥያቄ ላይ ደግሞ ለመሆኑ የተዛባ አመለካከት እንዲኖር የሚያደርጉ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? በሚል የቀረበላቸውን ጥያቄ ተማሪዎች መልስ ሰጥተውበታል፡በተወያዮቹ፡ ከተዘረዘሩት ነጥቦች መካከል የተሻሉ ናቸው በሚል በአጥኚው አማካኝነት ተከታዮቹ ሀሳቦች ተለይተው ቀርበዋል።

- ጎሰኝነት በሁሉም ጉዳዮቻችን ላይ ስለሚንጸባረቅ ነዉ፣
- ብዙውን ጊዜ ሰዎች የራሳቸው የሆነን ነገር ስለሚያስበልጡ ፣
- የግንዛቤ /ዕውቀት/ ማ ነስ ችግር መኖሩ ነዉ ፣
- ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና የመሳሰሉት ልዩነቶችን መ ነሻ በማድረግ ፣
- በጋዜጦች፣ በመጽሔቶች፣ በሬዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ላይ የዋሉ ቋንቋዎችንና ዘዬዎችን ከፍ የማድረግና የተሻለ ግምት ከመስጠት የሚመጣ ነዉ ፣

- ከአካባቢ ወይም ከማህበረሰብ ጋር በሚፈጠር ቅራኔ የተነሳ በዘዬዎች አልፎም በቋንቋዎች እኩልነትነት ላይ አለመተማመን ሊከሰት በመቻሉ ነው። የሚሉት ዋናዋናዎቹ ናቸዉ ።ተጠኚዎቹ ካቀረቧቸው ነጥቦች መገንዘብ እንደሚቻለው በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ዘዬዎችን በሚጠቀሙ ማህበረሰቦች መካከል የተለያዩ ልዩነትን ግጭትን አለመግባባትን ሊከሰቱ የሚችሉ ብዙ ውጫዊ /external/ ምክንያቶች አሉ። ስለሆነም ክፍተቶችን መመርመርና መፍትሄዎችን መሻት አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም:::

መወያያ ነጥብ 6፣ዘዬን በተመለከተ የሚታየውን የተዘባ አመለካከት እንዴት ማስተካከል ይቻላል? በሚል ለቀረበዉ የመወያያ ጥያቄ ተማሪዎች ይበጃሉ ያሏቸውን የመፍትሄ ሀሳቦች በዉይይት አዳብረዉ ሲያስረዱ ብዙሀኑ በተደጋጋሚ የገለጹት የመፍትሄ ሃሳብ ማስተማር ነዉ የሚል ነዉ። ባለማወቅ ባለመገንዘብ ብዙ ስህተቶች ስለሚፈጠሩ ግንዛቤን ማሳደግ አስፈላጊ እንደሆነ ነው የገለፁት። ከዚህ በማስከተል ደግሞ ማወቅ ብቻውን በቂ ባለመሆኑ የመቻቻልን ባህል በማሳደግ ልዩነትን ተፈጥሯዊ አድርጎ ማየት፣ በትምህርት ራስን መቀየር ቢቻል ችግሩ እንደሚቀረፍ አስረድተዋል፡ለዚህ ችግር፡መፍትሄ ይሆናል በሚል ችግሩን በጥናትና ምርምር የፈተሹ የመስኩ ባለሙያዎችም

የግንዛቤ አጥረትን ማስወገድ ተገቢ እንደሆነ በአጽንኦት አስገንዝበዋል። ዘያዊ ልዩነትን /dialectal variation/ አስመልክቶ ሊከሰቱ የሚችሉ አለመግባባቶችን ለመቅረፍ ግንዛቤን ማጠንከርና የመቻቻል ባህልን ማጠንከር አስፈላጊ ነገሮች እንደሆኑ Harding & Riley (1993) ፣ Kramash(1996) (Murphy 2012)ባቀረቧቸዉ ሀተታዎች ለማሳገንዘብ ሞክረዋል ።

ቀደም ሲል በምራፍ ሁለት የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ዉስጥ ለመጠቆም እንደተሞከረዉ ሰዎች ባለማዎቅ የተነሳ የራሳቸዉን ቋንቋም ሆነ ዘዬ ከፍ የማድረግና የሌሎችን ደግሞ ዝቅ የማድረግ አዝማሚያ ይታይባቸዋል። ስለሆነም የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት ችግሩን ለመቅረፍ እንደሚያስችል አጠያያቂ ጉዳይ ሊሆን አይችልም።

ምዕራፍ አምስት

ማጠቀለያና አስተያየት

5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ ዘያዊ ልዩነቶቹና ተማሪዎችና መምህራን ስለዘዬ ያላቸው ግንዛቤ ቋንቋውን በማስተማር መማር ሂደት የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ መመርመር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጥናቱ ሌሎች ንዑሳን ዓላማዎችም አሉት፡እነዚህም ፦

- ተጠኝ መምህራንና ተማሪዎች ስለዘዬ ያላቸውን ግንዛቤ መፈተሽ፣
- ዘያዊ ልዩነት በመምህራንና በተማሪዎች ተግባቦት የሚያሳድረውን ተፅእኖ መመርመር፣
- ተጠኝ ተማሪዎችን በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታማ እንዳይሆኑ የሚያደርጉ የዘዬ /ቀበልኛ/ አጠቃቀም ችግሮች ምንምን እንደሆኑ መፈተሽ፣
- በመደበኛዉ የቋንቋዉ ትምህርት ቀበልኛ ዘዬን በጽሁፋቸዉና በንግግራቸዉ ቀላቅለዉ የሚጠቀሙ ተማሪዎችን ለማስተካከል መምህራን የሚጠቀሙባቸዉን የግብረመልስ አሰጣጥ ዘዴዎች ተገቢነት መፈተሽ፣
- በጥናቱ አማካኝነት ለተለዩ ችግሮች መፍትሄ ማ ፈላለግ ናቸው፡፡፡

እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካትም መረጃ ከተጠኚዎች ማለትም ከመምህራንና ከተማሪዎች እንዲሁም ከመማሪያ መጻህፍት በመዛግብት ፍተሻ አማካኝነት ተሰብስቧል፡፡ የመረጃዉን ተአማኒነት የተሻለ ለማድረግም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሁለት ሶስት እንዲሆኑ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ይኸውም የጽሁፍ መጠይቅ፣የቃል መጠይቅ ቡድን ተኮር ውይይትና የሰነድ ፍተሻ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡

በነዚህ መሳሪያዎች አማካኝነት ለዚህ ጥናት በተተኳሪነት ከተለዩት የሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የፊልጶስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የዕውቀት ወገኔ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤትና የብስራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራንና ተማሪዎች መረጃው ተሰብስቧል፡፡ በአጠቃላይ በምዕራፍ ሶስት ውስጥ በዝርዝር ለመግለፅ እንደተሞከረው ከነዚህ አራት ተቋማት ውስጥ ሃያ አምስት (ሁሉም) የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና እንዲሁም በናሙናነት የተለዩ 270 ተማሪዎች ተሳትፈዋል፡፡ መምህራት

በመረጃ ሰጪ ነት የተለዩት በግኝት ንሞና አማካኝት ሲሆን ተማሪዎች ደግሞ በቀላል የንዋና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡

በዚህ ሂደት መሰረት የተሰበሰበው የጥናቱ መረጃ በዓይነታዊና መጠናዊ ምርምር አማካኝነት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በጽሁፍ እና በቃል መጠይቅ እንዲሁም በሰነድ ፍተሸና በቡድን ተኮር ውይይት አማካኝነት የተሰበሰበው መረጃ በገለፃና ትረካ ስልት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ መጠናዊ ዘዴን በመጠቀምም እንዲሁ በየጥያቄዎቹ መልስ የሰጡ ተጠኚዎችን አሀዝ በመለየትና ወደ መቶኛ ስሌት በመቀየር መረጃውን ለመግለጽና ለማብራራት ተሞክሯል፡፡በሶስቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

ውጤቱ እንደሚያሳየው ተጠኚ መምህራንና ተማሪዎች ስለዘዬ ያላቸው ግንዛቤ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህም በመሆኑ ቀበልኛ ንግግሮችን በሚናገሩ ተማሪዎችና መምህራን ላይ የመደበኛዉ ዘዬ ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎች የሚስቁባቸዉ ፣ የሚሳለቁባቸዉና የሚዘባበቱባቸወ መሆኑ ታውቋል፡፡ እንዲሁም ቀበልኛ ተናጋሪዎችን እንደባላገር የመቁጠር፣ ዝንባሌዎች መኖራቸው ተረጋግጧል፤ መምህራንም እንዲሁ “ቀበልኛ በሚናገሩ ተማሪዎች ንባብ ባስነብብ ክፍሉን ያስረብሹብኛል በሚል ዕጅ ያወጡ ተማሪዎችን ሳይቀር ዕድል የሚነፍጉበት ሁኔታ መኖሩ ታውቋል፡፡ አንዳንድ መምህራን በበኩላቸዉ የግብረ መልስ መስጫ መንገዳቹዉ ቀበልኛ ዘዬ አጠቃቀምን እንደ ወንጀል በመቁጠር ተከታትለው ውጤት መቀነስ መሆኑን ተማሪዎቹ በመጠይቁ ምላሽ ላይ ጠቁመዋል፡፡ከዚህ የምንረዳው የግንዛቤ ችግር መኖሩን ነው፤፤ ምክንየቱም መምህራኑም ሆኑ ተማሪዎች ዘዬ በአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች መካከል ሊታይ የሚችል አንድ ስነልሳናዊ የቋንቋ ለዉጥ መሆኑን በመገንዘብ ለዘዬ ተጠቃሚዎች አዎንታዊ ምላሽ በመስጠትና በመቻቻል መንፈስ መስራትና ማሰራት አልቻሉም፡፡ እንዲያውም ዘዬ /ቀበልኛ/ ንግግር በጎያልሆነ አመለካከትን ፣አለመረዳዳትና አለመተባበርን መፍጠሩን ጥናቱ አመላክቷል፡፡

የጥናቱ ተሳታፊ መምህራንና ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ልዩ ልዩ ዘዬዎችን ማለትም የጎጃም፣ የጎንደር፣ የወሎ ፣ የሸዋ እና የአዲስ አበባ ዘዬዎችን የሚጠቀሙ መሆናቸው የተረጋገጠ ቢሆንም ከፍ ሲል እንደተገለፀው ተጠኝዎቹ ስለ ዘዬ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ ሆኖ ታይቷል፡፡ ይህም በመሆኑ በአንድ ቋንቋ ውስጥ የተለያዩ ዘዬዎች ሊኖሩ የመቻላቸውን ተፈጥሯዊ ስነልሳናዊ እውነታ የመዘንጋት ችግር ታይቶባቸዋል፡፡ ስለሆነም ከመደበኛው ዘዬ ውጪ ባደጉበት አካባቢ የለመዷቸውን ግለዘዬዎች የሚያንፀባርቁ ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን እንዳኂላቀር፣ እንደባላገር ከመቆጠርም በላይ ለስድድብና ለድብድብ የተጋለጡበት

ሁኔታ መኖሩም በተጠኝዎቹ ተጠቅሷል።ይህም ክስተት የመማር ማስተማሩ ሂደት ጤናማ ሆኖ እንዳይታይ አድርጎታል።

በሌላ በኩል ዘያዊ የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዳለዉም ጥናቱ አመላክቷል ።ተጠኚ መምህራን እንዳስረዱት በቋንቋዉ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር ስነጽሁፍን ለማስተማር የጎላ ድርሻ እላቸዉ ።ይሄዉም በፈጠራ ድርሰት ዉስጥ ገጸባህርያት የሚናገሯቸዉ የተለያዩ ቀበልኛ ንግግሮች የድርሰቶቹን መቼት ለመጠቆምና ጭብጥን ለማመላከት ያስችላሉ ።ይህም ዘያዊ ልዩነት ቋንቋን በማስተማር ሂደት ሊኖረዉ የሚችለዉን በጎ ተጽዕኖ ያሳያል።

ለምሳሌ በዚህ ጥናት እንደተረጋገጠው (አርጎ ያስጠላኝ፣ ጎረቤ አምጣልኝ ፣ ኮረጆሽን ያዥና ዉጪ፣ እከሊት የለይም? ወዘተ) ቀበልኛ አጠቃቀሞችን የሚያንፀባርቅ ቀበልኛ ዘዬ ተናጋሪ መምህር የአማርኛን የተለያዩ ዘዬዎች ለሚናገሩ የክፍል ተማሪዎች ቋንቋውን ያስተምራል። በሌላ በኩል አንድ የተለየ የአማርኛ ቋንቋ ዘዬን (የአዲስ አበባ ዘዬን) የሚናገሩ ተማሪዎች የተለያዩ የአማርኛ ቋንቋ ዘዬዎችን ተናጋሪ በሆኑ መምህራን እንዲማሩ ሆኗል። ከተማሪዎችና ከመምህራን በጽሁፍ መጠይቅ እንዲሁም ከተማሪዎች ቡድን ተኮር ውይይት የተገኘው መረጃ እንዳመለከተው ይህ አይነቱ የማስተማር መማር ሂደት በተማሪዎች ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። ተጠኚ መምህራን ለማስረዳት እንደሞከሩት ደግሞ የተፅዕኖ ምንጮቹ ምዕላዳዊ፣ ቃላዊ፣ እና አገባባዊ ልዩነቶች በሚል ሊገለጹ የሚችሉ ናቸው። ይኸውም የቋንቋው ዘዬዎች በቃላት ደረጃ መለያየት (ለአብነትም “ስኒ” ለማለት ፍንጃል፣ “ችቦ” ለማለት ዳቦት፣ “ምጣድ” ለማለት ምጎጎ) የሚባልበት ሁኔታ ይታያል። እንዲሁም በቋንቋ ዘያዊ አጠቃቀም ጊዜ የሚስተዋሉ አገባባዊ ልዩነቶች መኖር ሌላው የተጽዕኖ ምንጭ ሆኖ ተጠቁሟል። እኔ ወደ ቤቴ ልሄድ ነው ተብሎ መነገር የነበረበት አረፍተ ነገር በጎጃም ዘዬ (ምዕራብ ጎጃም) እና በጎንደር ዘዬ አገላለጽ “ቤቴን ልሄድነኝ” ተብሎ መደበኛዉን አጠቃቀም በጣሰ መልኩ ቀርቧል። በምዕላድ ደረጃም እንዲሁ ፆታ አመልካች ምዕላድ የሆነችው “ች” በሌላ አቻ አገልግሎት ባላት ምዕላድ “ይ” ተቀይራ የምትገኝበትን ሁኔታም (አለች = አለይ)ን መመልከት ተችሏል። በአጠቃላይ እነዚህና ሌሎች መሰል ተጽእኖዎች የተማሪዎችን መማር ውጤታማ እንዳይሆን የሚያደርጉ መሆናቸውን የተጠኚዎች ምላሽ አመላክቷል።

5.2. አስተያየት

በዚህ ጥናት የማጠቃለያ ክፍል ለማሳየት እንደተሞከረው የአማርኛ ቋንቋ ዘያዊ ልዩነቶቹ መኖርና መምህራንና ተማሪዎች ስለዘዬ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ ሆኖ መገኘት አማርኛን በማስተማር መማር ሂደቱ ላይ የራሳቸዉን ተፅዕኖዎች አሳርፈዋል፡፡ በመሆኑም ችግሩን ለመቀነስ ብሎም ለመቅረፍ መፍትሄ ይሆናሉ በሚል የሚከተሉት ሐሳቦች አጥኚው አስፍሯል፡፡

1. መምህራን ስለ ዘያዊ ልዩነት /dialectal variation/ ግንዛቤያቸውን በማሳደግ ለተማሪዎቻቸው በቂ ግንዛቤ ቢያስጨብጡ፣
2. ዘዬን /ቀበልኛን/ በሚጠቀሙና በመደኛው የቋንቋ ተግባቦት በሚገለገሉ ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን የቋንቋን ተለዋዋጭነት ባህሪ አሞኖ በመቀበል በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ በሚኖር የቋንቋ መስተጋብር ጊዜ የመከባበርና የመቻቻል ባህልን ቢያሳድጉ፣
3. መምህራን ቋንቋን ሲያስተምሩ በተማሪዎች የሚታየውን የቋንቋ ችግር ለመረዳት ሙከራ ቢያደርጉና የማሻሻል (የእርምት) ሂደቱን የቋንቋን ስነልሳናዊ ለውጦችን ባገናዘበ የቋንቋ ሳይንስን በማይጣረስ መልኩ ለማከናወን ቢሞከሩ ፣
4. መምህራን ለተማሪዎቻቸው የቋንቋ ለውጥ ተፈጥሯዊ መሆኑን በማስረዳት ተማሪዎች ዘዬን ጨምሮ ሌሎች የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነቶችን በሚማሩበት ጊዜ በእዉቀት በተገራ አእምሮ ታግዘው የመቻቻልና የመከባበር ልምድን እንዲያዳብሩ ቢያደርጉ፣
5. የሚመለከታቸው አካላት፣ ለመምህራን እንደአጠቃላይ በማህበራዊ ስነልሳን ላይ ፣ በተለየ ትኩረት ደግሞ በዘዬ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ቢሰጡ፡፣
6. መምህራን አሳታፊ የማስተማር ስነዘዴን በመተግበር የተለያዩ ዘዬዎችን የሚናገሩ ተማሪዎችን መርጦ በአንድ ቡድን በመመደብ በተግባር ዘዬን ሲጠቀሙ በክፍል በማሳየት ቀበልኛ ንግግር መቀላቀል ኃላቀርነት ወይም ዕጣ ፋንታ እንዳልሆነ ለማሳየት ቢሞክሩ፣
7. መምህራን ግብረመልስ ሲሰጡ የቀበልኛ ተናጋሪዎቹን ሞራል በማይነካ ሁኔታ ለማቅረብ ቢሞክሩ፡፡

ዋቢ መጻህፍት

ባየ ይማም ። (2000)።የአማርኛ ሰዋስዉ የተሻሻለ ሁለተኛ እትም። አዲስ አበባ፣ዕሌኒ ማ/ኅላ/የተ/የግ/ማህበር ።

አብነት ስሜ።(2007)።የቋንቋ መሠረታዉያን ።አዲስ አበባ ፣ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኅላ/የተ/የግ/ማህበር ።

ትምህርት ሚኒስቴር ። (2004)። አማርኛ የተማሪ መማሪያ አስራ አንደኛ ክፍል ፣ ኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚና አታሚ ድርጅት ኅ/የተ/የግ/ማህበር ።አዲስ አበባ ፣እና አል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት፣ ዱባይ ።

ትምህርት ሚኒስቴር። (2004)። አማርኛ የተማሪዉ መማሪያ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ድርጅት ኅላ/የተ/የግ/ማህበር ።አዲስ አበባ፣እና አል - ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት፣ ዱባይ ።

ትምህርት ሚኒስቴር።(2007)። አማርኛ የተማሪዉ መማሪያ ሰባተኛ ክፍል። ኩራዝ ኢንተርናሽናል አታሚና አሳታሚ ደርጅት ፣አዲስ አበባ።

ትምህርት ሚኒስቴር። (2007)። አማርኛ የተማሪዉ መማሪያ ስምንተኛ ክፍል። ኩራዝ ኢነተርናሽናል አታሚና አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ።

ዘሪሁን አስፋዉ።(1992)።የስነጽሁፍ መሠረታዉያን ።አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያድርጅት ።

የሻዉ ተሰማ ።(1996)።ልሳነ ብዕር ከመልሳነ ሰብዕ ።አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት።

ያለዉ እንዳወቀ ።(2006)።የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር ።ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ደበበ ኃይለጊዮርጊስ።(1996) ቅድመ ኮሌጅ አማርኛ።አዲስ አበባ ፣እሌኒ ማተሚያ ድርጅት።

Andrson، V, and Danel، R . (1956). Patterns of Educational Leadrship. Engleood Cliffs ፡Printic Hall.

Arndt، V.Harvey، P. & Natal ، J . (2000) A live to Language ; perspectives on Language awareness for English Languge Teachaars .Cambridge፡ Cambridge Univercity Press.

Chambrs،J.K and Tridgill،P.2004.Dialectoiogy(2nd ed).Cambridge: Cambridge University Press.

Cheshire، J.2007. Dialect and Education ،Responses from Sociolingustics .Cambridge: Cambridge Universsssity Press.Yuxin،Y.

Christen،D (1987).Vernaculare Dialccts In US Schools.ERIC Digests.http://eric،ed.gov/?id= ED289364.

Collmas F. (2005). Sociolingustics .The Fale of Speakers cheicer .Cambridge :Cambridge University Press.

Crutten. D .(986). Intonation .Cambridge ،Cambridge University Press.

Crystal D. (1997).The Cambridge Encyclopediya (2nd ed.)Cambridge ، UK:Cambridge University Press.

Fasold. R.(1984). The Sociolingusetics of Society ،Oxford : Blackwell.

Folk. J.(1978) Lingustcs and Language Toronto Wiley and Sons Press.

Ginn. C .(2005). Kalidioscope Teachers Guide. Tour.Uk.Harcccourt Educational limited.retrived from http://books.google.com.bd/books

Groves، J. (2008).Langue or Dialects – or Topolect ?Acomparison of the Attiudes of Hong Kongrs Mainland Chinese towards the status of Cantonese Hong Kong Baptist University.

Gupta F.A.(1997) When Mothertongue Education is not Prefrred .Journal of Multilingual and Multicultural Deviopment 18:496-506.

Hagen، A .(1989) .Dialects .Frisian and Education Some European Perspectives (48-61)Philadelphia: Multilingual Matters Limitted.

Harding، E. Reley،P(1996). The Bilingual Family،A hand Book for Parnts: Cambridge University Press.

Hazen، K.(2001). Teaching Abaut Dialects.Center for Applied Lingustics.Digest. retrived from www.google.com/Search ?q=tea.

Hofstter¸C..H.(2003). Sociolingustics: The study of Speakers Choices. Cambridge ¸UK: Cambridge University Press.

Holmes ¸J. (1992).An introduction to Sociolingustics .London: Longman.

Holms. J .(2001). An introduction to Sociolingustics Malaysia :Pearson Educational Limitted .Educational Journal 2015;4(5):263-269

Hudson. R. A (2001). Sociolingustics (2nd ed) Cambridge: Cambridge University Press.

Hudson. R. A. (1980). Sociolingustics .Cambridge : Cambridge University Press.

Hudson. R.A.(1996).Sociolingustics .2nd.ed¸(Cambridge .Text Books in Lingustics.) Cambridge : Cambridge University Press.

Jenny¸ C(.1982). Variation in an English Dialect Asociolingusttic Study Cambriidge:Cambridge University Press.

Jenny ¸C.(1987).Dialect and education .responses from sociolingustics and.In papapavlou and pavlos pavlou(eds.)Sociolingustics and Pedagogical Dimensions of Dialects in Education .Cambridge : Cambridge Scholars Press.

Kramash¸C.(1993).ContextandCalturinLanguagTeaching.Oxford UniversityPress.

Kramash¸C.(1996). Context and Cultre in Language Teaching .Oxford University Press.

Lado¸ R.(1964)Languge Teaching : Ascintific Approch .New York :Mc Graw Hill.

Mekonen Hhndie (2004)Lexical Standardization in Oromo un published MA Thesis Institute of Languge studies .Addis Ababa Universsity.

Mengistu Tadesse .(2011). Documentation and Discriptions of Amharic Dialects .APHD RESERTATIONON Addis Ababa University .Deviopment of Lingustics and Culture Program .(Unpublished).

Milroy¸ J. (1999). The Consequences of Standardization in Discriptive Lingustics .In Bex .T(ed)Standard English .London:Ruyledge.

Morshed¸ A. K. (2006).Banglapedia National Encyciopedia and Bangladish.Retrived from http//www.org/HT/D012.HTM.

Murphy،N.(2012). Teaching Dialect AWarenessinthe College Composition Classaan evaluation Adissertation Submitted to thgraduate school in Particularfulfilment of the requirement for the Degree ofDoctor of Philosophy Ball State University Muncle،Indiana.

Peter، J. (2002). Sociolingustics Variations and changes Wasngton DC: Georgetown University Press.

Ricards، J. and Weber، H.(1985)Longman dictionary of Lingustics. .Encyclopedia England Logman Group Limitted.

Richards،J.Platt،J.andWeber،H (.1985). Longman Dictionary of Lingustics، England; Longman Group Limitted.

Sesnan، B.(1997).How to Teach English Oxford Univrsity Press.

Schchi. S. (2013). The Effect Bangla Dialect on English Language Teaching : Teachers Perspectives & Attitudes Department of English &Humanities .Inpartialfulfilment of the requirements for the degree of MA in English ، BARAK UNIVERSITY.

Snell،J.Andrews،R(.2014).Towhat extent does aregional Dialect and accent impact on the development of reading and writing Skills Areport for the BBC .Ricard Andrews Institute of Education ،Universsity of London.

Takle Taddse .(2000) .Principls of Dveloping New Words and Technical vocabulary .Institute of Language Studies: Addis Ababa University.

Thomas، K.(1969)Areport Paper to be read at the 1969 convention of Teachers of English to spekof other language (TESOL)Chicago،Illinois،March،5-8،1969.

Wardhaugh ،R. (2010).An Introduction to Sociolingustics United Kingdom Blackwell Publishers Limitted.

Wolfram. W. (2008).When Islands lose Dialects the case of The ocraoke Brogue .Shima: The Intrenational Jouurnal of Research into Island cultures V.2 N0.1

Wolfram. W.(2008)Dialect in Society .In F.Colmas(Ed). The HandBook of Sociolingustics .Oxford/Cambridge:Bllacwell.

Wondimu Tegegne¸(2015).The use of Dialects in Education and its Impacts on Studnts Learning and Achievements Education Journal .Vol 4□¸No5¸2015pp.263-269dp. 10¸11648/j.edu.20150 405-22.

Yuxin¸Y.and Jan¸ C.V.O 2014 The effect of Dialect Speaking on Education and its Spillover Effects. CentER¸Tilburg Universty The Netherlands፡y.yaouvt.nlAsako

Zelalm ¸L.(2007).The Amharic Dialects Rivisted in .R voigt(ed.s). ¨From Beyond the Mediterranean"Akten des Intrnationalen Semitohamitisten Kongeresses (vll.ishak). VII.ISHAK). Brlin13 bis15;449-80.

አባሪ ሀ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጸሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

በተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ፤-

የዚህ መጠይቅ ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ ዘያዊ ልዩነቶቹና፣ መምህራንና ተማሪዎች ስለዘዬ ያላቸው ግንዛቤ ቋንቋዉን በማስተማር መማር ሂደት የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ ለመመርመር ታስቦ ለሚካሄደው ጥናት መረጃ ከተማሪዎች መሰብሰብ ነው፡፡፡ በመሆኑም አማርኛ ቋንቋን በማስተማር መማሩ ሂደት ላይ ዘዬን አስመልክቶ የምትሰጡት ምላሽ ለጥናቱ ስኬት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም ለቀረቡት ጥቄዎች ተገቢ ምላሽ በመስጠት መልካም ትብብራችሁ አይለየኝ፡፡ በመጀመሪያ ስለትብብራችሁ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ሀ. ማሳሰቢያ፡-

1. በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡
2. እናንተ የምትሰጡት ምላሽ ምስጢራዊነቱ ተጠብቆ ለጥናቱ ተግባር ብቻ የሚውል ይሆናል፡፡
3. የምርጫ ጥያቄዎችን ትክክል ነው የምትሉትን ምርጫ ብቻ በማክበብ መልሱ ፤ የባዶ ቦታ ሙሉ ጥያቄዎችን ደግሞ በተሰጠው ቦታ ብቻ መልሳችሁን አስፍሩ ፡፡

ለ. ግላዊ መረጃዎች፡-

- የትምህርት ቤቱ ስም --
- ክፍልና ሴክሽን--

ሐ. ጥያቄዎች፡-

1. አንተ/አንቺ የየትኛው የአማርኛ ቀበልኛ (ዘዬ) ተናጋሪ ነህ/ነሽ?

ሀ. የወሎ ለ. የጎጃም ሐ. የጎንደር መ. የሸዋ

ሌላም ካለ ይገለጽ ---

2. የትኛው የአማርኛ ዘዬ ደስ ይላል? (ክብር አለው)? ትላለህ/ ትያለሽ?

ሀ. የወሎ ለ. የጎጃም ሐ. የጎንደር መ.የሸዋ

ለሁለተኛዉ ጥያቄ ላቀረብከዉ/ሽዉ መልሰ ምክንያትህ/ሽ ምነድን ነዉ?---------------------
----

3. አንተ/ቺ የምትናገሪው/ሪው ዘዬ (ቀበልኛ ንግግር) መደበኛውን የአማርኛ ዘዬ ስትማር/ሪ ምን ያህል ተጽዕኖ ያደርግብሃል/ሻል?

ሀ. ከፍተኛ ለ. መጠነኛ ሐ. ምንም ተጽዕኖ አያደርግብኝም

ለሶስተኛዉ ጥያቄ መልስህ/ሽ ከ "ሐ" ዉጭ ከሆነ መገለጫዎቹ ምድን ናቸዉ ?-------

----

4. ከመደበኛው ዘዬ ውጪ ሌሎች ዘዬዎችን መናገር የሚቀናቸው ተማሪዎች ከአማርኛ ትምህርት ዓላማዎች የትኛውን ለመማር ይቸገራሉ?

ሀ. ማንበብን ለ.መጻፍን ሐ. ማዳመጥን መ. መ ናገርን ሠ. ሰዋስውን

ሌላም ካለ ይፃፉ ………………---

5 ቀበልኛ ዘዬን በንግግራቸዉ ጣልቃ እያስገቡ የሚጠቀሙ ተማሪዎች ምን ያህል ሳይሸማቀቁ በክፍል ዉስጥ በነጻነት ዘዬዎቻቸዉን ይገለገሉባቸዋል?

ሀ. ሁልጊዜ ለ .አልፎ አልፎ ሐ. ተማሪዎች ስለሚስቁባቸዉ ቀበልኛ ዘዬን ላለመጠቀም ሙከራ ያደርጋሉ

6.የክፍል ጓደኞቻቸው ጥያቄ ሲጠይቁ፣ ንባብ ሲያነቡ ወይም ገለፃና ማብራሪያ ሲያቀርቡ ቀበልኛ የቋንቋ አጠቃቀምን ቀላቅለው በሚናገሩበት ጊዜ የክፍላችሁ ተማሪች አቀባበል ምን ይመስላል?

ሀ. ፈገግ ይላሉ (ይስቃሉ)

ለ. ይጠቋቆማሉ (ይጠቃቀሳሉ)

ሐ. ያዳመጧቸውን ዕንግዳ ቃላት ይጽፏቸዋል

ሌላም ካለ ይገለጽ --

7.የአማርኛ መምህራችሁ ከቀበልኛ አነጋገር አንፃር ሲፈረጁ የትኛው ትክልል ይሆናል?

ሀ. በዘወትር ንግግራቸው ቀበልኛ ዘዬን ይቀላቅላሉ፡፡

ለ. አልፎ አልፎ ቀበልኛን ይጠቀማሉ፡፡

ሐ. ምንም አይነት ቀበልኛ አጠቃቀም አይታይባቸውም፡፡

8.ቀበልኛ ዘዬ አጠቃቀሞች በክፍል ዉስጥ የሚደመጡት በየትኛዉ አጋጣሚ ነው?

ሀ. አስተማሪ ሲያስተምር

ለ. ተማሪዎች ሲጠይቁ/ ሲመልሱ /

ሐ. ንባብ ሲነበብ

ሌላ መልስ ካለም ይገለጽ--

----

9. መደበኛውን የአማርኛ ዘዬ ቀበልኛ ዘዬ ተናጋሪ ለሆኑ ተማሪዎች ለማስተማር በሚሞከርበት ጊዜ የሚያጋጥሙ ችግሮች ምን ምን ናቸው? -----------------------------

----

10. በተማሪና በተማሪ መካል፤ ወይም በተማሪና በመምህር መካከል ቀበልኛን (ዘዬዊ አነጋገርን ምክንያት ያደረገ ግጭት /አለመከባበር/ ተፈጠሮ ያውቃል?

ለ10 ኛው ጥያቄ መልስህ/ሽህ አዎ ከሆነ የተከሰቱ አለመግባባቶችን በተመለከተ አጠር ያለ ማብራሪያ አቅርብ/ቢ ---

----

11.መነሳት የነበረበት ነገር ግን በቀረቡት ጥያቄዎች ዉስጥ ያልተካተተ ጠቃሚ ሃሳብ ካለ ብትጠቅሱልኝ?--

----

አባሪ ለ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

በመምህራን የሚሞላ መጠይቅ፤-

የዚህ መጠይቅ ዓላማ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር መማር ሂደት የቋንቋው የተለያዩ ዘዬዎች የሚያሳድሩትን ተጽእኖ ለመመርመር ታስቦ ለሚካሄደው ጥናት መረጃ ከተማሪዎች መሰብሰብ ነው፡፡ ስለሆነም የታሰበው ጥናት ስኬታማ ይሆን ዘንድ እናንተ ለቀረቡት ጥያቄዎች የምትሰጡት ምላሽ ወሳኝ በመሆኑ ጥያቄዎቹን በጥሞና በማንበብ ተገቢነት ያለው ምላሽ በመስጠት እንድትተባበሩኝ ስል በትህትና እጠይቃሁ፡፡ ለምታደርጉልኝ ቀና ትብብር በቅድሚያ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ሀ. ማሳሰቢያ፡-

1. በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡
2. እናንተ የምትሰጡት ምላሽ ምስጢራዊነቱ ተጠብቆ ለጥናቱ ተግባር ብቻ የሚውል ይሆናል፡፡
3. የምርጫ ጥያቄዎችን ትክክል ነው የምትሉትን ብቻ በመክበብ መልሱ፤ የባዶ ቦታ ጥያቄዎችን ደግሞ በተሰጠው ቦታ ብቻ መልሳችሁን አስፍሩ ፡፡

ለ. ግላዊ መረጃዎች፡-

- የትምህርት ቤቱ ስም ....
- የሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት.................. ክፍልና ሴክሽን..........

ሐ.የተመረቁበት የጥምህርት መስክ ዋና .... ንዑስ

1. እርስዎ የየትኛው የአማርኛ ቋንቋ ዘዬ ተናጋሪ ነዎት?

ሀ. የጎጃም ለ. የጎንደር ሐ. የወሎ መ. የአዲስ አበባ ሠ. የሸዋ ሌላም ካለ ይገለጽ..

2. የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች የተለያዩ የአማርኛ ቋንቋ ዘዬዎችን ይጠቀማሉ?

ሀ. አዎ ለ. አይጠቀሙም ሐ. እርግጠኛ አይደለሁም

3. እርስዎ የተለያዩ የአማርኛ ቋንቋ ዘዬዎችን የማይችሉ ከሆነ ከመደበኛው ዘዬ ውጪ ሌሎች ዘዬዎችን የሚናገሩ ተማሪዎች የሚፅፉትን፣ የሚሉትንና የሚያነቡልዎትን እንዴት ይረዳሉ?

ሀ. አውድን በመጠቀም

ለ. በጓደኞቻቸው በማስተርጎም

ሐ. የሌሎች መምህራንን እገዛ በመጠቀም

መ. ሌላም ካለ ይገለጽ ....

4. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተለያዩ የቋንቋው ቀበልኛ ተናጋሪዎች እኩል ውጤታማ ናቸው? ሀ. አዎ ለ. አይደሉም

ለአራተኛው ጥያቄ መልሱ አይደሉም ከሆነ ዘያዊ ልዩነት ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት የሚኖሩት ተፅዕኖዎች ምንድን ናቸው?(ከምን አንፃር የሚታዩ ናቸው ማለት ይቻላል?)

እርስዎን ጨምሮ ሌሎች የአማርኛ መምህራን ለአማርኛ ዘዬዎች እኩል እይታ (አመለካከት) አላችሁ?

5. የተለያዩ ቀበልኛ ተናጋሪ ተማሪዎች በሚናገሯቸው ቀበልኛዎች ኮርተው ምን ያህል በነፃነት የመጠቀም ዝንባሌ ያሳያሉ?

ሀ. ሁልጊዜ ለ. አልፎ አልፎ ሐ. በነጻነት የመጠቀም ስሜት አይታይባቸዉም

6. ለሰባተኛው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ¨ሐ” ከሆነ የቋንቋው የተለያዩ ዘዬ ተናጋሪዎች ተቻችለውና ተከባብረው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ከመምህራንና ከተማሪዎች ምን ይጠበቃል? ……………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………..

7. የተለያዩ የአማርኛ ቋንቋ ቀበልኛ ተናጋሪዎች የትኛውን ይዘት ሲማሩ የበለጠ ይቸገራሉ?

ሀ. የመናገር ለ. የማዳመጥ ሐ. የማንበብ መ. የመፃፍ ሐ. የሰዋስው

ሌላም ከላይገለጽ ……………………………………………………………..…

8. የተማሪዎችን ፈተናም ሆነ የክፍልና የቤት ስራዎች ሊያርሙ ትኩረት የሚያደርጉት ለየትኛው ነው ማለት ይቻላል?

ሀ. ለትምህርቱ ይዘት ለ. ለቋንቋ አጠቃቀማቸው ሐ. ሀና ለ

9. በአማርኛ ቋንቋ ዉስጥ የተለያዩ ቀበልኛ ንግግሮች መኖር በተማሪዎች መማርም ሆነ በመምህራን ማስተማር ላይ የሚያሳድረው የጎላ ተፅዕኖ አለ ብለው ያስባሉ?

ሀ. አዎ ለ. አላስብም

10. ለ9 ኛዉ ጥያቄ መልሰዎ አዎ ከሆነ ተጽዕኖዎቹ ምን ምን ሊሆኑ ይቸላሉ ?--

----

11. ተማሪዎቹ እነሱ ከሚናገሩት ዘዬ /ቀበልኛ/ ውጪ ሌሎች የሚናገራቸውን ለማዳመጥ ምን ያህል ፈቃደኛ ናቸው?

ሀ. ሁል ጊዜ ለ. አልፎ አልፎ ሐ. ፈቃደኞች አይደሉም

12. በቀበልኛ (ዘዬ) አጠቃቀም ምክንያት በተማሪዎች መካከል ወይም በተማሪና በመምህር መካከል አለመግባባት /ግጭት/ ተከስቶ ያውቃል?

ሀ. አዎ ለ. አያውቅም

13.አንዳንድ ወገኖች ስለዘዬ /ቀበለኛ አነጋገር አሉታዊ አመለካከት የሚያሳዩት ለምን ይመስልዎታል? ____

____

14.የአማርኛ ቀበልኛ ዘዬ ተጠቃሚ የሆኑ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች የሚያሳዩዋቸዉ የአጠቃቀም ልዩነቶች ከድምጽ ከቃላትና ከምዕላዶች አንጻር ምን ምን ናቸዉ ማለት ይቻላል በምሳሌዎች አስደግፈዉ ቢያብራሩልኝ?

15. በአማርኛ ቋንቋ ዉስጥ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር ቋንቋዉን በማስተማር መማር ሂደት ሊኖራቸዉ የሚችል፦

ሀ.አዎንታዊተጽዕኖዎችምንምን ናቸዉ? ______________________________________

____

____

____

ለ. አሉታዊ ተጽዕኖዎችስ? ____

____

____

አባሪ ሐ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዉማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድኅህረ ምረቃ መርሀ ግብር ፦

ለተማሪዎች የቡድን ዉይይት የተዘጋጁ መወያያ ነጥቦች

ዉድ ተማሪዎች! በቅድሚያ ጊዜያችሁን ሰዉታችሁ በመምጣት የዉይይቱ ተሳታፊ ስለሆናችሁ ልባዊ ምስጋናየን አቀረባለሁ።

የዚህ ዉይይት ዓላማ " የአማርኛ ቋንቋ ዘያዊ ልዩነቶቹና መምህራንና ተማሪዎች ስለዘዬ ያላቸዉ ግንዛቤ ቋንቋዉን በማስተማር መማር ሂደት ያላቸዉ ተጽዕኖ "በሚል ርእስ ለሚቀርበዉ ጥናት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ ሲሆን የምትሰጡት ሃሳብ ምንም አይነት አሉታዊ ተጽዕኖ እንደማያመጣባችሁ ከወዲሁ አስገነዝባለሁ።

የመወያያ ነጥቦች

1. ብዙ ጊዜ ቋንቋና ዘዬ ሲባል ትሰማላችሁ ለመሆኑ የሁለቱ ልዩነት ምንድን ነዉ?

2. በመደበኛ ዘዬና መደበኛ ባልሆነ ዘዬ /ቀበልኛ ንግግር መካከል ያለዉ ልዩነት ምንድን ነዉ?

3. ከጎንደር፣ ከጎጃም፣ ከወሎ፣ ከሸዋ ከአዲስ አበባ የአማርኛ ዘዬዎች መካከል የትኛዉ ደስ ይላል? ወይም ክብር አለዉ ? ለምን?

4. የአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎችን የሚጠቀሙ ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ በአንድ ላይ መገኘት በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ሊያስከትል የሚችለዉ አሉታዊ/አዎንታዊ ጎን ምንድን ነዉ?

5. አንዳደንድ ወገኖች ለቀበልኛ ዘዬ ወይም ንግግር ያላቸዉ አመለካለት የተዛባና ሚዛናዊነት የጎደለዉ ሆኖ ይታያል፤ ይህ ሁኔታ ከምን የሚመነጭ ይመስላችኋል?

6. ዘዬን በተመለከተ የሚታየዉን የተዛባ አመለካከት እንዴት ማስተካከል ይቻላል?

አባሪ መ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ የቋንቋች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ-ግብር

ለአማርኛ መምህራን የተዘጋጀ ቃለ-መጠይቅ

መምህር አንድ

ጾታ ፦ ወንድ

የትምህርት ደረጃ ፤ የመጀመሪያ ድግሪ

አማርኛን በማስተማር ያላቸዉ ልምድ፤ 11 ዓመት

-ቃለ ምልልሱ የተካሄደበት ቀን ፤ ግንቦት 30/09/2010 ዓ.ም

ሰዓት፤ 3፡30–4፡20

ቦታ ፤ ዕዉቀት ወገኔ ትምህርት ቤት

በመጀመሪያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ሆነዉ በሰአቱ በመገኘትዎ አመሰግናለሁ፡፡

ጥያቄ 1 ፤ እርስዎ የየትኛዉ አማርኛ ዘዬ ተናጋሪ ነዎት?

መልስ ፤ የአዲስ አበባ ዘዬ (መደበኛ ዘዬ)

ጥያቄ 2፤ በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር ቋንቋዉን በማስተማርና መማር ሂደት ዉስጥ ምን ጠቀሜታ አላቸዉ?

መልስ፤ የቋንቋ ተጠቃሚዉን /የዘዬ ተጠቃሚዉን ማንነት ለመገንዘብ ባህሉን ወጉን ለማወቅ አንደ ቅርስ (ትዉፊት) ማስተማሪያነት ያገለግላሉ ማለት ይቻላል፡፡

ጥያቄ 3፤ እርስዎ የሚናገሩት ዘዬ መደበኛዉን የአማርኛ ዘዬ በሚያስተምሩበት ጊዜ ጣልቃ እየገባ ያስቸግርዎታል?

መልስ ፤ እኔ መደበኛዉን ዘዬ ተጠቃሚ በመሆኔ አልቸገርም፡፡

ጥያቄ 4 ፣እርስዎ ከሚጠቀሟቸዉ ወይም ተማሪዎችዎ ከሚገለገሉባቸዉ ቀበልኛ ንግግሮች ጥቂት ማሳያዎቹን ቢጠቅሱልኝ ?

መልስ ፣አልበልቼም፣ አልሰምቼም፣ ዴግነት እዲር ወዘተ.

ጥያቄ 5፣ በቀበልኛ ዘዬ መገልገልን የኋላቀርነት ምልክት አድርገዉ የሚቆጥሩ ወገኖች አጋጥምዎት ያዉቀሉ? እርስዎ በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ሃሳብ አለዎት?

መልስ፣ብዙ ሰወች ከዚሁ አንጻር ነዉ የሚመለከቱት፡፡ እንደ አንድ የቋንቋ መምህር እኔ ደግሞ የኋላቀር መገለጫ አድርጌ አልምስደዉም ቋንቋ በመወለድ ሳይሆን የሚለምዱትና የሚማሩት በመሆኑ ተምሮ ማስተካከል ስለሚቻል መደበኛዉን ዘዬም መማር ስለሚቻል ችግር ተደርጎ የሚታይ መሆን የለበትም እላለሁ፡፡

ጥያቄ 6፣ በቀበልኛ ዘዬና በመደበኛ ዘዬ ተናጋሪ ተማሪዎችና መምህራን መካከል ዘዬን መሰረት/ ምክንያት ያደረጉ አለመግባባቶችና ግጭቶች ተከስተዉ አጋጥምዎት ያዉቃል ?

መልስ ፣ አይ አላጋጠመኝም ፡፡

ጥያቄ 7 ፣ ቀበልኛ ዘዬ ተጠቃሚ ተማሪዎች መደበኛዉን የአማርኛ ዘዬ ሲማሩ የበለጠ የሚቸገሩት በየትኛዉ የቋንቋ ትምህርት ይዘት ላይ ነዉ?ለምን?

መልስ፣በንግግር ክሂልና በመጻፍ ክሂል ላይ ነዉ ፡፡ምክንያቱም የራሳቸዉን ቀበልኛ ዘዬ እንዲቀላቀሉ የሚጋለጡት በነዚህ ሁለት ክሂሎች ላይ ስለሆነ ፣

ጥያቄ 8፣በአማርኛ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር በማስተማር መማሩ ላይ ሊኖራቸዉ የሚችሉ አሉታዊ ተጽዕኖዎች ካሉ ቢጠቅሱልኝ?

መልስ፣ከአካባቢያቸዉ ራቅ ብለዉ የሚማሩ (መምህራንም ከሆኑ የሚያስተምሩ) ወገኖች በዘያቸዉ በመጠኑም ቢሆን ከሄዱበት አካባቢ ስለሚለዩ በትምህርት ቤት /በክፍል ተማሪዎች /ሊገለሉ በቅላጼያቸዉ ሊሳቅባቸዉ ስለሚችል ይህንን እያሰቡ ቀበልኛ ዘዬ ተናጋሪዎች ጥያቄ ከመጠየቅ መልሰ ከመመለስ እንዲቆጠቡ ያደርጋሉ፡፡

ጥያቄ 9 ፣በቀበልኛ ንግግር /ዘዬ/ ምክንያት በመማር ማስተማርሩ ሂደት ላይ አለመግባባትና መናናቅ እንዳይፈጠር ምን ቢደረግ የተሻለ ይሆናል?

መልስ፣ እኔ እንዳስተዋልኩት ችግሩ በአመዛኙ ከመምህራን በኩል የሚታይ ነዉ ፡፡በተለይ አዲስ ተመድበዉ የሚመጡ መምህራን የተለያዩ ቀበልኛ ንግግሮችን በስፋት የሚጠቀሙ በመሆኑ አዲስ አበባ ሲመደቡ በተቻለ መጠን ቅድመ ሁኔታዎችን ተረድተዉ የቋንቋዉን ሳይንስ ስለሚያዉቁት በቀበልኛ ንግግራቸዉ ሳይሸማቀቁ ተማሪዎችንም እንደ ጠላት ሳይመለከቱ ቀስበቀስ ከነሱጋር የመግባባት /የመቅረብ ስራ ቢሰሩ ችግሩ ይቀረፋል ብዬ አስባለሁ፡፡

ጥጣቂ 10 ፣ ቀበልኛ ዘዬ /ንግግር በንግግራቸዉም በጽኁፋቸዉም እያቀላቀሉ ለሚናገሩና ለሚጽፉ ተማሪዎቸ በቃልም ሆነ በጽሁፍ ግብረ መልስ የሚሰጥበት ሁኔታ ምን ይመስላል?

መልስ፣ ይኄነዉ ብዬ የምገልጸዉ የተለየ ነገር የለኝም ፡፡ነገርግን በመደበኛዉ የጽህፈት ትምህርት ኢመደበኛ የሆነ ማናቸዉንም አጠቃቀም እንዳይጠቀሙ ጥረት አደርጋለሁ፡፡ በፈተና ጊዜ ከሆነ ደግሞ ዉጤት የምቀንስበት ሁኔታም አለ፡፡

መምህር ሁለት

ጾታ፣   ሴት

የትምህርት ደረጃ የመጀመሪያ ዲግሪ

አማርኛን በማስተማር ያላቸዉ ልምድ 5 ዓመት

ቃለ ምልልስ የተካሄደበት ቀን ሰኔ 1/10/2010 ዓ.ም

ሰዓት፣ 5፡30-6፡15

ቦታ፣ ብስራት የመጀመሪያ ደረጃ ትህርት ቤት

በመጀመሪያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ሆነዉ በመገኘትዎ አመሰግናለሁ ፡፡

ጥያቂ 1፣ እርስዎ የትኛዉን የአማርኛ ዘዬ ይናገራሉ ?

መልስ ፣የጎንደርን ዘዬ እናገራለሁ፡፡

ጥያቂ 2፣ በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር ቋንቋዉን በማስተማር መማር ሂደት ዉስጥ አስፈላጊነታቸዉን እንዴት ይገልጹታል?

መለልስ ፣በጣም ዉሱን የሆነ አገልግሎት ያላቸዉ መስሎ ይታየኛል ።ምክንያቱም በትምህርት ቤት የሚሰጠዉ ቋንቋ ከነሱ በተቃራኒ በመደበኛዉ ዘዬ በመሆኑ ነዉ።

ጥያቄ 3፣አርስዎ የሚናገሩት ዘዬ መደበኛዉን የአማርኛ ዘዬ በሚያስተምሩበት ጊዜ ጣልቃ እየገባ ያስቸግርዎታል ?

መልስ ፣አዎ በተወሰነ መልኩ ሳላስበዉ ቀበልኛ አነጋገር የምቀላቅልበት ሁኔታ አለ።

ጥያቄ 4 ፣ እርስዎ ከሚጠቀሟቸዉ ወይም ተማሪዎችዎ ሲጠቀሟቸዉ ከሰሟቸዉ ቀበልኛ አነጋገሮች የተወሰኑ ማሳያዎችን ቢጠቅሱልኝ?

መልስ ፣እኔ ብዙ ጊዜ(ኸ ፣ ኸ፣ ኸ)ማለት አዘዎትራለሁ ።ለምሳሌ ከጓደኛየ ጋር ሳወራ " ኸ ! አንተ ምን ሆነህ ነዉ ?ኸ ! ምኑ ነዉ አንተ "በዚህ አይነት ንግግሬ እታወቃለሁ ።

ጥያቄ 5፣በቀበልኛ ዘዬ መጠቀም የኂላቀርነት ምልክት አድርገዉ የሚመለከቱ ሰዎች አጋጥምዎት ያዉቃሉ ?አርስዎ በዚህ ሃሳብ ምን አስተያየት አለዎት ?

መልስ ፣እንደተባለዉም ሰዎች ቀበልኛ ንግግርን የፋራነትና ያለመሰልጠን ምልክት አድርገዉ ይመለከታሉ ።ሆኖም ቀበልኛ ተናጋሪ ሆነህ አትሰለጥንም እንደማለት እየወሰዱት ነዉ፤ በጣም ስህተት ነዉ ።ሁሉም ሰዉ አፍ የፈታበትን የቋንቋ አጠቃቀም በቶሎ ሊቀይር አይችልም ይኼነዉ መታየት ያለበት።ከመሰልጠን ካለመሰልጠን ጋር ካያያዝነዉ ዉጫዊ ምክንያት ጋር አያያዝነዉ ማለት ነዉ።

ጥያቄ 6፣ቀበልኛ ዘዬ ተናጋሪ /ተጠቃሚ መምህራንና ተማሪዎች መደበኛዉን የአማርኛ ዘዬ ከሚጠቀሙት ጋር ዘያዊ አጠቃቀምን ምክንያት ባደረገ አላስፈላጊ ግጭት ዉስጥ ገብተዉ አጋጥምዎት ያዉቃል?

መልስ፣ አዎ አጋጥሞኛል ።ብዙም የከፋ ጠብ ዉስጥ ባያስገባቸዉም ሁለት ጓደኞቼ "አብራጃ " የሚል ቃል አንደኛዉ ጥላ ቦታ በሚል አገባብ ተጠቅሞበት ስለሰማዉ ምን ለማለት ፈልገህ ነዉ ብሎ ስለሳቀበት፤ በይባላል አይባልም ክርክር ዱላ ቀረሽ ዉዝግብ ዉስጥ ገብተዉ እንደነበር አስታዉሳለሁ።

ጥያቄ 7፣ቀበልኛ ተናጋሪ ተማሪዎች መደበኛዉን የአማርኛ ዘዬ /ቋንቋ/ ሲማሩ በየትኛዉ የትምህርቱ ይዘት ላይ የበለጠ ይቸገራሉ ማለት ይቻላል?

መልስ ፣ያዉ በንግግር ላይ ይለዩ ካልሆነ በስተቀር በትምህርት አቀባበል አንዲያዉም የተሻሉ እነሱ ናቸዉ።

ጥያቄ 8 ፣በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር ቋንቋዉን በማስተማር መማር ላይ ሊኖራቸዉ የሚችሉ አሉታዊ ተጽዕኖዎች ምን ምን ናቸዉ?

መልስ፣ ቀበልኛ ተጠቃሚዎች ተደማጭነትን ሲከለክሏቸዉ ማለትም ሲስቁባቸዉ ሲመለከቱ የበታችነት ስሜት ሊሰማቸዉ ይችላል፤ በዚህ ጊዜ ትምህርታቸዉም ላይ ጥላ ሊያጠላ የሚችል መጥፎ ስሜት ሊመጣባቸዉ ይችላል። በሌላ በኩል በግልባጭ ስንመለከተዉ ደግሞ የአዲስ አበባዉን መደበኛ ዘዬ የሚናገሩ ተማሪዎች ራሳቸዉን እንደ ሰለጠነ አካል በመቁጠር ራሳቸዉን እንዲኮፍሱ ምክንያት ሊሆናቸዉ ይችላል።

ጥያቄ 9 ፣በቀበልኛ ንግግር ምክንያት በተማሪና በመምህር መካከል ሊፈጠር የሚችል አላስፈላጊ የሆነ እርስበርስ መናናቅን፣ አለመደማመጥን ለመቅረፍ ምን መደረግ አለበት ?

መልስ፣መፍትሄዉ ያዉ መማማር ግንዛቤን ማስፋፋት ዲሞክራሲን በመማር ማስተማሩ ሂደትም ማረጋገጥ ቢቻል መቻቻሉ የመግባባቱ ነገር ይፈጠር ይመስለኛል ።

ጥያቄ 10 ፣ መደበኛ ያልሆነ ዘዬን በንግግራቸዉና እንዲሁም በጽሁፎቻቸዉ ጣልቃ እያስገቡ ለሚጠቀሙ ተማሪዎች ግብረመልስ የሚሰጡት በምን መልኩ ነዉ?

መልስ ፣ብዙዉን ጊዜ¨ ኤክስ¨ እና " ራይት" ብዬ ነዉ የምሰጣቸዉ ።በንግግር ጊዜ ከሆነ ምን ማለትህ/ሽ ነዉ ? አማርኛ ነዉ? ቻይንኛ ? ብዬ አንዳንድ ጊዜ ልቀልድባቸዉ እችል ይሆናል፤ ይህን የማደርገዉ ግን ክፍሉን ለማነቃቃት ነዉ በተለይ ከሰአት በኋላ ሲሆን ።

አመሰግናለሁ።

መምህር ሶስት ፣

ጾታ ፦ ወንድ

የጥምህርት ደረጃ ፦ የመጀመሪያ ዲግሪ

አማርኛን በማስተማር ያላቸዉ ልምድ ፣ 6 ዓመት

ቃለ ምልልሱ የተካሄደበት፣ ቀን ሰኔ 1/10 /2010 ዓ.ም.

ሰዓት ፣ 8፡ 00-8፡42

ቦታ ፦ ፊልጶስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት

በመጀመሪያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ሆነዉ በመገኘትዎ አመሰግናለሁ።

ጥያቄ 1፦ እርስዎ የትኛዉን የአማርኛ ዘዬ ይናገራሉ?

መልስ ፦ የወሎን

ጥያቄ 2፦ በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር ቋንቋዉን በማስተማር መማር ሂደት ዉስጥ አስፈላጊነታቸዉ ምን ያህል ነዉ?

መልስ፣ ያዉ የቋንቋዉ ትምህርት የሚቀርብባቸዉ ዓላማዎች ስላሉት እነሱን ለማሳካት ያግዛሉ ።ለምሳሌ ስነጽሁፍ ለማስተማር ቋንቋዉ "እንደወረደ" (ተፈጥሯ ዊ ባህሪዉን እንደ ጠበቀ) ለመጠቀም ዘዬዎችን የምንጠቀምበት ሁኔታ አለ። "ለቫራይቲዉ" የሚባል ነገርም እዚህ ላይ ሊነሳ ይችላል ። ለንጽጽር ጠቀሜታ አላቸዉ።ትክክል የሆነዉ ላልሆነዉ በምን ተለዬ?ሲባል መደበኛ የሆነዉ ካልሆነዉ የተለየበትን ማነጻጸር ያስችላሉ።

ጥያቄ 3 ፣ቀበልኛ ንግግርዎ መደበኛዉን ዘዬ /ቋንቋ በሚያስተምሩበት ጊዜ ጣልቃ እየገባ አስቸግሮዎት ያዉቃል?

መልስ ፣ አዎ በጣም (ያስሸግረኛል) አብሮን አድጎ ኋላ የት ይተወናል ።

ጥያቄ 4፣እርስዎ ከሚጠቀሟቸዉ ወይም ተማሪዎችዎ ሲናገሯቸዉ ከሰሟቸዉ ዘያዊ ንግግሮች መከከል ጥቂት ምሳሌዎችን ይንገሩኝ?

መልስ፣ "እንዴት ናችሁ አቦ"፣እኔ ብዙ ጊዜ የምጠቀመዉ ነዉ ። ከዚህ ባሻገር በወሎዬ ዘዬ ዉስጥ "ዴ" በጣም ተደጋግሞ እንደሚደመጥ ብዙ ተብሎለታል ። ለምሳሌ ("ዴብተር ፣ዴጋ፣ ዴረቅ ዴሞ") መጠቀስ ይችላሉ። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ፣ "ኸዚ ኸዛ" ሲሉ ይደመጣሉ።

ጥያቄ 5፣በቀበልኛ ዘዬ መጠቀምን እንደ ኋላቀርነት ማሳያ አድርገዉ የሚመለከቱ ሰዎችን ታዝበዉ ያዉቃሉ?እርስዎ በዚህ ላይ ምን ሃሳብ አለዎት?

መልስ ፣ አዎ አሉ።በተለይ የቋንቋና ቋንቋ ነክ እዉቀት የሌላቸዉ ወገኖች ይህንን ሀሳብ በሚገባ ተቀብለዉት ሲናገሩት ይሰማሉ። ስለዚህ ችግሩ ካለማወቅና አንዳንዴም ሆን ተብሎ

አንድን ማህበረሰብ ዝቅ ብሎ እንዲታይ በመፈለግ ቋንቋዉን ወይም ዘዬዉን የማጥላላት ዘመቻ ሊኖር ይችላል፡፡

ጥያቄ 6፣በትምህርት ቤታችሁ ዉስጥ ቀበልኛ ንግግርን ምክንያት ያደረጉ ግጭቶች ወይም አለመግባባቶችን በተማሪዎችና በመምህራን እንዲሁም በተማሪና በተማሪ መካከል አስተዉለዋል?

መልስ ፣አይ አስተዉየ አላዉቅም፡፡

ጥያቄ 7፣ ቀበልኛ ዘዬ ተጠቃሚ የሆኑ አማርኛ ተማሪዎች መደበኛዉን ዘዬ ሲማሩ የሚቸገሩት የትኛዉን የቋንዉን ይዘት ሲማሩ ነዉ ?

መልስ ፣መደበኛ ዘዬን ሲማሩ ሊቸገሩ የሚችሉት መናገር ላይ ነዉ ሊሆን የሚችለዉ፡፡ ምክንያቱም ድምጾችን ለመጥራት ሲፈልጉ ቅላጼያቸዉ እየተቀየረ ስለሚያስቸግራቸዉ፡፡

ጥያቄ 8 ፣በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር ቋንቋዉን በማስተማር መማር ሂደት ሊያሳድሩ የሚችሏቸዉ አሉታዊ ተጽዕኖዎች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ ?

መልስ ፣ከመምህሩ አንጻር የመደበኛ ዘዬዉን ያህል ቀበልኛ ዘዬዎች የተጠኑበት ሁኔታ ስለሌለ የመረጃ አጥረት ሊያገጥም ይችላል ፤ይህ ሆነ ማለት ደግሞ የጠራ ግንዛቤ ሳይኖር ማስተማሩ ተማሪዎችን ጨምሮ ወደማደናገሩ መዉሰድ ማለት ነዉ፡፡አንዱ ዘዬ ከሌላዉ በምን ይለያል ? ዘዬ እንዴት ይፈጠራል? የመሳሰሉ ጥያቄዎች በጥናት ተፈትሸዉ በቂ መረጃ የማይገኝላቸዉ ከሆነ ሳይንሳዊ ትንታኔ ስለሚጠፋ ፉክክሩ ልማዳዊ ብቻ ስለሚሆን ዘዬዎች ለግጭት መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ጥያቄ 9፤ በመማር ማስተማሩ ሂደት ዘያዊ ልዩነት ወደአላስፈላጊ መናናቅና አለመግባባት ደረጃ እንዳይወስድ ምን ማድረግ ተገቢነት አለዉ?

መልስ ፤ መምህራን ላይ ስራ ቢሰራ ተማሪዎችንም መቀየር ይቻላል፡፡ስለዘህ አዳዲስ መረጃዎች በቋንቋ ላይ እንዲሁም በዘዬ ላይ በስልጠና መልኩ ለመምህራን ማድረስ ከተቻለ ችግር አይፈጠርም ብዬ አስባለሁ ፡፡ከዚህም በተጨማሪ የመምህራን ምደባ በተቻለ መጠን ቢያንስ ቢያንሰ ልምድ አስኪያካብቱ ድረስ በለመዱት አካባቢ እንዲሰሩ ቢደረግ የተሻለ ይሆናል ፡፡ ምክንያቱም አዲስ ምሩቃን ከየክልሎች መጥተዉ አማርኛን በመደበኛ ዘዬነት ለሚናገሩ የከተማ ተማሪዎች ለማስተማር በሚሞክሩበት ጊዜ ቀበልኛ አነጋገራቸዉ ጎልቶ እየወጣ በተማሪዎቻቸዉ ይሳቅባቸዋል፣ይህም ብቻ ሳይሆን ትምህርቱንም እንደማይችሉት

የመቁጠርና መምህሩን የመናቅ ሁኔታ አለ፡፡ስለዚህ ለተማሪዎች ቋንቋዉን መናገር መቻልና ማወቅ እንደሚለያይ ፣ማስተማር ማብቃት ችግሩን ሊቀንሰዉ ይችላል፡፡

ጥያቄ 10፤መደበኛ ያልሆነዉን የአማርኛ ዘዬ በንግግርም ሆነ በጽሁፋቸዉ ቀላቅለዉ የሚጠቀሙ ተማሪዎችን ግብረ መልስ የሚሰጥዋቸዉ በምን መልኩ ነዉ?

መልስ፣ በጽሁፍ ከሆነ እዚያዉ ላይ ትክክል እንዳልሆኑ አርሜ ምክንያት አጽፍላቸዋለሁ፣ በንግግር ጊዜ ከሆነ ደግሞ ለማለት የፈለጉትን ሃሳብ ከአዉዱ ተገንዝቤ በምን መልኩ መቅረብ እንደነበረበት እገልጽላቸዋለሁ፡፡

መምህር አራት ፣

ጾታ፣ ሴት

የትምህርት ደረጃ፣ ሁለተኛ ዲግሪ

አማርኛን በማስተማር ያላቸዉ ልምድ፣ 23 ዓመት

ቃለ ምልልሱ የተካሄደበት ቀን፣ ሰኔ 2/10/2010ዓም

ቦታ፣ ሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት

በመጀመሪያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ሆነዉ በቀጠሯችን በመገኘትዎ አመሰግናለሁ፡፡

ጥያቄ 1፣ እርስዎ የትኛዉን የአማርኛ ዘዬ ይናገራሉ?

መልስ፣ የጎጃምን ዘዬ እናገራለሁ፡፡

ጥያቄ 2፣በአማርኛ ቋንቋ ዉስጥ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር ቋንቋዉን በማስተማር መማር ሂደት ዉስጥ አስፈላጊነታቸዉ ምንያህል ነዉ ?

መልስ ፣ከፍተኛ ነዉ ፡፡ ቀበልኛ ዘዬዎችም ሆኑ መደበኛዉ ዘዬ በስነልሳን የጥናት ዘርፍ ከድምጽ ጥናት ጀምሮ ይጠናሉ ፡፡ስለሆነም ቋንቋን ከስረመሰረቱ ለማወቅ እነዚህ የተለያዩ ዘዬዎች መጠናት ስላለባቸዉ አስፈላጊ ይሆናሉ ፡፡በስነጽሑፍ ዘርፍም ቢሆን ዘዬዎች ለቋንቋዉ ትምህርት አስፈላጊ ናቸዉ፡፡ለምሳሌ በፈጠራ ድርሰት ዉስጥ በገጸባህርያት ንግግር /ዘዬ አማካኝነት የፈጠራ ስራዉን አካባቢ (መቸት) መግለጽ ይቻላል፤እንዲሁም የድርሰትን ጭብጥ ለማመላከት ቀበልኛ ንግግር የጎላ ጠቀሜታ አለዉ፡፡

ጥያቄ 3፣ አርስዎ የሚናገሩት ዘዬ መደበኛዉን የቋንቋዉን ዘዬ ለማስተማር በሚሞክሩበት ጊዜ ጣልቃ እየገባ ያስቸግርዎታል?

መልስ፣ አዎ አልፎ አልፎ በተለይ ገና ጀማሪ መምህር በነበርኩባቸዉ ጊዜያት ጣልቃ እየገቡ ያስቸግሩኝ ነበር ።

ጥያቄ 4፣ እርስዎ ከሚናገሯቸዉ /ተማሪዎቸዎ ሲናገረዋቸዉ ከሰሟቸዉ ቀበልኛ ንግግሮች የተወሰኑ ምሳሌዎች ቢጠቅሱልኝ ?

መልስ፣ ለምሳሌ (ክላ፣ ወግድ ፤ልሰበዉ፣ ደሸናም ፣ እንዳይገልህ((እንዳይገጭህ) እነዚህን አስታዉሳለሁ።

ጥያቄ 5፣ ቀበልኛ ዘዬ መናገርን የኋላ ቀርነት መገለጫ አድርገዉ የሚመለከቱ ወገኖችን አስተዉለዉ ያዉቃሉ ?በዚህ ላይ የርስዎ ሃሳብስ ምንድን ነዉ?

መልስ፣ በትክክል፤ በዙዎች የሚያስቡት እንደተባለዉ ነዉ።እኔ ትክክል አንዳልሆነ አስባለሁ።ምንም አይነት ንድፈሃሳባዊ ድጋፍ የሌለዉ ጭፍን አመለካከት ነዉ።

ጥያቄ 6 ፣ቀበልኛ ዘዬ ተጠቃሚ ተማሪዎችና መምህራን መደበኛ ዘዬ ተነጋሪ ከሆኑ ት ጋር በዘዬ አጠቀቀም ምክንያት አለመግባባት ደረጃ ተዳርሰዉ ያዩበት ሁኔታ ይኖር ይሆን?

መልስ ፣እኔ በግሌ አላጋጠመኝም።ነገር ግን በዙ ጊዜ የሚጋጩ አንዳንድ መምህራን አንዳሉ አዉቃለሁ ።በንግግራቸዉ ተማሪዎች የሚያሾፉባዉ መምህራን እንዳሉ ግልጽ ነዉ።ለምሳሌ በትምህርት ቤታችን አንድ የ11ኛ ክፍል ተማሪ አስተማሪዉ የሚጠቀምባቸዉን አንዳንድ ቀበልኛ ቃላት እያስተጋባ ተማሪዎች በመምህሩ ላይ እንዲስቁ ያደርግ ስለነበር ጉዳዩ በክስ ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ደርሶ ተማሪዉ ለአንድ ዓመት ከትምህርት ገበታዉ የተቀጣበትን ሁኔታም አስታዉሳለሁ ።

ጥያቄ 7፣ ቀበልኛ ተናጋሪ ተማሪዎች መደበኛዉን የአማርኛ ዘዬ ሲማሩ በየትኛዉ የቋንቋዉ ትምህርት ይዘት ላይ የበለጠ ይቸገራሉ ማለት ይቻላል ?ለምን?

መልስ በዘዬ ልዩነት ምክንያት ሊቸገሩ ከቻሉ በንግግር ክሂል ላይ ይሆናል ብዬ ነዉ የማስበዉ ።ምክንያቱም ከንግግር ጋር ዘዬ ቀጥተኛ ትስስር ስላለዉ ነዉ ።

ጥያቄ 8፣በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር በማስተማር መማሩ ሂደት ሊኖራቸዉ የሚችል አሉታዊ ተጽዕኖዎች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

መልስ ያን ያህል የጎላ "አካዳሚያዊ " ተጽዕኖ ይኖራቸዋል ብዬ አላስብም ፡፡ሆኖም በክፍል ዉስጥ የቀበልኛ ዘዬ ቅላጼ በሚያሰሙ ተማሪዎች ወይም መምህራን የሚስቁ የሚያፌዙ ስላሉ ለመማር ማስተማሩ ሂደት እንቅፋት ይሆናሉ፡፡

ጥያቄ 9፣ በቀበልኛ ዘዬ /ንግግር/ምክንያት አላስፈላጊ የሆኑ አለመግባባቶች መናናቆች እንዳይፈጠሩ ምን መደረግ አለበት ብለዉ ያስባሉ?

መልስ ለመምህራን /ለጀማሪዎቹ የክፍል አያያዝ ላይ ስልጠና አልፎ አልፎ ቢሰጥ፡፡ ብዙጊዜ ችግር ዉስጥ የሚታዩት እነሱ ስለሆኑ ችግሩን መቀነስ የሚቻል ይመስለኛል፡፡

ጥያቄ 10 .መደበኛ ያልሆነዉን የአማርኛ ዘዬ በንግግራቸዉም በጽሁፋቸውም ቀላቅለዉ ለሚጠቀሙ ተማሪዎች ግብረ መልስ የሚሰጡበት ሁኔታ ምን ይመስላል ?

መልስ ፣ አይባልም ይባላል ከማለት ባሻገር በዙም የተለዬ ግብረ-መልስ የምሰጥበት ሁኔታ የለም፡፡

መምህር አምስት፡-

ጾታ፣ ሴት

የትምህርት ደረጃ፣ የመጀመሪያ ዲግሪ

አማርኛን በማስተማር ያላቸዉ ልምድ 4 ዓመት

ቃለ ምልልሱ የተካሄደበት ቀን ሰኔ 3/10/2010 ዓም.

ሰዓት፣ 5 ፡07-5፡50

ቦታ፣ ብስራት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት

በመጀመሪያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ሆነዉ በመገኘትዎ አመሰግናለሁ፡፡

ጥያቄ 1፣ እርስዎ የየትኛዉ የአማርኛ ዘዬ ተናጋሪ ነዎት ?

መልስ፣ የጎንደር

ጥያቄ 2፣ በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር ቋንቋዉን በማስተማር መማር ሂደት ምን ጠቀሜታ ሊኖራቸዉ ይችላል?

መልስ፣ ቋንቋንና የተለያዩ የማህበረሰብ ባህልና ወጎችን አስተሳስሮ ለማስተማር ለማጥናት ይረዳሉ። በተደመጠ ዘዬ መነሻ ስለተናጋሪዉ ማናነት /ስብዕና ለመረዳት ከቋንቋ ትምህርቱ በተጨማሪ ጥሩ መማሪያ/agood lesson/ናቸዉ።

ጥያቄ 3፣ እርስዎ የሚናገሩት ዘዬ መደበኛዉን የአማርኛ ዘዬ በሚያስተምሩበት ጊዜ ጣልቃ እየገባ ያስቸግርዎታል?

መልስ፣ አዎ። በመጠኑም ቢሆን አቀላቅሎ መጠቀም አይቀርም ።

ጥያቄ 4፣ እርስዎ ከሚጠቀሙባቸዉ ወይም ተማሪዎች ሲናገሩ ከሰሟቸዉ ቀበልኛ አነጋገሮች የተወሰኑትን ቢጠቅሱልኝ ?

መልስ፣ ለምሳሌ ልጅ ለማለት አሽከር ፣ክፈትልኝ ለማለት ክፈተኝ በጣም የተለመዱ በጎንደር አካባቢ የሚነገሩ ቀበልኛ አነጋገሮች ናቸዉ።

ጥያቄ 5 ፣ በቀበልኛ ዘዬ /ንግግር/ መጠቀምን የኋላ ቀርነት ምልክት አድርገዉ የሚመለከቱ ወገኖች አጋጥምዎት ያዉቃሉ? እርስዎ በጉዳዩ ላይ ምን ሀሳብ አለዎት?

መልስ፣ አዎ ያጋጥማል ።መደበኛ ዘዬን በጣም አልቆ የማየት ቀበልኛዎቹን ደግሞ የገጠር አማርኛ በማለት ማንኳሰስ የተለመደ ጉዳይ ነዉ ።

ጥያቄ 6 የቀበልኛ ዘዬ ተናጋሪ መምህራንና ተማሪዎች መደበኛዉን ዘዬ ከሚናገሩ አቻዎቻቸዉ ጋር ዘያዊ ንግግርን ምክንያት ባደረገ አለመግባባት ዉስጥ ገብተዉ ያስተዋሉበት ሁኔታ አለ?

መልስ ፣ አላጋጠመኝም ።

ጥያቄ 7፣ ቀበልኛ ዘዬ ተጠቃሚ ተማሪዎች መደበኛዉን ዘዬ ሲማሩ የሚቸገሩበት ይዘት ከቋንቋ ትምህርት ዓለማዎች አንጻር በየትኛዉ ነዉ ?

መልስ ፣ በሁሉም ይዘቶች አኩል ተሳትፎ የሚኖራቸዉ ነዉ የሚመስለኝ ምናልባት በንግግር ጊዜ ሊባል ይችላል፤ ነገር ግን እንደ እንግሊዝኛ ትምህርት ንግግርን የምንፈትሽበት መልመጃ /የትምህርት ይዘት በአማርኛ ትምህርት ዉስጥ አለ ማለት አይቻልም።

ጥያቄ 8፣ በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር በቋንቋዉ ትምህርት ሊያስከትሏቸዉ የሚችሉ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ቢጠቅሱልኝ?

መልስ፣ በመምህርና በተማሪ፣ እንዲሁም በተማሪዎች መካከል አልፎ አልፎ መናናቅ እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

ጥያቄ 9፣ መደበኛ ያልሆኑ ዘዬዎች በቋንቋዉ መኖር ምክንያት የሚፈጠሩ ችግሮች መማር ማስተማሩን እንዳያስተጓጉሉት ምን ቢደረግ የተሻለ ይሆናል?

መልስ፣ ዘዬነክ ርዕሰ ጉዳዮችን በስፋት በትምህርቱ በማካተት የተማሪዎችን ተጋልጦ በማስፋት ፣ሌላዉ ደግሞ የቋንቋዎችን እኩልነት በሚገባ እንዲረዱት ለማድረግ ቢሰራ ችግሩን ማስወገድ ባይቻልም አንኳ መቀነስ ግን የሚቻል ይመስለኛል።

ጥያቄ፣ 10፣ቀበልኛ አጠቃቀሞችን በመደበኛዉ የቋንቋዉ ትምህርት በንግግርም፣ በጽሁፍም በስፋት ለሚጠቀሙ ተማሪዎች የእርማት ግብረ-መልስ የሚሰጡት እንዴት ነዉ?

መልስ ፣ በንግግር የሚደመጡት ዘያዊ አነጋገሮች ቅጽበታዊ በመሆናቸዉ ለእርማት አሰጣጥ ያስቸግራሉ ።በጽሁፍ የሚቀርቡትን ግን መስፈርቶችን በመስጠት ተማሪዎች ን ራሳቸዉን ማስገምገም ስህተት የሚሏቸዉን ደግሞ ከምን አንጻር እንደሆነ እንዲያስረዱ ማድረግ ይቻላል ።በተጨማሪም በሰሯቸዉ የወረቀት ስራዎቻቸዉ ላይ ስህተቶችን በአይነት በአይነት ጽፎ ማሳየት የእርማት መንገዶች ናቸዉ።

መምህር ስድስት፡-

ጾታ፣ ወንድ

የትምህርት ደረጃ፣ የመጀመሪያ ዲግሪ

አማርኛን በማስተማር ያላቸዉ ልምድ፣ 11 ዓመት

ቦታ፣ ፊልጶስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት

ሰዓት፣ 3፡30–4፡10

በመጀመሪያ በቃለመጠይቁ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ሆነዉ በመገኘትዎ አመሰግናለሁ።

ጥያቄ 1፣ እርስዎ የየትኛዉ ዘዬ ተጠቃሚ ነዎት?

መልስ፣ የጎጃም ዘዬ እናገራለሁ።

ጥያቄ 2፣ በአማርኛ ቋነቋ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር ቋንቋዉን በማስተማር መማር ሂደት ዉስጥ ምን አስተዋጽኦ ሊኖራቸዉ ይችላል ?

መልስ ፣ ቋንቋዉንና የቋንቋዉን መገለጫ ባህርያት ለምሳሌ ቋንቋ ተለዋዋጭ ነዉ፣ ረቂቅ ነዉ፣ ቋንቋ መግባቢያ ነዉ የሚባሉትን ባህርያት ዘዬዎችን ማሳያ በማድረግ በተጨባጭ ማሰተማር ይቻላል።

ጥያቄ 3፣ እርስዎ የሚናገሩት ዘዬ መደበኛዉን ቋንቋ ለማስተማር በሚፈልጉበት ጊዜ ጣልቃ አየገባ ያስቸግርዎታል?

መልስ ፣ አዎ ያስቸግረኛል ።

ጥያ 4 ፣እርስዎ ከሚጠቀሙባቸዉ ወይም ተማሪዎች ሲጠቀሙባቸዉ ከሰሟቸዉ ቀበልኛ ዘዬዎች የተወሰኑ ምሳሌዎችን ይጥቀሱልኝ ?

መልስ፣ ጎጃምኛ ዘዬ (አዎ ፣ አዋ ፤አዎን፤ አዎድ ፤ ወግድ ፤ የሚሉትን) መጥቀስ ይቻላል።

ጥያቄ 5፣ በቀበልኛ ዘዬ መጠቀም የኋላቀርነት ምልክት አንደሆነ የሚቆጥሩ ወገኖች ያጋጥማሉና የእርስዎ እይታ ምን ይመስላል?

መልስ፣ አይ ስህተት ነዉ። ዘዬዎችም ቋንቋዎችም እኩል ናቸዉ ።ዘዬን ከዘዬ ቋንቋን ከቋንቋ ለማበላለጥ የሚደረገዉ ሙከራ የተሳሳተና ጤናማ ያልሆነ ነዉ።ምንም አይነት ሳይንሳዊ ድጋፍ የለወም ።

ጥያቄ 6፣በቀበልኛ ዘዬ ተናጋሪ መምህራንና ተማሪዎች መካከል ዘዬን መሰረት ያደረገ ወይም ምክንያት ያደረገ አለመግባባት ተፈጥሮ አስተዉለዉ ያዉቃሉ?

መልስ ፣ ከሚናገረዉ ዘዬ ተነስተዉ ተማሪዎች ቅጽል ስም የሰጡት አስተማሪ አዉቃለሁ።ጠብ ሲፈጠር ግን አይቼ አላዉቅም።ጎጃምኛ ዘዬን አብዝቶ የሚጠቀምን መምህር ተማሪዎቹ "ቆምጨዉ " የሚል ቅጽል ስም ሰጥተዉት በዚሁ ቅጽል ስሙ መምህራንም ሳይቀሩ ይጠሩታል። ቆምጬ በተለምዶ በአዲስ አበባ የቤት መወልወያና፣ ማር፣ ቅቤ በማዞር ለሚሸጡ፤ በዙዉን ጊዜ ከጎጃም አካባቢ ለሚመጡ ወገኖች የተሰጠ መጠሪያ ነዉ።እነዚህ ወገኖች የሚጠቀሙት አማርኛ ቀበልኛ ዘዬዎች የበዙበት ነዉ። ለምሳሌ (ኧሯ፣ ክላ፤ እማትከላ ፣ ምን አባትህ ነዉ? አንተ እነዳልቦነቅስህ ፣ ኧረ እሱንማ አርጌ የመዠረጥኩት፣

ምሳ በላነ ፤ ጠጣነ ፣ አርጎ ያስጠላኝ) ፣ እንዲህ ብለብለዉ ….) በመሳሰሉት ንግግሮቻቸዉ ይታወቃሉ፡፡

ጥያቁ 7፣ቀበልኛ ዘዬ ተናጋሪ የሆኑ ተማሪዎች የትኛዉን የአማርኛ ቋንቋ ይዘት ለመማር ይቸገራሉ ብለዉ ያስባሉ?

መልስ፣ መጻፍና መናገር በነዚህ ክሂሎች ዘያዊ ንግግሮቻቸዉ መጠነኛ ችግር ሊፈጥሩባቸዉ ይችላሉ፡፡

ጥያቄ 8፣ በአማርኛ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎች መኖር ቋንቋዉን በመማር ማስተማር ሂደት ምን አይነት ተጽእኖዎች ሊኖሯቸዉ ይችላል?

መልስ፣በጎ የሆነ ተጽእኖ ይኖራቸዋል ብዬ አስባለሁ፡፡ በቋንቋዉ ትምህርት ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ናቸዉ ፡፡የቋንቋዉን ደረቅ ሳይንስ ከማስተማር መማር በዘለለ ስነጽሁፋዊ ይዘቱንም ለማስተማር ዘዬዎችም ጠቀሜታ ይኖራቸዋል፡፡

ጥያቄ 9፣ዘዬዎችን በተመለከተ ያለዉን የተዛባ አመለካከት ለመቀየር መፍትሄዉ ምንድን ነዉ?

መልስ ፣በማህበረሰቡ ግንዛቤ መፈጠር የተሻለ አማራጭ ይመስለኛል፡፡

ጥያቄ 10፣ እርስዎ በመደበኛዉ የትምህርት ክፍለጊዜ ቀበልኛ ዘዬዎችን በንግግራቸውም፣ በጽሁፋቸዉም ቀላቅለዉ ለሚጠቀሙ ተማሪዎች ግብረ መልስ የሚሰጡበት ሁኔታ ምን ይመስላል?

መልስ፣ የማርማቸዉን ወረቀቶች ግብረ መልሰ እጽፍባቸዋለሁ፡፡በንግግር ጊዜ ከሆነ የተጠቀሙትን ዘዬ በመደበኛ ቃል ወይም ሀረግ እቀይርና አሳያቸዋለሁ ወይም ተማሪዎችን እራሳቸዉን ተጠቅሜ ትክክለኛዉ መልስ እንዲሰጥ አደርጋለሁ፡፡